ዛሬ ይሙት ፣ ነገ ይሙት ሳይለይለት ምን ታረጊለታሽ ! ተማክረው ምን ያሉት አይገማም አሉ” አሉ ቀኛዝማች በኩራ ስሜት ።

“እኔማ ምን አለኝና ምን ላርግለት፣ በምን አሳብቤ?” አሉ ሳይታወቃቸው ።

“እንዴት የለሽም፣ ለሰበብም ከሆነ ደሙ ፈሰሷል።”

“ለሱ እሚሆን ምን አለኝ፣ እስቲ አንቱ ንገሩኝ?” አሉ ችግሩ የተቃለለ እየመሰላቸው ።

“ምነው ያ ዘመድ ያመጣልሽ ያልተቀጠቀጠ ወጠጤሽስ ?”

“ብልጥ ልጅ አስቀድሞ ያለቅሳል አሉ —— በሉ እንዳልኩ ።”

“እሄሄ! ትልቅ ነገር ሆነና ነው?! አዞሮ ማየት ነውዴ —— ”

“እኮ ምን ወጣኝ? —— ይሁን እኮ ነው ያልኩሁ ።”

“እኛን ብሎ በመጣና እኛን ብሎ በተጠጋ ——— ” ሳይጨርሱ ፣

“የምን ነገር መደጋገም ነው ። ተንግዴህ ውሾን ያነሣ ውሾ ነው ያሉት ቢጤ ነው ። ከኔና ካንቱ እንዳያልፍ —— ባንቱ ያምራል ፣ አንቱ ወስደሁ ስጡት” አሉ የሰውዬውን ልብ ለማማለልና ውዴታቸውን ለማሳየት ።

“የለም! የለም! ያንቺን አንቺ አድርሺ ፣ —— እኔ ደሞ የኔን”

“ደሞ ሌላ?”

“አንቺኮ ዘመድሽ ስለ በደለው ፣ ማንም ሳያውቅ መካስሽ ነው ፣ ማገገሚያውን ። መቼም ወሬ መያዣ የለውም ። ጨማምረው ቢነግሩትም አፍ ማስያዣ ይሆናል —— ቀላል እኮ ነው ፣ አንቺ በናትነቴ ሰጠሁህ ትይዋለሽ ፣ የኔን ደሞ ዋል አደር ብለን እንሰጠዋለን ። እ! —— ይኸው ነው” ብለዋቸው ወደ ምንዳዬ ጐጆ አመሩ ።



# ምዕራፍ ሐያ

አውቶቡሱ በሁለት ትይዩ ጐራዎች ላይ እንደ ጀሮ ተለጥፋ በሸለቆ ውስጥ የተቆረቆረችውን የካራቆሬን ከተማ ዐልፎ ጠመዝማዛውን ቁልቁለት እንደ ወረደ ፣ ወ/ሮ ደጅ ይጥኑ እጐናቸው የተቀመጠውን መንገደኛ ፣

“ወንድሜ፣ የሣር አምባ ሰው መስልኸኝ —— ” አሉት በለዘብታ ።

“አዎድ ነኝ” አለ ፈጠን ብሎ ።

“ሰው ልጠይቅህ አስቤ ፣ ታሁን—አሁን እያልኩ ሳመነታ ——”

“ማንን?”

“ቀኛማይ በላይነህ ታፈሰን ታአቸው የለ?!” አሉ እንደሚያውቃቸው እያወቁ ።

“ሣርአምባ ተወልጄ እሳቸውንማ ታላወኩ?——”

ቀስ በቀስ ወሬ ቀጠሉ ። ሌላው ቀርቶ የቀኛዝማችንና የሳቸውን ግንኙነት ጠቀስ አድርጎ በማስደሰት ፣ እሱ ወደ ማጀቴ ሲገሠግሥ እግረ—መንገዱን ያየውንና የሰማውን ሁሉ ነገራቸው ። ክፉኛ ደነገጡ ።

“የኔ መድካኔ—ዓለም የት ሔዶ? ነግሬዋለኋ! አደራህን ብየዋለሁኋ! እኚህ ሰውዬ አንድ ነገር ቢሆኑ ኖሮ ፣ አዳሜ ይቺ ገደ—ቢስ እያለ መግቢያ መውጫ ያሳጣኝ ነበር ። የእሱም ቢሆን ነገ ተነገ ወዲያ ይሽርለታል ፣ ዋናው ነገር አለመሞቱ ብቻ” አሉ በልባቸው ።

አውቶቡሱ ደብረ—ሲና ከተማ እንደ ደረሰ ከተንገሮቹ በከፊል ለቁርስ አይሉት ለምሳ በየተራ ሲወርዱ ወ/ሮ ድጅ—ይጥኑ ላቀችን በእጅ ምልክት “አንቺ እዚያው ቆዪ” አሏት ።

አብሯቸው ከሚጓዘው የሣር አምባ ሰውዬ ጋር ከመንገድ በታች ምግብ ቤት ገብተው እየተቆነኑ ጥቂት ከበሉ በኋላ ፣ “በል አንተ ቅልጥፍጥፍ አርገህ ብላ ፣ እንዴት ያለ ማለፊያ ወጥ መሰለህ ፣ እኔ መኪና ላይ ስወጣ ብዬ ብዬም አይለኝ” ብለው ተዉለት ። ቤትዮዋ የምግቡን ዋጋ ተሽቀዳድመው ከፈሉ ። ባላገሩ ሰውየም ደስ

ብሎት አመሰገነ ። መንገደኞች ከየቆዩበት ሲመለሱ ወ/ሮ ደጅ ይጥኑም ተመልካቾቻቸውን እያስገረሙና ፥ የገላ ቅርፅ አይተው የሚቋምጡ ወንዶችን የስሰና ምራቅ እያስዋጡ ተመልሰው ገቡ ። ለላቀች ግን ፥ አውቶቡሱ ውስጥ እየተዘዋወሩ ቆሎ ከሚሸጡ ልጆች መኻል አንዱን ጠርተው በምልክት ካሳዩት በኋላ የዐሥር ሣንቲም የገብስና የሽምብራ ቆሎ አዘዙላት ። ለራሳቸው ከገዙት ሙዝም ሳኩላት ። በትልቅ አገልግል ጥሰቅ ብሎ የተቋጠረው የዶሮ—ወጥና እንጀራ ግን ፥ አዲስ አበባ ለጉራና ለዝና ቀርቦ የሚበላ የባለሙያነት ማስመስከሪያ ነው ።

ወይዘሮ ደጅ ይጥኑ የሚበሉና የሚጠጡት ፥ የሚለብሱና የሚያጌጡበት ነገር ሁሉ ከሰው የበለጠ ቢሆንላቸው ደስታውን አይችሉትም ። የሚያኮራ ስምና ዝና ይወዳሉ ።

"ጥሎብኝ ፥ ከትንሽ ሰው ጋር መዋል አይሆንልኝም ፥ መብልም ቢሆን ጥፍጥ ያለች በትንሿ ትበአለች ። አሰስ ገሰስ አልወድም" ይላሉ ።

ቀኛዝማችን የወሸሙ ሰሞንም ፥ "እያዩ ነው መውደቅ ፥ ለንዲህ ያለው ሰው ቢበለጡም አይቆጭ ፥ ከማን ጋ ነው ቢባልም ስማቸው ብቻ ያኮራል ። ካንድ ቁና ኀያ አንድ ቃጢ ስንዴ ይበልጣል" በማለት ከጐረቤቶቻቸው ጋር አውርተዋል ። ወደ አዲስ አበባ ለመሔድ የተነሡበትም ዋናው ምክንያት ፥ አዲስ የተመረጡት የሕዝብ እንደራሴ የቀኛዝማች በላይነህ ሚስት ናቸው በመባል የዝና ተካፋይ ለመሆን ነው ። ይህ ፍላጐታቸው በሰውዬው በኩል ካልተሳካ ሌላ ብልሃት ከመፈለግና ከማስፈለግ ቸል አይሉም ።



## ምዕራፍ ሐያ አንድ

የምንዳዬና የሞተው ሰውዬ ጉዳይ እንደ ሌሎች ተራ ወሬዎች ቶሎ በመቀዝቀዝ ፈንታ እንደ ፍግ ረመጥ ውስጥ—ውስጡን ተጋጋመ ። የአፈሣ ቤተሰቡን ጥሎ መሔድ በየቤቱ በተለያየ ሁኔታ ተወራ።

አንዳንዱ 'እቴዋ እያለች እንዴት የማንም ጋለሞታ ቀድማት አዲስ አበባ ወጣች' ብሎ ከቀኛማይ ጋር ተጣልቶ ነው አሉ ሲል ፥ ሌላው ደግሞ 'ሬሣ ጥባእ አድሮ ሊነጋጋ ቲል ፥ ምንዳዬን እጠይቃለሁ ብሎ ቲሔድ የምንዳዬ ሚስት ጨለማ ውስጥ ተቀምጣ ስታለቃቅስ ጥግ—ጥጉን ቲሔድ አይታ ፥ እሷም ለራሷ ፈርታ ሳታውቅ ብጠይቀው ይፈራና ይሸሻል ፤ በዚያ አፍሮ ነው የጠፋው አሉ' ይላል ። በጣም አውቃለሁ ባዩ ደግሞ ፥ ወሬውን ከየት እንደ ሰማና እንዳገኘው ሳይታወቅ 'ከየቱ ፥ ነገሩ ወዲህ ነው አሉ ፥ ምንዳዬ የቆሰለ ለት ፥ አፈሣ ከቀኛማይ ቤት የተዋሰው አገልግል ሟቹ ሰውዬ ማሽመቂያ ላይ ተገኝቶ ነው አሉ ። በዚህ የተነሣ ነገር እንዳይባባስ ብሎ ነው አሉ'ይላል ።

ሁሉም በየቤቱ የአፈሣን ነገር እያነሣ የየግሉን ጥርጣሬና ግምት ሲሰጥ ፥ የመጨረሻዋ ወሬ ግን በየት በኩል እንደ ተገኘች ማንም አያውቅ ።

ቸርነት ፥ የወይዘሮ እልፍ ይከንዱን ወጠጤ እረፋዱ ላይ አርዶ ሥጋውን በቆሪና በሰዴቃ ላይ ከፋፍሎ ወደ ቤት ካስገባ በኋላ ምንዳዬ አጠገብ ዐረፍ ብሎ ፥

"እመመህ መሰል ምንዳ?" አለው ።

"አይ ደግ ነኝ ፥ ምንም አይለኝ ፥ እንደ ፈራሁትም አደል!"

"ሥጋ ለሥጋ መሆኑ በጀ ፥ አጥንትህንማ ቢጨርፍ ኖሮ —— መቼም የኛ ነገር ጥሎብን ፥ ኮርኮም ቢያረገንም ማማረራችን አይቀር —— ሞትስ አለ አደል ? አብነቱ የጌትነቱ ነው! እኔማ እዚያ ፋፌ ውስጥ ወድቀህ በደም ተለውሰህ ቃይህ ፥ ልቤን ሰውር ነበር ያረገኝ ፥ ያደነጋገጤን ነገር አታንሣ —— "

"እኔ ደሞ ሰውዬው ባፍጢሙ ተደፍቶ ሳየው በጣም ደስ አለኝ ። ትንሽም ንድድ ያለኝ እሱም ገድየዋለሁ ብሎ ይሆን እያልኩ ሳሰብ

ነው ። እንዲህ የልቤን ሥርቼ ሰባት ዓመት ብተኛ ምናባቱ !” አለ ምንዳዬ ራሱን እየነቀነቀ ።

“ለምን የፈለገው አይሆንም! እንደ ባር—ቅል አፈንድተኸዋል እኮ! እኔ ደሞ ተሁሉም ተሁሉም የገረመኝ የማድፈጫው ፤‘ያንተ ያለህ’ አለ የኔ አገር ሰው ። ሲደለድል ከርሞ ተሠራለቲ ። ደሞ ያገልግሉ ጋጋታ ነውዬ ፣ ገና በወጉ በልቶ ሳይጨርስ ነው ከች ያልከበት ። አገልግሉን ቀኛማይ አኑረውታል ። እኔማ ጡር ሥርቻለሁ ። ፍትፍቱን አፈሰስኩት ።”

“የምን አገልግል ?” አለ ምንዳዬ በጣም ተገርሞ ።

“አላየኸውም እንዴ ?”

“አይ አንተ! እኔ ለራሴ ነፍሴን ስቼ ምኑን ዐውቀዋለሁ ?”

“እንግዲያውማ ሰውዬው እነበረበት ቦታ ላይ አገልግል ተገኝቶ” ሲል ድንገት ከውጪ የገቡት ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ‘አገልግል ተገኝቶ’ የሚሉትን ቃላት እንደሰሙ “ለሳቸው ሰጧቸው” አለ ኖር ለማለት እየተነሣ ።

የወይዘሮ እልፍ ይከንዱን ነፍስ ዳግመኛ የፍርሃትና የሥጋት ንዳድ አመሳት ። እንዲያው ለወጉ ያህል “አንቺ ልኬለሽ !” ብለው ወደ እሷ ተራመዱ ። ‘ምነው እግሬን በሰበረው’ እያሉ በልባቸው ። “እኔ አይሰማብኝ እያልኩ አሣሬን አያለሁዬ ፣ ለካ ነገሩን ቸርነትም ያውቀዋል ። እውሽ ሆድ ቅቤ አያድርም” አሉና የመጡበትን ትተው ያልመጡበትን ነገር ፣ ያውም ደግመው የማያስታውሱትን ነግረዋት ተመለሱ ።

“በል ያን የጀመርከልኝን ወሬ ጨርስልኝ” አለ ምንዳዬ አግድም እያየ ።

“መቼም ሰውዬው ሲጠረጥሩ ቆቅ ናቸው ። ምን ነገር ሹክ እንዳላቸው እንጃ እስኪ አካባቢውን ፈትሹት ብለውን” ብሎ ከመጀመሩ ፣ ሸዋርካብሽ ‘በይ ቶሎ ሒጂና የሚወራውን ሰምተሽ ነይ’ የተባለች ይመስል ፣ ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ወጣ ከማለታቸው ከች በማለቷ ቸርነት ፣ “ቶሎ ይዘነው ወጣን እልሃለሁ ፣ አንተስ ቢሆን ታውቀው የለ ፣ እንዲህ ነበር ነገሩ ሁሉ” ብሎ ወሬውን የጨረሰ ለማስመሰል ዝም አለ ። ምንዳዬም ወሬው የተቋረጠበት ምክንያት ገባው ።

* * *



ቀኛዝማች በላይነህ ታፈሰ ግቢ ውስጥ ትልቅ ትንሹ በደስታ እያውካካ ይተራመሳል ። መምሬ ተክለ ጊዮርጊስም ፣ ከውቢት ሚካኤል ፣ ከደብረ ወርቅ ማርያምና ከካብ ሥላሴ አብያተ ክርስቲያናት የጠሯቸውን ካህናት ባንድ ወገን አስቀምጠው ለሽኘታ ስንብት ቀርበዋል ። ከካህናቱ ፊት—ለፊት በስተደቡብ ወገን እርም አይቀሬና መሰሎቹ በየሥራቸው ያሉትን ተጋዦችና ገባሮች ከሰበተጀርባቸው ደርድረው በየደረጃቸው መደዳውን ቆመዋል ። ምድረ—ግቢው ባይጨናነቅም ሞልቷል ።

ገበሬዎቹ አዳፋ ሸማ ፣ የነተበና የተጣጣፈ እጀ ጠባብ ወይም ኮት ፣ የተደራረተና ባያሌ ክር የተወሰወሰ እፈ— ሰፋፊ ዙሪያ ቅምቅም የመናኛ አቡጀዲና ካኪ ቁምጣ ሱሪ ለብሰው ረድፍ—የለሽ የሰው አጥር ፈጥረዋል ። በዐይነ—ጅምላ ትኩር ብሎ ላያቸው በሰው ቁመት ልክ የተከረከመ ሰደድ እሳትና ጢስ የገረፈው ግንድ ይመስላሉ ። ሆዳቸው ቢሞላም ፣ ፊታቸው አይወዛም ። ከግላቸው የደስታ ክልል ውጪ ቢፈጉም ፣ ውስጣቸው ረመጥ ነው ። ሲያመርቱ ነጣቂ ፣ ሲናገሩ ሸውከኛ አለባቸው ። ኑሮና ተስፋቸው “በእርሱ” ያውቃል ላይ ተመሥርቶ የነገውን ኑሯቸውን ከዛሬው ለይተው አያዩትም ። የሕይወት ጎህ አይታያቸውም ። ውስጣቸውም ደጃቸውም ጽልመት ነው ።

ቀኛዝማች በልዩ ልዩ ምክንያት ወጣ—ገባ ሲሉ ፣ ከካህናቱ ይልቅ ገበሬዎቹ ፣ እንዱ በሌላው ትከሻና ጭንቅላት ላይ አሻግረው ይመለከቷቸዋል ። ወደነሱ መለስ ብለው አየት ባደረጉ ቁጥር ደግሞ ፣ እያንዳንዱ እሱን ያዩና ያወቁት እየመሰለው በደንብ እንዲታይ ፣ ወይ ካይኑ ፊጠጥ ፣ ወይ ከወደ ጥርሱ በትሕትና ገለጥ ፤ አለበለዚያም አንገቱን አስገ ለመታየት ይሞክራል ። በርግጥ ያዩት እኔን ነው ባዩ ደግሞ ድንገት እጅ እነሣለሁ ሲል እፊቱ ከቆመው ሰው ትከሻ ወይም ጀርባ ጋር ይጋጭና በድርጊቱ ያፍራል ። አብዛኛው ሰው በግምቱ እኔን ደህና አርገው አይተው ለይተውኛል ፣ እንኳንም አልቀረሁ ። ሌላው ቢቀር እንደ ልቤ አርሳለሁ” ይላል ።

ቀኛዝማች ፣ ካዳራሾቹ ፊት ለፊት ግቢው መኻል ወደ ካህናቱ ቀረብ ብለው ከተቀመጡበት ድጋፍ የለሽ አጠር ያለ የጠፍር ወንበር ላይ ሆነው የሚፈልጉትን ሰው በየተራ እያስጠሩ ፣ ትእዛዝ ፣ ምስጋናና አደራ ከሰጡ በኋላ ፣ ካህናቱን በስተቀኝ ወገን ባለው አዳራሽ ፣ ገበሬዎቹንና በነሱው ደረጃ የሚገኙትን ደግሞ በስተግራ በኩል ባለው አዳራሽ ግብር አበሉ ። ለምንዳዬም ተላከለት ። ገበሬዎቹ የቀኛዝማች ወኪሎችና አፍ—ጠባቂዎች በሌሉበት እርስ—በርሳቸው ሲያወሩ ፤ ብሶትና ምኞታቸውን አይደባበቁም ። የልቦቻቸውን በሮች ከፍተው

ሐሳቦቻቸውን ያስተናግዳሉ ። ቦጥቧጭ ወይም አስቦጥቧጫቸው ብቅ ካለ ደግሞ ፤ በሮቻቸውን ቶሎ ይዘጉና በመጣጣ ፊቶቻቸው ላይ የቆረፈደ ፈገግታ ያሳያሉ ።

ሁሉም ነገር እንደ ታሰበው ተጠናቆ ፤ የፓርላማው ተመራጭ ቀኛዝማች በላይነህ ታፈሰ ወደ አዲስ አበባ የሚነሡባት ሰዓት እንደ ደረሰች ፤ በመጀመሪያ በትላልቅ የፍየል ሙክት ስልቻ የነጭ ጤፍ ዱቄት የተጫኑ አምስት አህዮች በትልቁ የአጥር በር ሲወጡ በተፈጠረው የሽቅድድም ግፊያ ሦስት—አራቱ በተለያየ ቃና አንዛርጠው ፤ አንድ ሁለቱ ፋንዲያ ጣሉ ። ቀጥሎ ፤ ቋንጣ የሞላ ትላልቅ አገልግል ያንጠለጠሉ ፤ ቅቤና ልቁጥ በርበሬ (ድልህ) የያዘ ገረወይና የተሸከሙ ሰዎችና በመጨረሻም አረንጓዴ የልብስ ሳጥን የተጫኑ ሁለት አህዮች ጓጉንቸር ቁልፋቸውን እንደ ጉትቻ አንጠልጥለው እያንኳኩ ተከታትለው ወጡ ።

ቀኛዝማች ፤ ድፍን ጥቁር የሱፍ ልብሳቸውን ከነሰደርያውና ፤ በነጭ ሸሚዝ ላይ ቡናማ ክራቫት አስረው ፤ ዙሪያ ወለሏ ያልሰፋ ባለሐር መቀነት ልከኛ ጥቁር ባርኔጣቸውን ደፍተው ፤ አፍንጫዋ ሾል ያለ ጥቁር ጫማ አድርገዋል ።

ባንድ በኩል ወሬው ተሰምቶ ዝናቸው እንዲስፋፋ ፤ በሌላ ወገን ደግሞ በበላይነት ባሕርይ እየተንቀባረሩ ሁሉንም አሽቆልቁለው ሲመለከቱ ዘውድ ቀረሽ የሣር አምባ ንጉሥ መሰሉ ።

ከዚያው አካባቢ የመጡ ሴቶች ደግሞ ፤ እንደ ባሎቻቸው በሁለቱ አዳራሾች ግራና ቀኝ እንደ ታሰረ የማገዶ እንጨት ሰብሰብ ብለው ፤ የቀኛዝማችን አለባበስና አኳኋን ይመለከታሉ ። ባጋጣሚ ወደ እነርሱ መለስ ያሉ እንደሆን ዐይኖቻቸውን ሰብረው አንገታቸውን ይደፋሉ ። አንዳንዶቹ በሹክሹክታ ፤ “ዛሬ ታቦት ቢያሸክሟቸው ሚካልን ይመስሉ ነበር” ብለው ሲሸረድዱ ፤ ሌሎቹ ደግሞ በሰደሪያቸው ላይ ወደ ፊት ገፍቶ በነፋስ እንደ ተሞላ ወናፍ የተቀቀተተ ቦርጫቸውን ይመለከቱና ፤ “አንቺዬ! አቤት! ሆዳቸው ምን አክለ ልጇ ፤ ቅርጫት መሰሉ አደለም እንዴ? እዚያማ ሲሔዱ ድብኝት ሆነው ቁጭ ነው ። እዝጊዮ ያንተ ሥራ! አሁን ይኸ የለበሱት ጥንዚዛ የመሰለ ነገር ምን ያህል ያወጣ ይሆን?” በማለት እስበሳቸው ሲጠያየቁ ከመካከላቸው አንዷ ፤ “ኧረ ስንትና ስንት መቶ ሽልንግ ነው ሲሉ ነበር እቴ! የጥማድ ይሁን የሁለት ጥማድ በሬ ዋጋ ያወጣል ቲሉ ሰምቻለሁ” ብላ መለሰች ። አንዳንዷ ደግሞ ፤ “እስቲ ታልጠፋ ልብስ አሙካ የጠገበ ያገሬን ባና የመሰለ ይልበሱ?” በማለት ታናንቃለች ።



ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ፤ ምኞቱ እንደ ተሳከለት ሰው በመደሰታቸው ሰዉን ሁሉ ተራ በተራ እየሳሙ ፤ ቢሳሙ ደስታቸው ነበር ። የሞቁት እንሶስላ ዐልፎ — ዐልፎ እጅና እግራቸው ላይ ጠቁሮ ፤ ሌላው የተንተረከከ ፍም መስሏል ። ቀኛዝማች “እልቦና አምባሩን ተይው” ባይሏቸው ኖሮ አዘጋጅተው ነበር ። ቱር ብሎ ታጥቦ የወተት ዐረፋ የመሰለ ልብሳቸውን ለብሰው ፤ ጥቁር ሻሻቸውን አስረውና ፤ ሰማያዊ ሸራ ጫማቸውን አድርገው ከሣር አምባ የሚወጡበትን ደቂቃ በጉጉት ይጠባበቃሉ ። አጠር ቀጠን ያሉ ናቸው ። እንዲህ እንደዛሬው ቅናትና ንዴት ፤ እልህና ብስጭት ፈገግታና ሙብታቸውን ሳይገፈው ወዛቸው የሐምሌ ቡቃያ ይመስል ነበር ። ጠየም ያለው ስልክክ ፊታቸው በመጠኑ ጐላ—ጐላ ካሉት ነጫጭ ዐይኖቻቸው ጋር ቀልብ ይዘርፋሉ ። ጥቁሩ ጸጉራቸው ሹርባ ቢሠራ ትከሻቸው ላይ ባይኩነሰን ስም አንገታቸውን ይሸፍናል ። ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ የተበደሉት ከወደ ዳሌና እግራቸው ነው ። የዳሌ ነገር ሲነሣ አይወዱም ፤ ባተሞንዳላ ፤ ተረከዘ ሎሚ እየተባለ ሲደነቅ ደማቸው ይፈላል ። እንደ ደጋን ጐበጥ ባለው ቅልጥማቸው ላይ ቁጭ — ቁጭ ያለችው ባታቸው የተጨፈለቀ ሙዝ ትመስላለች ። የእግራቸው አወራረድ ከአካሔዳቸው ጋር የብልሽት ሽርክና የፈጠረ ይመስል አረማመዳቸው ፈጣን ፤ አጣጣላቸው ወንካራ ነው ። የመጀመሪያ ባላቸውን ፈትተው ወላጆቻቸው ቤት በነበሩበት ያፍላ ወቅት ቁንጅናቸው ቀኛዝማችን ለመማረክ በጣም በቂ ነበር ። በጠይሙ ገላቸው ላይ ያለው ንቅሳት ጐልቶ ባይታይም ፤ የውበታቸው ግርማ የነበረው የወተት ዐረፋ መሳይ ክርክም ጥርሳቸው ፤ በፈገግታ ጸዳል ሲታጀብ የወንድ ቀልብ ይሰልብ ነበር ። ቀኛዝማችንም እያዳፋ አስገብቶ ሴትዮዋ መውደድ ውስጥ የሸጎረባቸው እሱው ነበር ። የኋላ — ኋላ ሦስትና አራት ልጆች እንደ ወለዱ ፤ ያ የአፍላ ሞንዳላ አካላት እየጎደለ ፤ ያ በጊዜው ሲያናጥር የነበረ ሙቀመጫቸው እንደ መንገደኛ ስንቅ እያለቀ ፤ ወንካራ እግራቸውም እየባሰበት ፤ ውበታቸውም ቀስ በቀስ እንደ እብቅ በነነ ። በተወላጅነትና በንጹሕ የዘር ሐረግ የተመረጡት ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ፤ በመጀመሪያ ውስጥ — ውስጡን ባንዳንድ የገበሬ ሚስቶች ፤ በመጨረሻም በወይዘሮ ደጅ ይጥኑ ቅምጥ መሆን አንጀታቸው አርሮ ፊታቸው ከስሏል ። ምንጊዜም ድንቡሽቡሽ ገላና የሚያረገርግ ቂጥ የሚወደው የቀኛዝማች በላይነህ ልብም ጓዙን ጠቅሎ ማጀቱ ጋለሞታ ቤት ሲገባ ነፍሳቸው ተናጋች ።

ዛሬ ከብዙ ሐሳብ እፎይ የሚሉበት ፤ ከምንዳዬ ዐይንና ከአፈሣ የወቀሳ መልዕክት የሚገላገሉበት ፤ ከሚቋ ሽፍታ የቅርብ ትውስታና ካስኳደችም የምሬት ልቅሶ የሚያመልጡበት ዕለት ነው ።

በተለይም ያ ያን ያህል አበሳጭቶ ያስቃያቸው አብር የመሔድ ጉዳይ እንዲህ መሰናከሉ ሁሉ ተወግዶ ለመሔድ በመብቃታቸው በጣውንታቸው ላይ የነበራቸውን የበላይነት ያረጋገጡ መሰላቸው ።

የቀኛዝማች የጭን በቅሎ ውድድሩን ባሸነፉ ሰሞን የተገዛላትን አዲስ ግላስ ለብሳ ፣ ልጓሟን እያነከች ዐረፋና ልሃጯን ስታዝረበርብ ቸርነትና መታፈሪያ አጠገቧ ቆመው ትንፋሿንና ፋንድያዋን ፣ ሽብረክ ብላ ስትሸናም ግም ሽንቷን ያሸታሉ ። ምንጊዜም ሽንቷን ስትሸና "ምናባቷ!" ብለው ፊታቸውን ያዞራሉ ።

ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ፣ ጐረቤቶቻቸውን ሲሰናበቱ አንዳንዶቹ እንባቸውን እያበሱ ፣ "እስቲ ይእናው እምዬዋ ፣ በደህና ያግባሁ ፣ የጤናና የሲሳይ አገር ይሁንልሁ ፣ አድባሯ ትቀበልሁ" አሏቸው ።

ከግቢ ሲወጡ ምንዳዬን ከነቤተሰቡ እሰበሰብ ላይ ተቀምጦ አዩት ። ልኬለሽ በወቅቱ ስለ ምንም ነገር ሳታስብ ተነሥታ ሔዳ ሳመቻቸውና ፣ "እንግዲህ መሔድሁ ነው ? በሉ በደህና ያግባሁ! አቤት የኛ ነገር ፣ አሁንማ ቤቱም ደጁም ጭር ማለቱ ነው ። መቼ መሆኑ ነው መምጫሁ?" አለቻቸው ፣ ከፊሉ ካንገት በላይ ።

"አይ ያንቺ ነገር ፣ እኔ ደሞ ምኑን ዐውቄው እቴ" ብለው ወደ ምንዳዬ ሔድ አሉና ፣ "እስቲ በርታ በርታ በል ልጄ! የውሻ ቁስል ያርግልህ! እሳቸውም መዳኒት ገዝቼ እልክለታለሁ ቲሉ ነበር ። ይኸ ተማጀቴ ያመጡልህ ጠእምህ የለ ? እኔም አዘከራቸዋለሁ ። በል ደህና ሁን"አሉት ።

"በሉ ደህና ዋሉ" አለ በይስሙላ አክብሮት የግድ እየተነሣ ።

"አሜን" ብለው ፈጠን ባለ ርምጃ ሲወጡ ሴቶቹ ተከተሏቸው ።

ምንዳዬ ወደ ልኬለሽ ዘወር ብሎ ፣ "እኔ እኮ ያንቺ ነገር ይገርመኛል ፣ እስቲ አሁን ዘለሽ መሳምሽ ምን ይባላል ?" አላት ።

"አይ አንተ ፣ — — ወድጃቸው መሰለህ ? — — የንከሻ ያክል ቁጠረው ።"

"'ድመት መንኩሳ ዐመሏን አትረሳ' አሉ አብዬ ይነሱ ። ሰው አግኝተሽ ሙተሻል ።"

"ላንዳፍታ ምን ይጐዳኝ መሰለህ! ምነው ብዙ ነገር ስታእ" ብላ ሳትጨርስ ቀኛዝማች አጃቢዎቻቸውን አስከትለው ብቅ ስላሉ ፣ ድንግጥ ብላ ወደ ምንዳዬ ለጠፍ አለች ። እሱ አንገቱን ሰበር አድርጎ በትሕትና ቆመ ።



ቀኛዝማች ፣ ምንዳዬን ሲያዩና አብረውት ሲያወሩ ወ/ሮ ደጅ ይጥኑም በዐይነ ሕሊና ስለሚታዩዋቸው ምንጊዜም ፈገግ ይላሉ ።

"እህ—በረታህ? አሁንስ ነቃ—ነቃ እያልክ ነው አጅሬ ፣ አይዞህ ! ሰውዬው እየተመላለሱ መድኃኒት ያደርጉልህ የለም እንዴ ? አደራ ብዬ በጥብቅ ነግሬአቸዋለሁ" አሉት ከእግር እስከ ራሱ እየተመለከቱ ።

"አዎ! መሰንበቻቸውን እየተመላለሱ መዳኒት አርገውልኛል ።"

"አሁን ለጊዜው ነው እንጂ እኔም መድኃኒት እልክልሃለሁ ። የሰውየውም ቢሆን ቀላል መድኃኒት አይምሰልህ ። አንተማ አይተኸዋል ። መቼም ቢሆን ማንኛውም ነገር እኛ ባሰብነው ሳይሆን ፣ እግዚአብሔር ባለው ነው የሚፈጸመው" እንዳሉ ፣

"እግዚአብሔር ይዕቀብከ እም ኩሉ እኩይ ! (እግዚአብሔር ከክፉ ነገር ይጠብቅህ) ብሎ የለ ፣ ቅዱስ ዳዊት ። እንኳን ብቻ በዚህ አለፈለት" በማለት መምሬ ተክለጊዮርጊስ በጣልቃ ተናገሩ ። አላደነቁላቸውም ።

"በል ጠንከርከር በል ! ለማንኛውም በቀደም ነግሬህ የለ ! አይዞህ" አሉት በፈገግታ ።

"ተንግዲህማ ምን አለብኝ እበረታለሁ !" ብሎ እጅ ነሣ ። በአዘኔታና በአበረታች ሁኔታ አይተውት መንገድ ቀጠሉ ። ሰዎቹም እሳቸውን እያዩና እየተጋፉ ተከተሉ ።

"እስኪ ሒጂ አንቺም ከተል በይ እንደሰዉ፣የንቄት እንዳይ መስል።"

"ምነው ተቆጥተህ" አለች እየሣቀች ።

"ሰውዬው እኮ እንዲህ አይምሰሉሽ ፣ ሆዳቸው ሸከክ አይልም ፣ ሴትዮዋ ናቸውዪ የጭቃ እሾህ! የሴትዮዋ ነገርስ አይነሣ!" አለ በምሬት።

"እኔን ሆነህ ባየኸው አለ አሉ ሰውዬው ፣ ባዶ ዐመድ መስሎት ረመጥ ከዘገነ በኋላ ። የባልዬውን ሥራ ሴትዮዋን ሁነህ ብታየው እንዲህ አትልም ነበር ። ባንተ ንዴትማ ፣ አንተ ትብስ ነበር ። የወንድ ምን ደህና አለው ፣ አብሶ እሳቸው! "

"ወዬ ጉድ! ሴት ለሴት መረዳቱ ነው መሰል! ለሙግቱ ኋላ ያደርስሻል " እንዳላት ፣ ከመጨረሻው ሰው ኋላ ተከትላ ወጣች ። በሰዎቹ መሐል ወደፊት ስትገሠግሥ የተላከች እየመሰላቸው ገለል እያሉ ስላሳለፏት ደስ አላት ።

ሰውዬው ባጋጣሚ ከፍ ካለ ቦታ ላይ ቆም ብለው አካባቢውን ሲመለከቱ ፣ እሷንም እንዲያዩዋት ወደ ፊትም ወደ ጐንም ተንቀሳቀሰች።

በመጨረሻም ቸርነትና መታፈሪያ በቅሎ ስላቀረቡ ፣ በቅሏቸው ላይ ተቀምጠው ልኬለሽ ወደ ነበረችበት አቅጣጫ ስለ ተመለከቱ ፣ እሷም እንደ ሌሎቹ እኔንም አይተውኛል በሚል ግምት ተደሰተች ። ልኬለሽ ስትመለስ ምንዳዬ ከነበረበት አልተነሣም ።

"እህ!አዩሽ!" አላት በፈገግታ ።

"ያውም፣ ታንዴም ሁለተዬ" አለች ደስ ይበለው ብላ ።

"እንኳንም የሔድሽ ፣ እሱንስ ቢያመው ነው ፣ እሷ ብቅ ያለማለቷ ለምንድን ነው ማለታቸው አይቀርም ነበር ። በማይረባ ነገር ከመራራቅ ፣ በትንሽ ነገር መዋደድ ይበልጣል ።"

"እሱማ እውነክን ነው ፣ እኔ እንዲያው ለሳቸው ብለህ በዚህም በዚያም ስትጠቃ ንድድ እያለኝ ነውዬ ፣ መች አጣሁት" ብላ ውስጧ እያረረ ዝም አለች ።

ገንዳ ውሃ ተገኘ ስለ ተባለው አገልግል ዋናውን ምስጢር ሳይሆን ከቤት ተወስዶ ለአፈሣ መሰጠቱንና ቀኛዝማች መስማታቸውን አረጋሽ በድብቅ ነግራታለች ። ያውም 'ለማንም እንዳትነግሪ' ብላ አስምላ ። ይህም የልኬለሽ አዲሱ የቂም እርሾ ነበር ።

እሱ ባጋጠመው አደጋ ምክንያት ቀርቶ ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ እንደ ተመኙት ብቻቸውን ወደ አዲስ አበባ በመሔዳቸው እልህ ተናዶ ፣ ልኬለሽ ከቀድሞው 'ወደ እንጾኪያ እንሒድ' ፍላጎቷ ተቃራኒ በሆነ አስተሳሰብ ደሟ ፈልቶና ስሜቷ ተለውጦ ፣ "ምነው ለኚህ ለአካይስት ቤትዮ እልህ ሲባል አብሮ ሔዶ ቢሆን ኖሮ ፣ ወይ ያንዳንድ ገደቢስ ቀን ነገር" ብላ ከንፈሯን እንደ ነከሰች ወደ ቤት ገቡ ።

* * *

ቀኛዝማችና ከሠላሳ የማያንሱት ተከታዮቻቸው የዐመዴ በሽርን ቦይ አከል ወራጅ ውሃ አልፈው ማጀቴ ሲገቡ ፣ የአጃቢዎቹን ውካታ የሰሙ የመንገድ ዳር ነዋሪዎችና ልጆች ከየቤታቸው እየወጡና ጨዋታቸውን እያቋረጡ ባድናቆት እዩዋቸው ። እሳቸውም እጅ ለነሷቸው ሁሉ ፣ በል ሲላቸው ባርኔጣቸውን እያነሡ ፣ የኩራት ስሜታቸው ብቅ ስትል ደግሞ ጠርዟን ብቻ እየነኩ ሰላምታ በመስጠት በገበያው ዳርቻ አቋርጠው ፣ ወደ ዘመዳቸው ግቢ ገቡ ። የእህል—ውሃው ነገር ቀደም ብሎ ታስቦበት ስለነበር ፣ አንዳችም የመስተንግዶ ችግር አልነበረም ።



የቀኛዝማችን ወደ ማጀቴ መምጣት የሰሙ ወዳጆቻቸውና ዘመድ ነኝ ባዩ ሁሉ ፣ የሞላለት ከራሱ ፣ የሌለው ከወዳጁ እየተለቃ ፣ እንደየአቅሙ ሳይሆን ፣ ለጉራና የሚመለስ ውለታ ለመጣል ፣ 'እሱ ደሞ ምን አለው እቴ' የሚባለውና አንድ እንስራ ጠላ ፣ 'ይኸ እንኳ ቢሻው' የሚባለው ሁለት እንስራ ጠላ እያሸከመ ፣ ሌላው አንድና ሁለት ጠርሙስ ካቲካላውን እየኮለኮለ ገባ ። ሽፍን ጫማ ያደረጉና ቦላሌ የለበሱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሠራተኞች ደግሞ ፣ የፈረንጅ አረቄ እየያዙ ጠጋ አሉ ። የቆየ ወዳጅነታቸውን ለማጠንከር የፈለጉ ሦስት—አራት ሰዎች የበሬ ሽንጥ ፣ ታላቅና ታናሽ ፣ ጉድን ተዳቢት እያሸከሙ ገቡ ። የለየለት ድግስ ሆነ ።

ከያቅጣጫው የመጣው እየተበላና እየተጠጣ ሁሉም ሆዱ ሞልቶ ከለብታ በላይ ሆነ ። አንዳንዱማ ሰክሮ ሽለላና ቀረርቶ ጀመረ ። ያቁመቁሙን ፣ የተበደለ ቁጭቱን በመግለጽ ግቢው ገላጣ ቦታ ላይ ከወዲያ ወዲህ እየተንቆራጠጠ ሲያቅራራ ቀኛዝማችና የቅርብ ወዳጆቻቸው ከቤቱ ታዛ ጥግ ተቀምጠው ቁልቁል ይመለከታሉ ።

የሚካኤል ድግስ ሰሞን ሣር አምባ ድረስ እየሔደና ፣ ማጀቴ ሲመጡለትም እገቡበት ጠጅ ቤት ገብቶ የሚያሞጋግሳቸው አዝማሪም ፣ ግቢው እንደ ተሟሟቀ ደረሰ ። ከምግብና ከመጠጡ ደህና አድርጎ ቀርቅቦ ፣ እሱም በተራው የቀኛዝማችን ስም በተደጋጋሚ እያነሣ ካሞጋገሰ በኋላ፦

"ለወንድነቱማ ሱሪ መች አነሰው ፣
ቀኛማች በላይነህ ቀሚሱን ለበሰው ።
ከሰው መርጦ ሹመት ፣ ከንጨት ለታቦት ፣
ጥንቱንም ነበረ በብሉይ አሪት ።"

ብሎ በማግጠሙ አንድ ወዳጃቸው ድፍን አምስት ብር ሸለሙት ። ሦስቱም ደስ አላቸው ።

ሁሉንም ስካር ገላገላቸው ። አብዛኛዎቹ ከሣር አምባ የመጡት ሸኚዎች እቤት ውስጥና እደጅ በየጥጉ ሲተኙ ፣ የማጀቴዎቹ ግን ወደየቤታቸው ሔዱ ።

የቀኛዝማች ዕቃ ጧት አውቶቡስ ላይ እንደ ተጫነ ፣ እሳቸው ከሾፌሩ በስተቀኝ ካለው የፊት ወንበር ፣ ባለቤታቸው ከሾፌሩ ኋላ ሁለተኛው መደዳ ላይ ተቀመጡ ። አብዛኛዎቹ ሸኚዎች በሰውዬው በኩል ፣ የሴትዮዋ ዘመዶችና ዐልፎ ፣ ዐልፎ ቀኛዝማች ዘንድ ባማላጅነት የረዷቸው አንዳንድ ሰዎች ደረስ መለስ እያሉ በሌላ በኩል አንጋጠው ይመለከታሉ ። ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ድፍን የማጀቴ

ሰው እያየና እየሰማ ከባለቤታቸው ጋራ ወደ አዲስ አበባ ለመሔድ በመብቃታቸው ልባቸው ፈንድቋል ።

“እንዲህ የልቤ ደርሶና እንጀቴ ርሶ ፣ ለምን ዛሬ ማምሸዬን አል ሞትም” እስከ ማለት ደረሱ ። አውቶቡሱ ሲንቀሳቀስ አብዛኛው ሰው በተደጋጋሚ እጅ ሲነሣ ፣ ቀኛዝማችም ባርኔጣቸውን አውልቀው ተሰናበቱ ። ሴትዬዋም ቶሎ—ቶሎ ራሳቸውን እየደፉና እያቀኑ“ደህና ሰንብቱ” አሉ ።



## ምዕራፍ ሐያ ሁለት

ወይዘሮ ደጅ ይጥኑ ፣ ከታላቁ ቤተ መንግሥት በስተ—ምሥራ ራቅ ረባዳው ቦታ ላይ ከተሠራው ከእናታቸው አንት ግቢ ውስጥ አንድ ሰፊ ባለ ጓዳ ክፍል ተሰጥቷቸው ደህና ተቀምጠዋል ።

በአጎትነት ስም የሚጠሯቸው አቶ ወርቅነህ ደመቀም ከንጉሡ በስጦታ ፣ ከመኳንንትና ሹማምንቱ በመማለጃና በልመና ሰፊ የከተማ ቦታና የገጠር መሬት ይዘው ፣ ጥሪት ያበጁና ቋሚ ንብረት ያደራጁ የታወቁ የጽሕፈት ሚኒስቴር ሁለተኛ መዝገብ ቤት ዲሬክተር ናቸው ። የሽምግልናቸውን ምዕራፍ ከጀመሩ ሰንበትበት ቢሉም ዙሪያውን የቆመላቸው ረዳትና የገንዘብ ወጋግራ ቀጥ አድርጎ ስለ ደገፋቸው ፣ ዕድሜያቸው ተቀናንሶና ጠባያቸው ተኳኩሎ ገና ለብዙ ጊዜ የሚያ ገለግል ተፈላጊ ሹም አድርጓቸዋል ።

የሳቸው ደህንነትና ተስፋ በወዳጅና በውለታ ከፋዮች ሲጠበ ቅና ሲከበር ፣ እሳቸውም በበኩላቸው የደጋፊዎቻቸውንና የአይዞህ ባዮቻቸውን ደህንነትና ጥቅም ሥራዬ ብለው ይከታተላሉ ። ቢሆንም ፣ ላላከኩላቸው አያኩም ፣ ሳልጋገሩላቸው አያንጉቱም ። በዙሪያቸውና ከበ ላያቸው ያሉት ሰዎች ኑሮ ተዋቅሮ የተጨመጨመው ፣ በአማግረኝ ላማግርህ ፣ በአካድነኝ ላካድንህ ፣ እንካ — በንካ ስልት በመሆኑ ቾል ታና ዝንጋታ የኑሮ መዕድን ያናጋሉ ። አፋቸው ለጉርሻ ፣ እጃቸው ለእጅ መንሻ የተከፈተና የተዘረጋ በመሆኑ ፣ ከዘንጉ መነጠቅ ፣ ችላ ካሉ መጨፍለቅ ስላለ ፣ የሁሉም የጋራ ምሳሌ ‘የዘነጋ ተወጋ’ ወይም ‘ፍት ፍቱን እይተህ ተጎራረስ’ ነው ።

አቶ ወርቅነህ ደመቀ ከተላላኪነት ወደ ተራ ጸሐፊነት ፣ ከዚ ያም ደረጃ በደረጃ ወደ ፪ኛ መዝገብ ቤት ዲሬክተርነት የደረሱት ፣ በሥራና በአገልግሎት ብቻ ሳይሆን ፣ ለአለቆቻቸው በሚያደርጉትና በሚያሳዩት ከፍ ያለ ሽር —ጉድና የተትረፈረፈ ትሕትና ሲሆን ፣ በተጨማሪም በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች እንደ ጠቃሚያቸው ሰው ፍላጐትና ሁኔታ ለተለያዩ አለቆቻቸው በሚያቀርቡት ገጸ —በረከ ትና ‘ይኸ ምስጢር ነው’ በማለት በሚያደርሱት ወሬ ጭምር ነበር ። በዚህም ምክንያት ከአያሌ ዓመታት ጀምሮ ጠባያቸውን አሳምረው የሚያውቁ የቅርብ የሥራ ባልደረቦቻቸው ፣ “ወርቅነህ መዘውር” በማለት ቅጥያ አወጡላቸው ።

ሕይወታቸው በተላላኪነት ሥራ ወዲያ — ወዲህ ካለችበት ጊዜ ጀምሮ በሠሩበት ቦታ ሁሉ ፣ አንዱ ባንዱ ላይ ተንጠላጥሎና ተሻግሮ ፣ ተጐትቶና ስቦ እንደሚኖር በማየታቸው ቋሚ ጠባያቸውን ዐውቆ ፣ እምነትና ጽናታቸውን ገምግሞ ለመተንበይ የሚያዳግት ባሕሪ አላቸው ። ካለ ነገራቸው ግን ፣ ተናግረው ሰው አያስቀይሙም ። ልባቸው ከፈቀደና እጃቸው ከተዘረጋ ፣ ለጋስና ቂም — ነገረኛ ሲሆኑ ፣ ቂም ይዘው በክፉ ዐይናቸው ካዩ ደግሞ ፣ የጥቃት ጦራቸውን አድፍጠው ይወረውራሉ ።

በሥራቸውና በጠጋ — ጠጋቸው ምክንያት የተነሣ ለም ከጠፍ የመንግሥት መሬት ያለበትን ፣ ሹመት የሚገኝበትንና የታጨለትን ፣ የደመወዝ ዕድገት የሚሰጥበትን ፣ የየትኛው ክፍል ባለሥልጣን በምን ዓይነት ጉዳይ እንደሚያግዝ በመንገርና በማማከር እንደምንም ጠቅሞ መጠቀም ልማዳቸው ነው ። ወ/ሮ ደጅ ይጥኑ አዲስ አበባ በገቡ ሰሞን ፣ "እይዞሽ! የምትፈልጊውን ነገር ንገሪኝ ፣ ከሰው እንሶ መታየት አልወድም ፣ እ!" በማለት አኩራሯቸው ። ቀድሞውንም ዝናና አይዞሽ ባይ ወዳድ የነበሩት ሴትዮ ምኞታቸው ተሳክቶ ፣ በቀኛዝማችም ሆነ በሌሎች ወሬ ቃራሚዎች ፊት የሚያስከብሩና 'እኔ አለሁ' የሚሉ ዘመድ በማግኘታቸው ፣ ልባቸው በኩራትና በተስፋ ተለጠጠ ።

ላቀችም ገና ከማጀቴ ሳይነሡ እንደ ተነገራት አቶ ወርቅነህ ደመቀ ቤት ተልካ በገባች ቁጥር ፣ ካፏ ቀጠብ ፣ ካቀማመጧ ሰብሰብ ፣ ካንገቷ ሰበር ማለትንና የሚበላም ይሁን የሚጠጣ ሲሰጣት ፣ ካንገት በላይ መግደርደርን ሥራዬ ብላ ተያያዘችው ። ካደገችበት የገጠር ልማድ በባሰ ሁኔታ ፣ "እንዲህ እያልሽ ነው መናገር ፣ እንዲህ እያደረግሽ ነው መሥራት" እየተባለች በተደጋጋሚ በመነገሯ 'እሺ' እንጂ 'እምቢ' የሚል ቃል ከአንደበቷ የጠፋ መሰለ ። የኩተቱ ዓይነትም በዛባት ። የምታየው ዕቃ ሁሉ ሲነኩት የሚሰበር ፣ ሰው ሁሉ ቅን የማይናገር እየመሰላት ፣ ዕቃውን ሁሉ የምታነሣው በጥንቃቄ ፣ ሰውን ሁሉ የምታናግረው በፍርሃት ሆነ ። በጣም ያስደነቃት ዕቃ ግን ፣ ግድግዳው ላይ ረዥም ጥቁር የገመድ ጅራቱን ሾጉጦ ፣ ክብ ጠረጴዛ ላይ ማዕዘኑ ጥግ የተቀመጠው አነስተኛ ሳጥን መሰል ነገር ነበር ።

ጧት — ጧት ቡና ሲጠጣና ከምሳ በኋላ የአቶ ወርቅነህ ልጅ ነካ ስታደርገው ፣ እንደ ሰው ያወራራና በመኻሉ ደግሞ ዘፈኑን ያስነካዋል ። ማታም እንዲሁ ። ወ/ሮ ደጅ ይጥኑ ወጣ ሲሉላት ያንን ለፍላፊና ዘፋኝ ሳጥን ከወደ ቂጧ ሸሸት ፣ ከወደ ደረትና ራሷ ወደ ፊት ሰገግ ብላ ትመለከትና ፣ "እምኑ ጋ ይሆኑ ሰዎቹ?" ትላለች ።



አንድ ቀን ከወ/ሮ ደጅ ይጥኑ ጋር ብቻቸውን ሲያወሩ ፣ "እቴዋ ፣ ይኽ ነገርዮ ምንድነው እልኋለሁ እያልኩ" አለች እያፈረች ።

"የቱ?" አሉ አካባቢውን እየቃኙ ።

"ያ እጠረንቤዛው ላይ ሆኖ እሚዘፍነው" አለች በጣቷ እያሳየች ።

"ያ ጠረንቤዛው ላይ ያለው?" አሉ እየሣቁ ።

"አዎድ!" አለች ስለተሣቀባት አፍራ ።

"ነካካሽው እንዴ?" አሉ ኮስተር ብለው ።

"ኧረ ምን ቅብጥ አርጎኝ"

"አዎ ፡ የማታኢውን ነገር አትንኪ ፡ ረዲዎን ነው ።"

"እቴዋ? ዐፈር ስሆን አትሳኡብኝና እሚናገሩትና እሚዘፍኑት እምኑ ጋ ሆነው ነው?"

"ፈረንጅ እማይጠብበው ምናለ? እኔስ የት ዐውቄው ብለሽኝ" ብለው ስለ መለሱላት ፣ እሳቸውም እንደሷ ባለማወቃቸው "ኧረግ! ለካ የኔው ቢጤ ናቸውና" ብላ በልቧ ተደሰተች ።

ወ/ሮ ደጅ ይጥኑ ፣ ብዙ ጊዜ የተመኙትን ወርዳምና ቁመታም የቁም — ሳጥን መስታወት በማግኘታቸው ፣ ጀርባቸውን ወደ መስታወቱ አዙረው የአካላቸውን ቅርፅና አቀማመጥ አንገታቸውን እስኪያማቸው ተጠምዘው በተደጋጋሚ ያዩታል ። የተለያዩ የገጠር ቅድ ቀሚሶቻቸውን በመቀያየርም በየትኛው ወፍራም ፣ በየትኛው ደግሞ ልከኛ መስለው እንደሚታዩ ለማወቅ ዐሥሬዎ እያወለቁና እያጠለቁ ይመለከታሉ ።

ከአቶ ወርቅነህ ሚስት ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን በሔዱባቸው ቀናትም በአለባበስና በአረማመድ ፣ እንዲሁም ከወደ ቂጥና ዳሌአቸው ከሳቸው የሚበልጡና የተኩነሰነሱ ፣ አጣጣልና እርግፍጋፌውን የሚያሳምሩት አያሌ ሴቶች በማየታቸው በተበለጥኩ ስሜት ቀኑ ። "ሆሆይ! ለካ በያገሩና በየቤቱ ስንት መልከ መልካም አለ እናንተ ሆዬ!" እስከ ማለት ደረሱ ። ቀኛዝማች እንደሚወዷቸው ቢያውቁም ፣ የእንዲህ ዓይነቶቹን ሴቶች ቁመና በተደጋጋሚ ሲያዩ ልባቸው ይሸፍት ይሆናል በማለት ጠረጠሩ ።

ላቀች ሴትዮዋ ወጣ ባሉላት ቁጥር ፣ መስተዋቱ ፊት ትተካለች ። ቀጠን ፣ ለዘግ ያለው ቁመቷና አቀማመጠ መልካሙ የአካላቷ ቅርፅ ደስ ስለሚላት ፣ ቤቱ መስተዋት ብቻ ቢሆን ምኞቷ ነበር ።

*        *        *

ቀኛዝማች ፣ እሑድ ረፋዱ ላይ ወ/ሮ ደጅ ይጥኑን ሊጠይቁ በሔዱ ጊዜ አቶ ወርቅነህ ጥሩ አቀባበልና የመስተንግዶ ግብዣ አደረጉላቸው ። ከጥቂት ጭውውት በኋላ ቀኛዝማችና ሴትዮዋ ወደ ማረፊያቸው ሔዱ ። ተነፋፍቀዋል ።መኝታ ቤት ውስጥ ገብተው በመጀመሪያ ስለየራሳቸው ፣ ከዚያም በምንዳዬ ላይ ስለ ደረሰው አደጋ ባጭሩ አወሩ ። ሮውዬው አፋቸው እያወራ ፣ እጃቸው ይዳብሳል ። የሴትዬዋን ጣቶች ፣ ክንድ ፣ ጠፍጠፍ ብሎ አሮጌው ሶፋ ላይ የተጋደመውን ጭን እያሻሹ ፣ ስሜታቸውን ቀሰቀሱት ። ሴትዬዋም ነዝሯቸው ውስጣቸው ወከክ አለ ። ወዲያው የመኝታ ቤቱን በር በዝግታ መለስ አድርገው አንጀታቸውን አራሱ ። ረዘም ካለ ሰመመናም ቆይታ በኋላ በረድረድ ባለስሜት ወሬ ጀመሩ ።

“እንዲያው ያጨካከንሁ ነገር —” አሉ ሴትዮዋ ።

“ምን አጠፋሁ? ያጠፋሁት ነገር አለ እንዴ?” አሉ ውስጥ—ውስጡን እየዳበሱ ።

“መሔጃዋ ደርሷልና እንዴት ሆና ይሆን ብለሁ ብቅ አለማለትሁ።”

“የሞላለት ሰው ደስ ማለቱ እናንተ ሆዬ?! አዲስ አበባ ስመጣ እኮ የገጠር ንብረቴን በታትኜ አይደለም ። አደራ ብዬ ነው ። ምንዳዬስ በማን ሰበብ የቆሰለ መሰለሽ? አንቺው ጋ ተልኮ ሲመጣ እኮ ነበር — —ቢሞትስ ኖሮ ፣ ምንድን ነው የሰው ውለታ ማጥፋት — ”

“የእሱንማ ሰምቼ አዘንኩ ፣ የከዚያ በፊቱን ማለቴ ነውዬ!”

“ከዚያ በፊትማ ይኸን በዚህ አርጉት ፣ ይኸን በዚህ አርጉት ስል — —”

“ኡኡቴ! — —ማ አባቱ እንዳይነካው ፣ ያደራው ጋጋታ ደሞ ምን እንዳይመጣ ነው ?”

“ቢሆንም ፣ እንኳን ከዘመድና ከባዳ ፣ ከገዛ ልጆችሽም መኻል ታማኝ ታማኙን ትመርጫለሽ ።ሁሉም እኩል አደራ አይባልም ፣ ስንት አላቴና ስንት ቀስፋታ አለ መሰለሽ?”

“እኔንስ ከማን እኩል ታማኑኛለሁ?” አሉ እየሣቁ ።

“እንዴት ከማን እኩል?” አሉ ግራ ገብቷቸው ።

“እንደኔ ምንዳዬ ነውው — —”



“ይኸውላችሁ ስታሽቆለቁል! አንቺ ይኸን ይኸን ምን አጠያየቀሽ ? ይገርማል እኮ! ‘ብርንዶ ይዞ ሣምባ ቅልወጣ’ አሉ መምሬ ተክለ ጊዮርጊስ ። እኔን ዋናውን ይዘሽ አደራ ጋ ምን ወሰደሽ?! ምን እንደምል ለመስማት ነው?” ብለው ሣቁ ።

ሴትዮዋ ለአንድ ቀን ዝናና ጉራ ያህል እንኳ እንዲያድሩላቸው ቢፈልጉም ፣ ወንድዬው ከባለቤታቸው ጋር አዲስ ንዝንዝ ላለመጀመር ስሜታቸውን ኮርኩመውና ነገር ፈርተው ወደ ቤታቸው ሔዱ ።

## ምዕራፍ ሐያ ሦስት

ምንዳዬ ፥ የቆሰለ ግራ ክንዱን አንገቱ ላይ ባጠለቀው የነጠላ ትልታይ ደግፎ እንጀራ ሲበላ ፥ ልኬለሽ አልጋው ጠርዝ ላይ ተቀምጣ አበላሉን እያየች ታጕርሰዋለች ።

"ብዬ እንጂ ልኬ ? አለያ እኔ መተዬ ነው ።"

"እየበላሁ አደል ! እኔ እኮ ስሠራም ኀረስረስ እያረኩ ነበር —"

"ደሞ የት ሆነሽ ነው የበላሽው? ሌላ የመብሊያ ሥርፋ ያለሽ ይመስል ?"

"እኔ ልሙት ! አላየኸኝሚ ስበላ ነበር ፥ አንተ በሽታ በሽታህን ስታዳምጥ" ብላ ልከኛ ጉርሻ ጠቅልላ እጅዋን ወደ ምንዳዬ ዘረጋች ።

"ቦጋለ ይሙት ፥ በቃኝ ጠግቢያለሁ" ብሎ ወደጎን ዞረ ። ወዲያው ፊቱን መለስ ከማድረጉ ፥

"ቢል ይኸው ስለማላህ ቀምሼልሃለሁ" ብላ ከጉርሻዋ አናት ላይ በፊት ጥርሶቿ በጥቃ ቀምሳ ፡ አፉ ሥር ደቀነችለት ። ፈገግ ብሎ ስለ ኀረሰ ደስ አላት ። እንደገና በእምቢታ የማያስመልስ ስም ስታስ ላስል ፥ የገዛ ስሚን አገኘች ።

"ዳግመኛ አልመጣብህም ፥ ይቺን ብቻ በልክዬ ሞት" ብላ ፋታ ሳትሰጥ አጎረሰችው ።

"አይ አንቺ ፡ እስካሁን የት ተደብቀሽ ነበር" ብሎ ሣቀ ።

ልኬለሽ የሞከከ —የሞከከውን ሥጋ እየመረጠች ስትሰጠውና ለራሷም ስትበላ ቆይታ ፥

"ይቺን ብቻ ዐፈር ስሆን?" አለችው አዘናግታ ።

"አሁንስ አበዛሽው!" ብሎ ካንገት በላይ ሲቆጣ ፥

"እኔ በውሃ እበቅላለሁ እንዴ?" ስላለችው እየሣቀ ጎረሰላት ። እሱም ብድሩን መለስ ። መሩጹ ሊነሣ ሲል "ልኬ!" አለ አንድ ሰው ከውጪ ።

"አቤት!" አለች ወደ በሩ እያየች ።

"ደህና ዋላችሁ ወይ ? እንዴ ዋላችሁ ?" ብሎ ገባና "በርትተህ ዋልክ ወይ ምንዳ? አንቺስ በጎ ዋልሽይ?" አለ ወደ ውስጥ እየዘለቀ ።

"ደህና ነን ፡ አንተስ በደህና ውለሃል ቸርነት?"አለች ለራሷ ይሁን ለምንዳ ያልለየለት ጉርሻ ይዛ ።

"ደህና ውለሃል ? — —ና ወዲህ ፡ ና ጠጋ በል!" አለ ምንዳዬ ።

"አሁን ገና ከሱው ላይ መነሣቴ ነው" አለ ወደ መደቡ እየሔደ ።

"አንተ ደሞ ! — ና ዐፈር ስሆን! ና !" አለችው ልኬለሽ ።

"እኮ ና!" ሲል ምንዳዬ ፡ ልኬለሽ ቸርነትን ጐትታ አልጋው አጠገብ ግርንቡድ ላይ ካስቀመጠችው በኋላ ፡ ያቀረበችለትን ምግብ እየበላ ሲያወሩ ፡ ምንዳዬ አንድ ነገር ትዝ ብሎት ፡

"በመጣህ ቁጥር እርስት አረገዋለሁ ፡ ያን የጀመርክልኝን እኮ አልጨረስክልኝም ቸሬ ?"

"የቱን?"

"ምነው ያነዬ ጀመር እንዳረክልኝ ሴትየዋ ደረስ ሲሉብን የተውከውሳ!"

"እ ! —ተወው ትዝ አለኝ! ያቺ መናጢ ስትመጣ የተውነውን ወሬ ማለትህ ነው? እሱን ተወውና ሌላ ወሬ አወራሃለሁ ። እሱ ተወርቶ — ተወርቶ በእቶታል" አለ ወሬ ለማስቀየር ።

"አንተ ደሞ ያልኩህን ትተህ ያላኩህን — —እየረሳሁት ነውዬ ሆድ —ሆዴን ነው የበላኝ ።"

"ምን ፋይዳ አለው ብለህ ነው — ከሆነም ሌላ ቀን እጫውትሃለሁ — —ስታገግም ።"

"'የማያስለቅስ ይነግሩህና ሲጣጣቁ ያድራሉ አሉ' እኛ አባቶቹ ። ምን እንዳልሆን ብለህ ነው ። እኔ እንደሁ ቀን ከጐደለብኝ ቆይቻለሁ ። ለምን ትደብቀኛለህ — —አዬ ቸርነት! ለካ አንተም—" ብሎ ሳይጨርስ ፡

"ምኑ እንዳይቀርብህ ብዬ ነዋ — ብትሰማ ጠልቼ መሰለህ?"

"ምንም ይሁን ምን ልስማው ፡ ምን እንዳላረግ ብለህ ነው! አይ



ቸርነት ፣ 'ቢያሟሙኝ አሞሌ ፣ ቢሰብሩኝ ብርሌ' ነው እሚባለው —" ብሎ ሐሳቡን ሳይጨርስ ፣

"ምን አርግ ነው እሚልህ ልጄ?" አለች ልኬለሽ ጉልቻ እያስተካከለችና ረመጥ በስንጥር እያስጠጋች ።

"አፍ አድጠኝ አንድ ወሬ ብልጭ አርጌለት ነበር ።ይኸው ካልነገርከኝ ብሎ ይጨቀጭቀኛል" አለ እንድታግዘው ፈልጎ ። ነገሩ ገባት ።ቸርነት የተጨነቀበትን ወሬ ፣ ከነጭምርማሪ አሉባልታው በአረጋሽ በኩል አንድ —ባንድ ሰምታዋለች ። የተወራውንና ተደረገ የተባለውን ሁሉ ቢሰማ ክፉኛ እንደሚናደድና ፣ በበሽታው ላይ ተጨማሪ በሽታ እንደሚሆንበት ስለ ታወቃት ፣ የሰማችውን ሁሉ ጠጣና ታግሣ 'የሱ አተራረፍ ደሞ ምኑ ይነጣል ። እስተዚያው ማውራትም አያሻ ፣ አንድ ነገር ቢሆንብኝ ምን አባቴ ይውጠኛል ፣ ነገንም ነው ማየት' ብላ ከነቁጭቷ ዝም ብላ ነበር ።

ቸርነት እጁን አፋትቶ ከገበታው እግር ላይ ሲጠራርግ ፣ መዓዱን አሥንታ አስታጠበችው ።

"አሁን ልቤን ባታወልቀው ምን ቸገረህ?"

"አንትስ ነግረሽኝ ብትገላገል ምን አለበት — ደሞ ሳገልግል ይህን ያክል — —" ብሎ ጋደም አለ ። ልኬለሽ ልቧ ተሸበረ ። 'አሄሄ! —ነገር መጣ!' አለ ቸርነት በልቡ ።

አውጥቶና አውርዶ አንድ ጥሩ ብልሃት በማግኘቱ ደስ አለው ። "መንገሩንስ እነግርሃለሁ ፣ግን ትምልልኝ እንደሁ ነው" አለው ሲፈራ ሲቸር ።

"እንዴ! እንዴነው ማላው ይኸ ነገር! ስለምን ነው መማሌ? ለሰው እንዳላወራ ነው ፣ወይስ ነገሩ ፣ ነገር አለበት?" አለ በመጠራጠርም በመገረምም እየሣቀ ።

"አደለም! እሱንማ ለማን ትነግረዋለህ ፣ እኔንም ልኬንም ደስ እንዲለን ብዬ ነው ። እሷንም ቢሆን አንጀቷ ገብቶ ያንጠበጥባታል" ብሎ ሳይታወቀው ሐሳቡን አጉልቶ ለቀቀው ።

"አይ ያንተ ነገር ፣ ደሞ ዛሬስ ብለህ ብለህ ለወሬ ታስምለኝ — እኔ ደሞ አልተው ፣ ስውነቴ ነግሮኛል — —በል በማን ልማልልህ?"

ልኬለሽ ድንገት"አሻጋሪ ይሙት ብለህ ማልለት" ብላ ጣልቃ ገባች ።

"የማነው አሻጋሪ? እሱ የተገኘው ትላንትና ፣ ይህን ያክል እሚያስጨንእችሁ ተሆነ ለምን ባንቺ በዋናይቱ አልምልለትም!?" አለ በድንገት ነገሩ አንጉቶት ።

"ይኸማ ጥሩ! እኔም ብሆን ደስ ይለኛል" አለ ቸርነት እየፈገገ ።
"እንግዲያውማ ይኸው፣ ልኬለሽ ትሙት !" ብሎ ማለ ።
ቸርነትና ልኬለሽ ትክዝ ብለው ተያዩ ።

ስለ አገልግሉ ገንዳ ውሃ መገኘትና ስለእነ አረጋሽ መጠየቅ እንዲሁም አፈሣ እንዴት ተውሶ እንደ ወሰደው ጭምር ያየና የሰማውን ነገረው ።

"ለዚች ኖሯል ያን ያክል የተጨነከው?"

"አይ አንተ! ምነው እኔን ሆንህ ባየኸው?"

"እኔ'ኮ ለምጀዋለሁ ። አልሆን ቦታ ጠብቆው ሲተኩሱብኝ ስንቱን ጠርጥሬአለሁ ። ዞን —አምባ እያለሁ ፣ ታንደዜም ሁለተዜ ፈጣሪ አምላኽ ከልሎኛል ። ስንትና ስንት ነገርም አጫውቸሃለሁ ። አንተ ብቻ ተንኮል አታስብ ፣ በሰው ላይ ነገር አትሥራ ። አንድ አምላኽ የሰጠህን ማንም አይነካብህ ። ብቻህንም ብትሆን እውነት እውነቱን ከሠራህ ፣ ደመኛህ ሁሉ እግርህ ሥር ይለሸለሻል ። ጥላህ የሚቀለውና በጠላትህ እጅ እምትወድቀው ዙልመኛ ስትሆንና የሰው ሐቅ ስትሻ ነው ። ዋ! የምር አይምሰልህ ፣ እንዲህ ኮነን እንቀር! ይቺ ቀን ታልፋለች!" ብሎ ራሱን ነቀነቀና ከንፈሩን ነከሰ ።

"ምነው ሙች ብለህ?! ምነው አልናደድም ስትል ምንዳ?" አለች ልኬለሽ እንባዋ እየመጣ ።

"አልተናደድኩም ልኬ ። ሞኝ የለቱን ፣ ብልህ ያመቱን ነው ። ብናደድስ ምን እንዳላመጣ? እሰው አገር ተቀምጨ ፣ የሰው መሬት እያረስኩ ፣ ብቆጣና ብናደድ ማንን ልጎዳ ነው ? ሽዋርካብሽም ቢሆን አድርጊ ያላሏትን አታረግ ፣ ትዋል —ትደሪ ይቺ ነገር ተደብአ አትቀር ! ያን ሽንታም አሞተቢስ ግን ፣ ሱሪውን በጭንቅላቱ ባላስ ወልቀው እኔ ምንዳ አይደለሁም ! ምን ያረጋል ፣ 'የዘነጋ ተወጋ' አሉ! በሉ እንዳትሆኑ — ምየላችሁ የለ? እኔም አልሰማሁ ፣ እናንተም አልነገራችሁኝ" ብሎ ጋቢውን አጣፍቶ ካልጋው ላይ ወረደና መደብ ላይ ተቀመጠ ።

"አሄሄ! ይቺ ሁላ ዘዴ ነች ። እኔ ያንተን ልብ አጣኋትና ነው ። ሆደሰፊ ነህ ብዬ አፌን ስቀድ የነገርኩህ እንድትበሳጭ አልነበረም ። እንዲህ መሆንህን ባውቅማ — —" እንዳለ ፣

"ምነው ቸርነት? ምነው? — ምነው እንዲህ ማለትህ? እኔስ እንደማደብኸኝ መች አጣሁት ። ቢቆጭህና ቢከነክንህማ ነው የነገርኩኝ ። አሁንም ቢሆን አልተበሳጨሁም ። ቸርነት ሙት! አልተናደድኩም!" አለው ። ፊቱ ግን እንደ ቀጨመ ነበር ።



## ምዕራፍ ሐያ አራት

ቀኛዝማች በላይነህ ታፈሰ ፣ ጥቅምት ወር አጋማሽ ላይ አዲስ አበባ ከደረሱ ጀምሮ ስለ ሕግ መምሪያና መወሰኛ ምክር ቤቶች አሠራርና ስለ መምሪያው ፕሬዚዳንትና ስለ ዐቃቤ ጉባኤው ሥልጣን ፣ የሚገልጸውን ውስጠ ደንብ ጨርሰው የ1957ቱን ዜና ፓርላማ ሲያነቡ ፤

"የተሻሻለውን ሕገ መንግሥት ካወጅንበት ከ1947 ዓ.ም. ጀምሮ ዛሬ ስምንተኛውን የፓርላማችንን ዓመታዊ ስብሰባ መክፈታችን ነው" በማለት ጀምሮ ፣

"ዘላቂ የመሻሻል እርምጃ ሊገኝ የሚቻለው ጥልቅና ቀዋሚ የሆነ መሠረት ሲኖረው ብቻ መሆኑን ማስጠንቀቅ ይገባል ። እንደዚህ ያለውም ቀዋሚና ጥልቅ መሠረት ያገሪቱን ኢኮኖሚ የሚያዳብርና የሚያጠናክር ፣ ለሕዝቡም የተሻሻለ ሙልካም ኑሮ የሚያስገኝለት የተስፋፋ ፕሮግራም ሲኖረውና በየዕለቱም የሚያጋጥሙንን ችግርና መሰናክል ለማስወገድ የሚያስችለን ዘመናዊ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዕውቀት እንዲሠራበትና የሕዝባችን የኑሮ ሁኔታ እንዲሻሻል ለማድረግ ሲሆን ነው" የሚለውን ሐተታ ሲያነቡ የሐሳቡ ይዘት ግራ ገባቸው ።

ቢሆንም ቀጠሉ ። "እናንተ የፓርላማ አባሎችና እያንዳንዱም ኢትዮጵያዊ ሁሉ ማናቸውንም ጉዳይ ብሩህና አስተዋይ በሆነ አእምሮ ለመመልከትና ለመመርመር ፣ የራሳችሁንም ሆነ የጓደኞቻችሁን ተግባር በማሻሻል ፍላጐት እንጂ ፣ በጥፋት መንፈስ ለመተቸትና ለመንቀፍ አትሞክሩ" ከሚለው በታች አያሌ አንቀጾች አንብበው ፣ "በመሬት ይዞታ መሻሻል ረገድ የሚደረገው ጥናት" የሚለውን አንቀጽ ሲጀምሩ ፣ ዐይናቸው ፈጠጥ ፣ ሁለመናቸው ነቃ ማለት ጀመረ ። "በልማድ የቆየውን አሠራር በመለወጥ የተሻሻለ ውጤት የሚገኝበትን ዘመናዊ ዘዴ ለመመሥረት በመሆኑ ፣ የጥናቱ ሥራ እጅግ ከባድና መሠረት ያለውም መሆኑ ግልጥ ነው ። ለዚህም ተግባር አደራ የተጣለባቸው የመንግሥታችን ሠራተኞች ያለማቋረጥ በመሥራት ሥራቸውን በሁለት ደረጃ ከፍለው በመዠመሪያ ደረጃ እንዲፈጸም ካቀረቡት ውስጥ የርስተ ጉልት ግብር አከፋፈል ማሻሻያ ዐዋጅ

ቀርቦላችሁ መክራችሁበታል ። በፍትሐ—ብሔር ለወጣው የሰብል
አከፋፈል ሕግ ማሻሻያ የሆነው የጭሰኛና የባለ መሬት ግን
ኙነትና የሰብል ክፍያ ሕግ እንድትመክሩበት ቀርቦላችሁ እናንተው
ዘንድ ይገኛል ። በሚቀጥለው ደረጃ የሚወሰደውም ርምጃ ጥናቱ ተጠ
ናቆ ወደፊት ይቀርብላችኋል ። ባለርስት የሚገብረው ለማነው? ለራሱ ፣
ለባለቤቱ ፣ ለልጁ ፣ ለአገሩ ነው ። ባለርስት በትጋት መሥራት አለ
በት" የሚለውን እንዳነበቡ መንፈሳቸው ረክቶ ፊታቸው ፈካ ። ከዚያ
ቀጥሎ የነበረውን ጽሑፍ ደስ ብሏቸው ቢያነቡትም አልገባቸውም ።

ቀኛዝማች ፣ እጅግ በጣም የጓጉለትና በሕይወታቸው ዘመን
እንደ መጀመሪያ ታላቅ ዕለት የቆጠሩት ኅዳር 3 ቀን አራት ሰዓት
ተኩል ላይ ቢቃለ—መሐላ ተጀመረ ። ከዚያም ልክ እኩለ ቀን ላይ
ታላቁ ቤተመንግሥት ውስጥ ከ3ኛ ጊዜ ተመራጮች ጋር ንጉሡ ዘንድ
ቀርበው እጅ ሲነሡ በተሰማቸው ኩራትና ራሳቸውም ጨማምረውና
አሰማምረው በፈጠሩት አድናቆት ተደስተው ዋሉ ። ደስታቸውን ሳይ
ጨርሱና ጋዜጣውን አንብበው ሳይጠግቡት ኅዳር 7 ቀን ደረሰ ።

አዲስ አበባ ከታላቁ ቤተ መንግሥት በስተሰሜን አራት ኪሎ
ሠፈር የሚገኘው የኢትዮጵያ ምክር ቤት ሕንፃ ፣ የሰዓት ደወል
ቤቱን እንደ ወፍራም ምርኩዝ እጐኑ ተክሎ እንደ ወርዳም
ትልቅ ቁምሳጥን ተጋድሟል ። ከልዩ ልዩ አቅጣጫ የሚጐርፈው የከ
ተማው ሕዝብ ከምክር ቤቱ በስተ ደቡብ ካለው ሕገ—መንግሥት
አደባባይ እና በስተምዕራቡ ካለው መንታ ጐዳና ላይ ፣ እንደ ጥምቀተ
ባሕር ይተራመሰበታል ። ከምክር ቤቱ ውጪ ባሉት መንገዶች ላይ ፣
መሣሪያ ያነገቱ ወታደሮችና ተዘዋዋሪ ፖሊሶች ፣ በቁጣና በለዘብታ ፣
በግልምጫና በፈገግታ ሕዝቡ የመንገዱን ዳርና ዳር ይዞ እንዲ
ቆምና እንዲሔድ ወይም በያለበት ሥርዓት እንዲጠብቅ እያዘዙ
ያስተናብሩታል ። ሽማግሌና ባልቴት ፣ ጐረምሳና ኮረዳ ፣ ልጆችና
ጐልማሶች ይሰበሰባሉ ። ልዩ ልዩ ከረሜላ ፣ የሸንኮራ—አገዳ ፣ የአረን
ቻታና ሌላ ሌላ — — ነጋዴዎችና ሱቅ በደረቴዎች በሕዝቡ መኻል
እየተዘዋወሩ ይነግዳሉ ። አንዳንድ ሰዎች በዳንቴል ከርና በባለ አበባ
ጨርቅ የተሸፈኑ ትራንዚስተር ሬዲዮኖች አንግተውና አንጠልጥለው
የዕለቱን የፓርላማ መክፈቻ ንግግር ከማጉሊያና ከሬዲዮናቸው ለማ
ዳመጥ ቀዳሚ ሐተታውን ይከታተላሉ ። ትርምሱ እየበዛና ግፊያው
እያየለ ወደ መንገዱ ዳር ሲጠጋ ወታደሮቹ በቁጣም ፣ በዱላም ይከ
ላከላሉ ። ከወዲያ —ወዲህ የሚዘዋወሩት ፈረሰኛ ፖሊሶች ሕዝቡን
በፈረስ ኮቴና ዱላ እያስፈራሩ ከመንገዱ ገለል ያደርጉታል ።

ከምክር ቤቱ ሕንፃ ዋና ደቡባዊ በር አናት ላይ ፣ ሰማዕቱ ቅዱስ
ጊዮርጊስና ከግራ— ቀኙ ደግሞ ዘውድ ጭነው አንዱ በግራ ፣ ሌላው



በቀኝ ባንዳንድ የፊት እግራቸው የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ የያዙ
አናብስት ሥዕል አለ ።

በዚያው ትይዩ ከግዙፉ ባለሁለት ተካፋች የብረት በር ግራና—
ቀኝ ባራት ማዕዘን ቅርፅ የጥርብ ድንጋይ ዓምድ አናት ላይ ፊታቸውን
ወደ ምሥራቅና ምዕራብ አዙረው የተገለጠ መጽሐፍ የያዙ የሁለት
ባለክንፍ አናብስት ሐውልት ይገኛል ። ከግርጌአቸው በጠባብ መቆሚያ
ውስጥ ቁመተ መለሎና አቋቋመ መልካም ፣ ትጥቀ ሽንቅጥ ቆፍጣና
ወታደሮች ይቆማሉ ።

ኅዳር 7 ቀን 1958 ዓ.ም. አራት ሰዓት ተኩል ላይ የኢትዮጵያ
ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የሕግ መምሪያ ምክር ቤት የ3ኛ ጊዜ ተመ
ራጭ እንደራሴዎች የሥራ ጊዜ መጀመሪያና ንጉሡ ሁለቱን ምክር
ቤቶች በዙፋን ንግግር የሚከፍቱበት ዕለት በመሆኑ ፣ ከንጉሡ የኃ
ላፊነት ሥልጣን የተሰጣቸውና ከፍተኛ የመተዳደሪያ ንብረት ያላ
ቸው ፣ ሐረግ መዘውና ያጥንት ስንጣሪ ፈልገው የተሰባሰቡ ፣ የኃይል
አደራ የተቀበሉ ሁሉ በምድረ ግቢው ውስጥ በማዕረግና በሥልጣን
ተዋረዳቸው መሠረት በውስጣዊ የቅናት መንፈስና ፉክክር ሽብ—
ረብ ይላሉ ። በሰልፈኛውና በተመልካቹ ሕዝብ መካከል በተለያዩ
የአለባበስ ሁናቴና የኑሮ ደረጃ አቀራረብ እንደ ጥሬ የተዘሩት
ነጭ ለባሾች ደግሞ አምተው እያናገሩ ፣ አሽሟጠው እያሳደቡ ፣ ወሽ
ክተው እየነካኩ ፣ ወይም አሞግሰው እያስሞገሱ ፣ እንደ ንክ—ሰው
እየተቅበዘበዙና እንደ ዔሊ እየተንቀረሰሱ ይዘዋወራሉ ። የፓር
ላማው የደርብ ሰዓት ደወል አራት ተኩል ላይ እንደ ደወለ አካባ
ቢው በእልልታና በጭብጨባ አስተጋባ ። ግፊያና ጫጫታ በዛ ።
የሁሉም ዐይን ወደ ቤተ መንግሥቱ ሰሜናዊ ዋና በርና ወደ መን
ታው ጐዳና አተኮረ ።

በግዙፍ ልጥልጥ ፈረሶች ላይ ተቀምጠው ፣ አጠር ባለ ሰንደቅ
ላይ በቢጫ ዘርፍ የተንቆጠቆጠች ሦሉስ ማዕዘን ባንዲራ የያዙ ፣
ባለ አንበሳ ጐፈር ቡሽ ባርኔጣ የደፉ ፣ ግራ ቀኝ ትከሻቸው ላይ ጐፈር
ያንዘረፈፉ ፣ ወፍራም ቢጫ ቋድ በደረትና በትከሻቸው በኩል ዐልፎ
እጐናቸው ላይ አናተ—ድብልብል ባለ—ዘርፍ ክሮች ያንዠረገጉ የክብር
ዘበኛ ፈረሰኞች ፣ አረንጓዴ ሽንጣም ውብ አቶሞቢል አጅበው በፓ
ርላማው ደቡባዊ በር በኩል እንደ ደረሱ ፣ በከፍተኛ ወታደራዊ ሥነ—
ሥርዓት የተሰለፉት ወታደሮች ረጂም የብረት ሰላምታ አቀረቡ ።

ንጉሡን ተከትለው እንዲገቡ የተፈቀደላቸው መሳፍንትና መኳ
ንንት ፣ ባለሥልጣኖችና ሽሞች ባስተናባሪዎች ቦታ ቦታቸውን ያዙ ።
ሁሉም ነገር የሚሽቆጠቆጥና የሚንሸቀሸቅ መሰለ ። ሕገ—መንግሥት

አደባባይ ከተሰበሰበው ሕዝብ መኻል ፣ ፍቅርና ጥላቻ ፣ ቂም በቀልና ውለታ ፣ ድጋፍና ጥርስ ነከሳ ፣ እርግማንና ምርቃት ፣ ብስልና ጥሬ ሐሳብ ጐን ለጐን ሲቆሙ ፣ አንዳንዱ በግልጽ ሌላው በስውር ውዴታና ጥላቻቸውን ይገልጻሉ ።

አጭር ፣ ቀጭን ፣ ፊተ እና አፍንጫ ሰልካካው ንጉሥ እጅግ ዘመናዊ የሆነ የሲቪል ልብስ እንደ ለበሱ ከአቶሞቢል ሲወርዱ የአካባቢው ሕዝብ በጭብጨባና በውካታ ድምፅ ተቀበላቸው ።

ንጉሡ ፈጠን ባለ አረማመድ በመሳፍንትና መኳንንቱ ፣ በታላላቅ የጦር —አለቆችና ባለሥልጣኖች ታጅበው ወደ ምክር ቤቱ ሲገቡ፣ በተለይ አንዳንዱ ለንጉሡ ያለውን ታማኝነትና ክብር ፣ መላ አካልና ሐሳቡን ለሳቸውና ለዙፋናቸው ደህንነትና ልዕልና የሰጠ መሆኑ እንዲታይና እንዲታወቅለት ይሯሯጣል ።

ጉባኤው አዳራሽ እንደ ደረሱ የሁለቱም ምክር ቤት አባላት ከፍ ባለ አስገምጋሚ ጭብጨባና የደስታ ስሜት ቆመው ተቀበሏቸው ። አብዛኛዎቹ የዘውዱ ሕልውና ጠባቂዎችና በዙፋኑ ዙሪያ የተማገሩ የበረከቱ ተቋዳሾች ሲሆኑ ፣ የሥዩመ እግዚአብሔርና የዘለዓለማዊነቱም መስካሪና አወዳሽ ፣ አውታርና ካስማዎች ናቸው ።

ንጉሡ ከመማክርቱ ፊት ለፊት ከፍ ካለ መድረክ ላይ ፣ መደገፊያው ረዘም ብሎ ፣ ከላይ መስቀል ባጎለለ ዘውድና ከግርጌው ሰማዕቱ ጊዮርጊስ ፣ ከግራ — ከቀኝ ሰይፍ በያዙ መላእክትና በፍትሕ ዓርማ ታጅቦ ፣ በዳዊት ኮከብ ቅርፅ ካሸበረቀው መንበረ ዙፋናቸው ላይ ሲቀመጡ ሁሉም ነገር ጸጥ — ረጭ አለ ። ንጉሡ መደብ ጠርዝ ላይ እንደሚቀመጥ ልጅ ዙፋኑ ጫፍ ላይ ሲቀመጡ በአዳራሹ ውስጥ የነበሩት ዐይኖች ሁሉ ወደሳቸው አተኮሩ ።

ቀኛዝማች በላይነህ ታፈሰ ፣ ከአድናቆታዊ ደስታ የተነሣ መላ—ቅጡ ጠፋቸው ። አንዳንድ ጊዜማ እንደ ሞኝ አፋቸውን ከፍተው ሲመለከቱ ፣ ዐይናቸው ይፈዝና እንቅልፍ የከበዳቸው ይመስሉ ነበር ። የንጉሡን የመጀመሪያ ቃል እንደ ሰሙም ፣ ወደ አንድ አዲስ ኑሮና አካባቢ እንደገቡ ታወቃቸው ።

የምክር ቤቱ መክፈቻ ንግግር ካንድ አንቀጽ ወደ ሌላ አንቀጽ በተሸጋገረ ቁጥር ከቀኛዝማች አስተሳሰብና ኑሮ ጋር ባለመገናኘቱ ፣ "ይኸ ምን ማለት ይሆን" እያሉ አንድ ቃል ወይም ሐሳብ ይዘው ሲያሰላስሉ ሌላው ያመልጣቸዋል ። በአዳዲስ ሐሳብና ፍቺው በማይገባ የቃላት ባሕር ተዘፈቁ ። ተገላገሉ ሲላቸው የግል ሐሳባቸውን ይዘው በእግረ —ሕሊና ማር አምባ ገቡ ።



"ያገሬ ሰዎች ለዚህ ታላቅ ክብር መብቃቴንና ከመላ ኢትዮጵያ ተመርጠው ከመጡ የምክር ቤት አባላት ጋር ተቀምጬ የዙፋን ንግግር ስሰማ ቢያዩኝ እንዴት ጥሩ ነበር" በማለት ብዙ ሰዎች ትዝ አሏቸው ። ወ/ሮ እልፍ ይከንዱን ሲያስታውሱ ደግሞ ፣ "ይኸንማ ብታይ ፣ ተገርማም አታባራ ፣ እምድር ዓለም ያለሁም አይመስላት ፣ ይቺን አይታ ማር አምባ ብትገባ ፣ ጃንሆይ ዘውድ ጭነውለት አየሁ ማለቷ አይቀርም ነበር" በማለት ኩራት ተሰማቸው ።

ሐሳባቸው ከማር አምባ መለስ ሲል ፣ ንጉሡ ፣ ስለ ወቅቱ የሀገራቱ የኢኮኖሚ ችግርና ትግል ፣ የተፈጥሮ ሕግና የሥራ ግዴታ ፣ የኀብረት ሥራ ድርጅቶችና የኢትዮጵያ እንግዶች ጉዳይ አንብበው ፣ ሮዴሺያ ጉዳይ ላይ ደርሰው ስለነበር ፣ ቀኛዝማች ከማያውቁት የፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ ድንገት በመደንቀራቸው ፣ ስማ—በለው የሚያሻው ሰው መሰለው ተጎለቱ ። ደግነቱ የዕለቱ የፓርላማ መክፈቻ ንባብ በአጭር የምክር ቃላት በመጠቃለሉ ፣ 'እንዲህ እንዲህ ያለውን ቀላል ቀላሉን ቢናገሩ ምንነበረበት?' አሉ በልባቸው ። ያውም እየፈሩ ።

እያንዳንዱ የምክር ቤት አባል በስሜቱ ንረት መጠን እየተቁነጠነጠ ጭብጨባውን አቀለጠው ። አንዳንድ አባላት ግን የተደረገውን ንግግር ፣ "ምንም ዓይነት መሻሻል እኮ የለም ። ሀገር በዙፋን ዲስኩርና በተቀናበረ የቃላት ክምር አትቀና ። የትግል ጊዜ ፣ የተፈጥሮ ሕግና የሥራ ግዴታ እያሉ ቢወተውቱት ምን ያረጋል ፣ እዚህ የተሰበሰበው ሁሉ የሚግጥ እንጂ የሚሠራ አይደል" በማለት የተደረገውን ንግግር በየልባቸው ነቀፉ ።

ንጉሡ ባጭር ቁመታቸውና በጠርባሪ አመለካከታቸው እየተቆነኑ ፣ ወደ ምክር ቤቱ የውጪ ደቡባዊ ሰገነት ሲያመሩ ማጀብ የሚገባቸው ብቻ በዝግታ ተከትለው ሔዱ ።

ሕዝቡ እንጋጦ እያየ እልልታና ጭብጨባውን አቀለጠው ። ንጉሡ ላመል ታህል አንገታቸውን ስብር ቀና ፣ ቀኝ እጃቸውን ወለብለብ ፣ ጥርስ ሳይገልጡ ፈገግ እያሉ አሽቆልቁለው ተመለከቱ ።

ቀኛዝማች በላይነህ ታፈሰ ፣ የንጉሡን ችሎታ እያደነቁና የገባ የገባቸውን ሐሳብ ብቻ እያሰላሰሉ ፣ መንፈሳቸው በደስታ ተንበሸበሸ ።

ከቀኑ ሰባት ሰዓት ላይ ታላቁ ቤተ መንግሥት በተደረገው የምሳ ግብዣ ላይ 'ሲቪል ጠቆር ያለ" በሚለው የአለባበስ ደንብ መሠረት የታዘዘውን ለብሰው በቦታው ላይ ሲገኙ የተሰማቸውን እርካታ ፣ ያው የእንቃሩ ውቢት ሚካኤል ይገልጽላቸው እንደሆን እንጂ ፣ ሌላውንማ ችሎታ አለው ብለው አይገምቱም ።

# ምዕራፍ ሐያ አምስት

ቀኛዝማች በላይነህ፣ አዲስ አበባ ከቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ወደ አፍንጮ በር በሚያዘልቀው መንገድና ከራስ መኮንን ምንጭ በላይ ሰባ ደረጃን ወጥቶ ወደ ቀኝ እጥፍ ሲሉ ካሉት ትላልቅ ባለ ሰፋፊ ግቢ ቤቶች መካከል መለስተኛ ግቢ ያለውን ቤት ቀደም ሲል በዘመድ በኩል ተከራይተው ስለነበር፣ የቆየ የከተማ ነዋሪ እንጂ አዲስ መጥ የገጠር ሰው አልመሰሉም። ግቢው በልዩ ልዩ አትክልትና ቁመተ — ኩንትሽ አናተ ክርክም ዛፎች የተዋበ ነው።ጥቁርና ቀይ ኮረት የፈሰሰበት ሁለትና ሦስት ርምጃ ወርድ ያላቸው መንገዶች ሲኖሩት፣ ረዘም ባለ የግንብ አጥር ታጥሮ በድምድማቱ ዙሪያ ዐልፎ ዐልፎ ሹል ብረቶች ተተክለው እሾሃም ሽቦ ተዘርግቷል።

ከትልቁ ባለ ሁለት ተካፋች የብረት በር አጠገብ ከልግ እንጨት የተሠራች አነስተኛ የዘበኛ ቤት አለች። ዋናው ቤት፣ ሰፊ ሳሎንና ሦስት የመኝታ፣ እንዲሁም የገላ መታጠቢያ፣ የዕቃና የወጥ ቤት ክፍሎች ያሉት ሲሆን፣ የበስተጀርባዎቹ አራት መደዳ ክፍሎች ደግሞ የሠራተኞች ማደሪያና የኩትት ማጎሪያ ናቸው።

ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ፣ መጀመሪያ የገቡ ዕለት ማታ፣ አለመደው በረት ገብቶ ግር እንደሚለው እንግዳ ከብት፣ ልባቸው ፈርቶ ቀልባቸው በርግጎ ነበር።ዕቃውም፣ ቤቱም ነፍስ ያለው መሰላቸው። «እንዳደጉበት እልፍኝና አዳራሽ እንደልብ መለስ ቀለስ የሚሉበት ሳይሆን በጣም እየተጠነቀቁ የ ሚገቡበት ቤት መሰላቸው። ከጥቂት ዓመታት በፊት ለዘመድ ልቅሶ መጥተው የሰነበቱበትን ቤት ከዚህኛው ጋር በሐሳብ ሲያነጻጽሩት ‘ኧረ — ወዴትና ወዴት ተገናኝቶ’ አሉ። በመጨረሻማ ‘እንዲህ ያለውን ቤት ማ ችሎ ይሠራዋል ? ቀድሞስ ምን ያክል ብር ይጠእመዋል? ሁለመናው ያጥበረብራል ፣ ምናልባት ንጉሡ ማረፊያ ይሁንሁ ብለው ሰጥተዋቸው ይሆናሊ ፣ እንዲህ ያለውን ቤት ማያኸምሳል’ በማለት ተገርመዋል።

ከቁመቷ አጠር ፡ ከመልኳ ቀላ ብላ ፡ ከወደ ቂጧ ደልደል ያለችውን ልጅ — እግር ሠራተኛ ፣ ገና የጅ ውሃ ይዛ ስትገባ ትኩር ብለው አዩዋት። ቀኛዝማችን ካሸፈተው ከወ/ሮ ደጅ ይጥኑ ቂጥ ወዲህ፣ የቡና ሙቀጫ የምታካክለዋ ቂጥ ሁሉ ታናድዳቸዋለች። በሰበቡ

ወይዘሮ ደጅ ይጥኑ ትዝ አሏቸውና 'ይታባቷንስና! እዳሜ ሥር—
—ሥሩን ተኋሁና አንቺ ቅደሚ እኔ እከተላለሁ ተባብላ መምጣቷን ያላወኩ መስሏታል? ይኸነዬ እሷ አንዱ ሥርቻ ተወሽቃ ይሆናል ። ይኸን መሳይ ክብርት ማባቷ ይሰጣታል ። እሷ እንደ ነዳይ ከገረገራ ውጪ፣ እኔ እንደ ቀዳሽ ወደ መኻል ሆንኳታ! አይ አንተ ጎርጊስ! አሁን ያንተ ገለታ ምንድን ነው?" በማለት ኩራት እየተሰማቸው አመሰግነዋል ።

*   *   *

ቀኛዝማች ከቤተ—መንግሥት ግብዣ እንደ ተመለሱ፣

"ቀንቶሁ ዋልኩ ወይ?" አሉ ሴትዮዋ ።

"እዎ!እንዴት ያለ ማለፊያ ቀን መሰለሽ" አሉ ኩራትን በሚያ ጉላ ወፍራም ድምፅ ።

"እንዲያው አሁን ተምር እሳቸው ዘንዳ ቀርበሁ ባይንሁ አየኋቸው ?"

"እንዴታ!"

"እስቲ ሙች በሉኝ?!"

"ምን መሆንዋ ነው! ገጥ—ለገጥ! አልኩሽ!"

"ምነው እንዲህ እንደ ማንቻውም ሰው አይታዩም ሲባል?"

"ኧረ በፈጠረሽ አምላክ! በይ ደሞ እንዲህ ብለሽ እሰው ፊት አውሪና እነዚህ ባላገሮች — — —"

"ምን ቅብጥ አርጎኝ—ሆ!" ብለው ራሳቸውን ነቀነቁና፣ "እምኔ ላይ ሞኝነት አየሁብኝ? ባይን አይታዩም፣ ትኩር ብለው ሲያዩዋቸው ግርማቸው ያስፈራል ሲሉ ሰምቼ ነውዬ፣ እኔ ተስተሁሉስ ምን ዶሎኝ!" አሉ ምነው ባልጠየቅሁ በማለት ።

"እኮ በይ በቃሽ?! ሲሉ ሰማሁ ተብሎ እንዲህ ያለው ነገር አይጠየቅም ። ቂል ናቸው ወይ ያሰኛል፣ አሁንስ ብቻችንን ነን ። እማታውቂውን ጉዳይ እሰው ፊት እንዳትጠይቂ ። ለብቻችን ስንሆን — —"

"ኧረ ንሺ ሰዎች! አንቱስ ብትሆኑ ግርማ ሞገሳቸው እንደ ታቦት ይከብዳል፣ ደፍሮ እሚያያቸው የለም ስትሉ አልነበረም ወይ?" አሉ በትዝብታዊ ሥላቅ ።



"እንደ ሰው ይታያሉ ወይ ማለትሽን ጠላሁቲ፣ ሌላ —ሌላውንማ ልክ ነሽ ። እንዲሁ ሲታዩማ ላይንም አይሞሉ ። ባጠገብሽ ሲያልፉ ያርገደግዱሻል ። አንደዬ ደፍረሽ ካየሻቸው ደግሞ፣ ዐይንሽን ንቀይ—ንቀይ አይልሽም" አሉ ሣቅ—ሣቅ እያሉ ።

"አሁን መቼም ጨዋታ ነው የያዝነው ። እንዲያው ለመሆኑ ማንን ያህላሉ ?" አሉ ዘና ባለ አንደበት ።

"እኪደከ! ማንን ያህላሉ ልበልሽ? ?አጭር፣ ቀጭን፣ ብስል ቀይ ናቸው ። ካሽከሮቻቸው ጋር ሲያስተያዩዋቸውማ — — ካፍ የወደቀች ጥሬ ነው እሚያህሉት — — ለወደፊትማ እዚች አቅርቧ እማርያም ሲመጡ ታያቸዋለሽ ። "

"ወዮ ጉድ! እኔ ደሞ ጉላ ያሉ ይመስሉኝ ነበር — —"

"ኧረዲያ እህል በልተው እሚያድሩም አይመስሉ ።"

"ያው ጠሙና ጠሎቱ ነዋ! እቀዝቃዛ ውስጥ እየገቡ ነው እሚ ጠልዩት ይባል የለ?"

"እሱንስ እኔም ሲባል ሰምቻለሁ ። ባይኔ አይቻቸዋለሁ የሚል አላገኘሁሚ !"

*   *   *

ወይዘሮ እልፍ ይኩንዱ፣ ቤትና ግቢያቸውን ቀስ በቀስ ለመዱት ። በየክፍሉ ያለውን የኤሌክትሪክ ማብሪያ ማጥፊያ የፈሩትን ያህል ደፈሩት ። "አሁን እዚህ ላይ ሰው ተቀምጦ — — —" በማለት ሁለት ሦስት ቀን ያዘኑለትን የሽንት ቤት መጸዳጃ ም ተጠቀሙበት ። በተለይ የገላ መታጠቢያውን ገንዳ ወደዱት ።

ከሩቅ የሚታዩ መኪናዎች እስኪያልፉ ቆሞ መጠበቅና መፍራታቸውም እያደር ቀረ ። ከዋል—አደርም አንዳንድ የአገራቸው ሰዎች ለቀኛዝማች ክብር በሚያደርጉት የመስተንግዶ ግብዣ ላይ እየተገኙ ከብዙ ሰዎች ጋር በመተዋወቃቸው፣ ሲሰማቸው የነበረው የባይተዋርነት ስሜት በመጠኑ ተቃለለ ።

አእምሮአቸው የሚበጠበጠው ምንዳዬና አፈሣ በዐይነ—ሕሊና ሲታዩዋቸው ነበር ። አፈሣ ትዝ ሲላቸውማ፣ አይንቁ ንቀት ይንቁትና፣ "ከሰው ጋር የተዋዋልኩ መስሎኝ መለመላዬን ልቀር ነበር ። አበስ ገበርኩ ጌታዬ፣ ይኸነዬ የስሜ ብዛቱ" በማለት ያሳቅሉታል ።

ወደ ምንዳዬ መለስ ሲሉ ደግሞ ደማቸው ይፈላና፣ "ምነው አብሮ በመጣና ይኸን መሳይ ክብርትና ማረጌን ባየው ። ይኸ አነካኪ፣ የጦም ዕቃ! እንዲያ ተወዲያ ወዲህ እያለ ቲያበግነኝ እንደ ከረማት ተራውን ይበግን ነበር ። ምነው በተፋጁልኝና አንዳቸውን እንኳ በተገላገልኩ" በማለት የሚያፋጅ ተንኮል ያልማሉ ።

ቀኛዝማች፣ ከሰኞ—ዐርብ፣ "መሐሪና ይቅር ባይ የሆንህ አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ! የዛሬውን ስብሰባችንን የተባረከ አድርግልን — — " በማለት ፣ ለኢትዮጵያ አንድነትና ነጻነት፣ ለንጉሡና ለቤተሰባቸው ረዢም ዕድሜ በመለመን ፣ "ከስሕተትም ጠብቀን ፣ ቸር ይቅር ባይ ነህና አሜን" በማለት በአራት ሰዓት ጸሎት የሚጀመረውን ስብሰባ ወደዱት ።

በልዩ ልዩ ስብሰባዎች ወቅት በሚደረግ ውይይትና ክርክር ላይ፣ ከእንደራሴዎቹ ኑሮና ጥቅም ጋር የሚያረር ጉዳይ ከቀረበ ሸንጥን ገትሮ መከራከርና መከላከልን ፣ ነገር እየጠመዘዙና እያፈተሉ ፊር ማሳትን፣ አንዳችም ቁም—ነገር ሳይሠሩ ተንጫጭቶ መበተንን ፣ ጠቃሚ ሐሳብ የሚያቀርቡ አማካሪዎችን በሹክሹክታና በውካታ ሰሚ ማሳጣትን ፣ በዘፈቀደ ተደርቦ ድምፅ መስጠትንና ድጋፍ መንሣትን እየተገነዘቡ ሔዱ ።

ቀኛዝማች፣ ምክር ቤት እንዳዩዋቸው አንዳንድ ሰዎች ፣ ዐዋቂና የተማረ ሰው ለመምሰል ጥሩ ጥሩ ብርዕ መያዝን፣ በማስታወሻ ላይ አንዳንድ ቃላትና ሐሳብ መጻፍን፣ በተጨማሪም የስብሰባው ጊዜ ሲራዘም በግል ሐሳብ ተይዞ ማንጎላጀትን እየለመዱት ሔዱ ። ወደ ወይዘሮ ደጅ ይጥኑ ቤት ጐራ ማለቱንም፣ ካዳራሽ ወደ እልፍኝ የመግባት ያህል ስለ ቆጠሩት፣ በሁለቱ ሴቶች መኻል እንደ ሸማኔ መወርወሪያ እየተመላለሱ ይንፈላሰሱ ጀመር ።



# ምዕራፍ ሐያ ስድስት

ቀኛዝማች፣ አደራ ያሏቸው ወጌሻ 'ቀለል ያለ ጉቶ ቢጤ በገመድ አሰርና አንሣሣበት፣ አለያም እየሁ እደጅህ ትልእ ባላ ትከልና ጣይክን እየሞክ፣ እባላባልቸው ላይ መጫኛህን አስረህ ሳብ—ለቀቅ፣ ሳብ—ለቀቅ፣ ቀና—ጋደም እያልክ ሥራ—ሥር ጡንቻህን እያፍታታህ አጠናክረው ። አሁንማ በርትተሃል፣ ላይን ሚዛን ቀላል ትመስላለህ፣ ጥንክር ሰው ነህ" ብለው ከነገሩት ወዲህ፣ ምንዳዬ አነስ ያለች ጉቶ በገመድ አስሮ ሲያንሣሣ በመሰንበቱ፣ ክንዱን እንደልብ እጥፍ፣ ዘርጋ ማድረግ ጀምሯል ።

"እስኪ ምን አስቸኮለህ? ይኸንዬኮ ውስጡ አልሻረም ይሆናል ። ዋ! ነካካኸኝ ብሎ ያቁምና" ብላ ልኬለሽ እንደ ቁጣም እንደ አዘኔታም አድርጋ ብትመክረው፣

"ኧረ ወዲያልኝ፣ እኔን ሆነሽ ባየሽው፣ እንደ እውር እህያ ቤት ለቤት መዋል ስለቸኝ" በማለት እዚያው ማር አምባ ውስጥ መዞር ጀመረ ።

አፈሣ የምንዳዬን ሁኔታ በየጊዜው እየተከታተለ፣ ነጋ ጠባ ተደብቆ መመላለሱን ወደሠልስትና ወደ ሣምንት አራዝሞ፣ ቢመጨረሻም ከሣር አምባ የእኩል ቀን መንገድ ራቀ ። ምንም እንኳ አንዳንድ የአፈሣ ዘመዶች፣ ምንዳዬን በክፉ ዐይን ቢያዩትም፣ የገዛ ዘመዳቸው ተንኮል ተጨማምሮበትና ሐሰቱ ቀጋንኖ ስለ ሰሙ፣ በሱ ዳፋ ደም መቃባትና ባላንጣ ማፍራት ባለመፈለግ፣ "ጌታ አምላኸ ምኑን አዛ ከዞን አምባ አምጥቶ ጣለብን" ከማለት አልፈው አልተተናኮ ሉትም ።

ጠየምየም ብሎ ላይን ያዝ እንዳደረገ ምንዳዬ እቤቱ ሰበሰብ ከትንሹ ልጁ ጋር ተቀምጦ የባቄላ አሹቁን ሲያወልቅ፣ ቸርነት ለልኬለሽ ያመጣላትን የወይራ ፍልጥ አስደግፎ፣ አጠገቡ ዐረፍ አለና፣

"ደህና ዋልክይ? ደሞ ምን ሁነሃል? አንተ መቼም ታስበው አታጣ" አለው ቶሎ ቶሎ እየተነፈሰ ።

"ሰው ያሰበው ያጣል ብለህ ነው? ቢያጣ ቢያጣ የራሱን ጣጣ ያጣል?" አለው እየሣቀ ።

ምንዳዬ አሹቅ ዘግኖ እንደ ሰጠው ፣

"ይኸነዬ ያ ማዶ ተራራ ሜዳ በሆነና ባረስኩት እያልክ ነው" አለ ቸርነት ።

"አንተ ደሞ ሁለዬ ስላፈር ነው ወሬህ! — —"

"ሴላማ የት አባቴ ዐቃለሁ! አንተስ ብትሆን ያው አደለህ! ያንተማ ከነመዘዙ ነው ። ሴላ — ሴላውን እንተወውና ፣ እኔና አንተንስ ያገናኘን ማ ሆነና ነው ? ዐፈርኮ ነው"

"አሁን ገና አገኘኸኝ! ለዚህ ሁሉ ችግር ያደረሰኝም ዐፈር ነው ። እንዲያው ብቻ የልቤን ታላደርስ ይኸ ፈጣሪ አምላኽ አይማ ደለኚ — —" አለ ምንዳዬ እየተከዘ ።

"ይኸነዬ ያንኑ ፈሪ ሰውዬ እያሰብክ ተናደህ ነው ።ሰው አግኝተህ ሙተሃል?"

"ይኸ ያላናደደ ምን ያናድ!? 'ፈሪ ተሚፈሳብህ ጀግና ይራብህ' ይባል የለ? ይኸን ያክል እቤት መዋሌና ከስንትና ስንት እሳቤ መታጎሌስ ምን ይውጣው? ለፈሪና ለጨካኝ ትንሽ ድል ትበቃዋለች" ብሎ መሬቱን በቀኝ እግሩ ጠፋ — ጠፋ አደረገው ።

"እስቲ ቆይ ታገሥ በል! ምነው ብዙ ብዙ ስታእ! በዚህ ጉዳይ አንተ አትግባበትም ፣ እኔ — —" ብሎ ሳይጨርስ ልኬለሽ በርበሬ የተነሰነሰበት ትኩስ እንጀራ ይዛ ስለ መጣች ወሬአቸው ተቋረጠ ።

ቸርነት "እንዴት ዋልሽ?" ከማለቱ ፣ "ያውልሽ እያ ሃች ያመጣልሽ የወይራ ፍልጥ ፣ እቤት እምታበይን ራት — —"

"ጫጩት መምቻ እምታህል ጭራሮ ባላመጣም ፣ በልቼ እሔዳለሁ — — ዕድሜ ለልኬ! አንተ አሹቅህን ስታወልቅ አልነበረም? ከእግርም ቢሆን ገዳም እግር አለ ። ይኸው እኔ ከምመጣቴ ትኩስ እንጀራ መጣ ፣ ገዴን ነው ማየት" ።

"ጐሽ! እንዲህ አንጀቴን አርሰኝ! ና ግባ ብለው እምቢ ብሎኝ ነበር ።ኑ በሉ እንግባ" ብላ እሷ ገና ያልተቀረሰውን እንጀራ ፣ ቸርነት ያሹቅ ጣባውን ይዘው እየተሟሟቁ ገቡ ። ጋገራዋን እንደ ጨረሰች በማሽላ እንጀራና በሥጋ ወጥ ራት አቅርባ ጠላቸውንም እየጠጣጡና እየተጐራረሱ ጥስቅ አርገው በሉ ።

እየጠጡ ሲያወሩ ፣ ቸርነት ራሱ በቀሰቀሰው ነገር ብው ብሎ ተናደደ ።



"ተው ግድየለህም ችላ በለው!"

"ድንገት ትዝ ሲለኝ ጊዜ ነው የነደደኝ ፣ እኔማ ዐፈር አርጌው ነው ዐፈር እምሆነው ። እንዲህ እንደ ቀዘነብኝ አይቀር! የሰው አገር ሰው ነው እያለ ነው መሰል ፣ ሰው ተተግኖ ሲንቀባረርብኝ ምን ላርግ ? ካገሬ በመሬት ሰብበ ወጣሁ ። አሁን ደሞ ያው ዕድሌ ቀድሞ ቆየኝ"

"በል ተወው — ተወው! አሁን ገና ነገሩ ገባኝ ።ያን እርም አይቀሬ እሚሉ መኸገር ነው! እሱ እኮ ሰው ሊበላ ምንም ያህል አይቀረው።"

"ይበላሊ! እንዴት አይበላም? ከፋትና ተንኮሉ የዋዛ አይምሰልህ? እሱን እርም አይቀሬ ብቻ አልነበረም ፣ ሰው — በሌ ማለት ነበረ! — —እስቲ እንዲያው አሁን ይሉኝታ ቢስ ሆኖ ነውዪ ፣ እሱን የሚያክል ሰው ከኔ ቢጤ ገንዘብ ይከጅላል ? ባየሁት ቁጥር ፊቱ እንደሳት ይፈጀኛል ። አንተ ሥር — ሥሩን ለምነህና ተለማምጠህ ላሰጠኸኝ ጉልማ ፣ እሱ እርር ትክን አለ ። ያላቸውና እንደ ልባቸው የሚያርሱትስ ይሁን በጁ ፣ እኔ ባመት አንድዬና ሁለተዬ ብሰጠው አነሰው ወይ? ለዚያውም — — —" ብሎ ቸርነት ሳይጨርስ ፣

"እንዴት አባቱ ሲቀልድብህ ከርሟል በል! ለኔ ብነግረኝ ኖሮ ለሳቸው ነግሬ ቀጥ እማስደርግልህን ፣ እሱኮ ሽንቁር ጋን ነው ፣ እንኳን አንተና የተረፉቸውም አልቻሉት ።"

"እኔማ ተደህናው መሬት መርጬ እሰጥሃለሁ ፣ እስተዛሬም ተጉድተሃል እያለ ሲደላልለኝ ጊዜ ፣ የሆነልኝ መስሎኝ ያቺኑ የከተትኳትን እህል እያወጣሁ ሸጥ አረግና እሰጠዋለሁ ።ለዚያውም ሰው እንዳያይና እንዳይሰማብኝ እየተደበኩ" እንዳለ ሐሳቡ ተበታተነበት ።

"ጨዋታህን በማር ላግደውና ፣ አንተ ደሞ አንድ ዐመል አለችብህ ። ትችል — ትችልና ድንገት ቡግ ትላለህ ። እስኪ ረጋ በል እኔ አነጋግረዋለሁ ።"

"ተንግዲህ ወዲያማ በእቶኝ — —"

"ግድየለህም ፣ እኔ የሱን ዐመል አቅበታለሁ"

"ግድ የለህም አትልፋ ፤ ብቆይም ጥኢት ቀን ነው ። ባጣ — ባጣ መጥረቢያ አላጣ ።"

"ምን ሊያረግልህ?!"

"እንደ ጌሾ ቀረጣጥፌው ፣ ከዚያ በኋላ የሆነው ይሁን — —"

"ለምን ተዚህ ሁሉ እኔ ጠበንግ አልሰጥህም?" አለ እየሣቀ ።

"አታረገውሚ ፣ ይኸማ እንዴት ያለ ጥድቅ ነበር ። ስተት ብለህ ሰማይ ቤት መግቢያህን ታገኝ ነበር ። ይኸ እሚያስኮንን አይምሰልህ ። አሁን ፈጣሪ እምላኽ ይኸን እጣውና ነው ።ያንንም ያንተን ሾለቅ አፍ አብሬ ጥጭ ላርገው ! — —እስኪ በል?!"

"ሥጋ ምረጭ ቢሏት ጣፊያ! ያን የሰው ግማሽ ተወው ። ይልቅቆ ለራስህ በርታ!" ብሎ ሣቀ ።

"አንተ ለካ እየቀለድክ ነው ። ይልቅቆ ስጠኝና እንደ ድኩላ አዘልዩ ላፍርጠው — — —"

"ይኸማ ደግም አደል ! አንዱ ባለ አደራ 'ኮ እኔ ነኝ" አለ ለማስመሰል ኮስተር ብሎ ።

"ታዲያ ቤትና ንብረቴን አሉኺ ፣ የእንዲህ ያለውን እንዛራጭ ነፍስ ጠብእልኝ አላሉህ!"

"ባይሉኝም! ታማኝ አሽከራቸወን እያየሁና እየሰማሁ አስገድላለሁ እንዴ? ሰው አስገድለህ ቆየኸኝ ቢሉኝስ?" አለው ሳይሥቅም ሳይፈግም።

"ባፍህ ሙሉ'ኮ ሰው አልከው? እሱ እኮ እንደ ሰው ተቆጥሮ ሰው ሞተ መባል የለበትም ።"

"አንተ ብትገለው ምን ገደልኩ ትላለህ? ዐፈር ስሆን ንገረኝ?" አለ ሣቅ እየቃጣው ።

"እንደ ሰው ቆሞ እሚሔድ ፣ አንዳይ ገደልኩ ነዋ! ይኸው ነው"።

"በል እንግዲያው እኔ ብልሃት ልንገርህ ፣ ባንደዬ አንገቱን በጥሶ መጣልማ አይጐዳውም ። ቀስ በቀስ እያስቀዘንክ ነው ልክ እስርፋው መዶል ! ደሃ የጠላውን ሰው ፣ ደሃን እያስደሰቱ ነው መማደል ። ዛሬ ጥኢት በጨቅ ፣ ነገ ጥኢት በጨቅ — — —"

"እኔ ከምሬ ነው ፣ — —አንጀቴ አርሮ — —አንተ ትኽልዳለህ?"

"ኧረ እንዴት ልሁነው ዘንድሮ!" ብሎ ምንዳዬ ተንከተከተና፣ "ከጣለ የገለበጠ ይባል የለ? ዛሬ ቀን ሰጥቶት ቢያጠቃህ ፣ ነገ እላዉ ላይ ጉብ ትልበታለህ ። የጌታን ነገር ማን ያቀዋል ? እስታሁንም ዝም ብዬ የሰማሁህ ፣ ካንጀትህ አደለም ብዬ ነው — —"

"አሁን ገና ጉድ ያለው ነገር ተናገርክ ። የኔ ቢጤ ችግር ያጋጠማቸው ሴትዮ 'አላገኘሽልኝም አሉ' አሉ" አለ ራሱን እየነቀነቀ ።

"እንዴት ማለት?" አለ ምንዳዬ ።



"እዎ ፣ እንዴት ማለትማ ጥሩ ነው ። ሴትዮዋ አሉ ፣ ኑረው — ኑረው በስተርጅና ይወልዳሉ ። ደህና አድጎላቸው እርፍ ጨብጦ አለሁልሽ ፣ ደረስኩልሽ ማለት እንደ ጀመረ ፣ የፈጣሪ ነገር ደሃን ማሳደድ ይወዳል መሰል ፣ ይገለው ሰው ሳያጣ ወረርሽኝ ይገባና ፣ ያንኑ አንድ ልጃቸውን ላሰ ያደርገዋል ። ሴትዮዋ ነጋ ጠባ ቲያለእሱ — ቲያለእሱ ፣ ቲያለእሱ ፣ 'ያም መጥቶ አታልቅሱ ፣ ያም መጥቶ አታልቅሱ' እያለ ወቀሴታ ያበዛባቸዋል ። አንድ ቀን ታዲያ አንዱ ቲነዘንዛቸው ጊዜ ፣ 'እስቲ ና አንተ ተቻልክ ሆዴን ጥርቅም አርገህ እሰርልኝ' ይሉታል ። በገዛ መቀነታቸው ጥርቅም አርጎ ያስርላቸዋል ። 'ዋ!ልጄ! ረመጡን አላገኘህልኝም' አሉት አሉ ።"

"እግዜሩም ዐይን የለው — —እንዴት አንጀታቸው አይጨስ!"

"ይኸውልህ የኔም አንጀት እንዲህ እየጨሰ ነው — —አሁን ገና ገባህ" አለ ተደሰቶ ።

ወደ ጓሮ ዞረው ረዘም ላለ ጊዜ ተወያዩ ። ምንዳዬ ረጋ ብሎ በምክር ገባው ። ነገሩን ሳይንቅ እያቀዘቀዘ ፣ የጓደኛውን ንዴትና ብስጭት ቀስ በቀስ አብርዶ ሐሳቡን አስለወጠው ። እየተሣሣቁ ወደ ቤት ሲገቡ ፣ በእንደዚያ ዓይነቱ የሁለቱ ወሬ ጣልቃ መግባት የማትወደው ልኬለሽ ፣ መግባባታቸው ደስ ብሏት ፣ ሽከናቸውን እየሞላች ሰጠቻቸው ።

* * *

ቸርነትና ምንዳዬ የተገናኙት ቀኛዝማች ቤት በሎሌነት ነበር ። ምንም እንኳ ቸርነት ሣር—አምባ በመግባት ባንድ ዓመት ቢቀድምም ፣ ቀኛዝማች ቤት በሎሌነት በማደር ግን ምንዳዬ በመንፈቅ ይቀድማል ።

ቸርነት በሸዋና ወሎ ድንበር አካባቢ ጨፋ በሚገኘው የአልጋ ወራሽ እርሻ ውስጥ ዓመት ያህል እንደ ሠራ ፣ ወባ ይዞት ከሞት አፋፍ ዳነ ። ከዚያም የያዛትን ይዞና ሸማውን ጠቅሎ ጨፋ—ሮቢት ገባ ። እዚያም ሁለት ወር ያህል እንደ ሸቃቀለ ፣ ቅዳሜ—ቅዳሜ በገበያ ሰበብ እየሔደ ያያት ማጀቴ ደስ አለችው ። አማካሪም አልፈለገ ፣ ስተት ብሎ ማጀቴ ገባ ። ከአንድ ሳምንት የመድኃኔ ዓለም ደጀ—ሰላም አዳር በኋላ ፣ የሚያስጠጋው ሰው አግኝቶ ሥራ ጀመረ ። የአትክልት ቦታቁፈራና ኩትኮታ ፣ ጌሾ ቅርጠፋ ፣ እርሻና ምንጣሮ — — — እየሠራ የትንሿን ከተማ ነዋሪዎች ለመዳቸው ። ሆኖም ለተለያዩ ሰዎች እየተቀጠረ መሥራቱን አልወደደውም ።

ደግነቱ አራት ወራት ያህል እንደቆዩ ፣ እሚያድርበት ቤት ውስጥ በእንግድነት እየመጡ ሁኔታውን ያዩ የነበሩ አንድ የማር እምባ ገበሬ ፣ የእርሻ መሬት ሲጎልሙት ፣ ከነሳቸው ሲጋዙለት ፣ ለእርሻ ማረሻው ዓርብ ዕለትን ሲተዉለት ፣ ለሌሊት ልብሱ ዶዶ ፣ ለሥራ መሥሪያ ያቡጀዲ ቁምጣና እጅ—ጉርድ ሸሚዝ ሲገዙለት ተቀውሎ ተቀጠረ ። ሆዱን ባይርበውና ይለብሰው ባያጣም ፣ የሥራው ብዛት አስመረረው ።

እርሻ ውሎ ሲመለስ የበሬ ራት አጭዶ ፣ ወይም የማገዶ እንጨት ተሸክሞ ይገባል ። ይህን ከልጅነቱ ጀምሮ ለምዶታል ፤ ማታ ማታ ከቤት በታች በሬዎቹን እየጠበቀ ሣር ሲያበላ ፣ አገሩ ትዝ ይለዋል ። ወሎ ፣ ውጫሌ ወረዳ ድብል ማርያም እናት አባቱ ቤት ። ተወልዶ ያደገባት ቤት ፣ ተዘግታ እና ሆናለች ። ያደገበትን ቀዬ ዳዋ ወርሶታል ።

የአባቱ የአቶ ይመር አያሌው ርስት ከማነሷ ፣ ያካባቢው ባላባቶች ከወዲያ ከወዲህ እየኮረኮሚት ፣ አባቱም በተደጋጋሚ ደሴ ድረስ ላቤቱታ ሔደው ሰሚ በማጣታቸው ፣ በመጨረሻ የቀረቻቸው ሁለት ጥማድ አታውልም ነበር ። ቤተሰብ እየበዛ ፣ ይለበስና ይጎረስ እያነሰ ሲሔድ ኑሮ ያስመርራል ። የደረሰ ልጅ ያርሰው መሬትና ጎጆ ይቀልስበት ቦታ ሲያጣ ፣ የወላጅ ዐይኑም ልቡም ያነባል ።

የቸርነት አባት መሬት እየተጋዙና በጭሰኝነትም እያረሱ ኑሮን ታገሉት ። ባይንበረከኩም ተርገደገዱ ። የእኩሌታውንም ፣ የሲሶውንም ሞከሩት ። እርቦም ሰፈሩ ። ለሚያርሱት መሬት የሞፈር ማጋደሚያ ክፍያው ፣ ማርና ሙክቱ ፣ አጨዳና ውቂያው ፣ ጎተራ መጎተሩ ፣ ምርት ጭኖ ማድረሱ አንገፈገፋቸው ። ለከብት ሣር ግጦሽ ባመት በበሬ ሐያ ብር ደረሰ ። የኋላ ኋላማ ባለርስቱ አውድማ ላይ እየተገኘ ገለባውንም እኩል መካፈል መጣ ። በመጨረሻም ገበሬ እየቀጠሩ ጭሰኛውን ነቀሉት ።

ከዚያ በኋላ የቸርነት አባትና ጓደኞቻቸው ፣ ሲጫን የሚችለውን ኮተት ጭነው ከብቶቻቸውን እየነዱ ሐያ አራት ቀናት ከተጓዙ በኋላ ጎጃም ፣ መተከል ድባጤ ማርያም ገቡ ።

ለመንታ ወንዝ አካባቢ ገዢ ሐያ ብር የመሬት ግብር ከፍለው የሚበቃቸውን ያህል መሬት እንደያዙ ፣ ቸርነት ከአባቱ ጋር የእርሻ ሥራውን ቀጠለ ። ከሔዱት መኻል አንዳንዶቹ ዓመትና ሁለት ዓመት እየቆዩ ሲመለሱ ፣ ቆራጥ—ቆራጡ እዚያው ቀረ ። ቸርነትም ልቡ ተነሣ። ቢሉት ቢሠሩት አሻፈረኝ አለ ። የጎረምሳ ልቡን መግራትና ችኩል



ሐሳቡን መግታት ስላልቻሉ ፣ ተመልሶ አገሩ ገባ ። እዚያም ከሁለት ወር በላይ አልተቀመጠም ። "ደሴ ሔጄ ሸቃቅዬ እመለሳለሁ" ብሎ ቢወጣም አልተመለሰም ። እንዳሰበው ሥራ ባለማግኘቱ ከደሴ ጨፋ ሔደ ። ጨፋ—ሮቢትም ለማጀቴ አስረከበችው ። ቸርነት እንዳለው 'የሀል ውሃ ነገር ሆነና' ማር—እምባ በሎሌነት ተሻገረ ። ገበሬው ቤት አንድ ዓመት እንዳገለገለ ፋታ የለሹ ሥራ አንገሸገሸው ። "እዚህ ብቻዬን ከምንገላታ ፣ ብዙ ሎሌ አለበት ቤት ይሻለኛል" በማለት ቀኛዝማች በላይነህ ታፈሰ ዘንድ እማላጅ ልኮ ሎሌነት ገባ ።

ከምንዳዬ ረዘም ይላል ። ቀጠን ብሎ ሸንቀጥ ያለ የቀይ—ዳማ ወንዳወንድ ነው ። ሲሥቅ ጥርሱና ጉራማይሌው ደስ ይላል ። ደፋር ቢሆንም አይቸኩልም ። ዐልፎ—ዐልፎ ግን ድንገት ቱግ ይላል ። ቸርነትና ምንዳዬ ቀስ በቀስ እየተግባቡ ተዋደዱ ። ከተራ ትውውቅና ወሬ ፣ ሰፋ ወዳለ ወዳጅነትና ምስጢረኝነት ተሸጋገሩ ። ቀኛዝማች ቢወዱትም ፣ "ይኸን ልጅ አትበድሉት ፣ የሰው አገር ሰው ነው" ከማለት አልፈው እንደ ምንዳዬ ምስጢር ነክ መልዕክት አይልኩትም ።

ሸዋርካብሽ ቁመናና ቅልጥፍናውን አይታ ብትወደውም ፣ እሱ ግን ፣ ችላ ብሏት አረጋሽን ወደደ ። በተለያዩ ጊዜም በጠላውም በጉርሻውም ልትደልለው ሞከራ አልሆን ስላላት ፣ ያደረገ ፣ ያላደረገውን ለወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ እየነገረች አስጠመደችው ። ሴትዮዋ በምኑም—በምኑም የተበሳጩና ሸዋርካብሽ ቅናቷ ያገረሸ ዕለት ፣ "ለኔ ሲል ነው እንዴ ከበእሎ ጋ ቲያዘጠዝጥ የዋለው?" በማለት ከእህል—ውሃ አቅም ያሳንሱበታል ። በእንዲህ ያለው ጊዜ "ዕድሜ ለልኬ" ብሎ ምንዳዬ ቤት ዘው ይላል ።

ምንዳዬ ቀስ በቀስ የቸርነትን ችግርና ታማኝነት ለቀኛዝማች አስረድቶ ጉልማ አሰጠው ።

## ምዕራፍ ሐያ ሰባት

የአፈሣ ከቤት እየራቀና ወሬው እየጠፋ መሔድ ከአስካደች ይልቅ ልኬለሽን አሠጋት ። "ይኸ ሰው እንዲህ አምርሮ ከጠፋ ነገር አለው ማለት ነው ። ምነው እንዲያ የጠላኋቸው ሰውዬ ፣ ይኸንዬ በመጡና ይዘውልኝ በሔዱ ። አፈሣ ገደለውም አስገደለውም የሞት ሞት ነው ። እዚያው ሔዶ ቢንገላታ ይሻላል" እያለች ትሸበራለች ።

ምንዳዬ የመበቃቀልን ጠንቅ በሚያስቀር የአካባቢ እርቅ ፣ ሿራን እንዳይሻገር ከባላገሮቹ ጋር እንዳደረገው የከልል ገደብ ፣ አፈሣም በገዛ ፍርሃቱ የከለለውን ድንበር ዐልፎ ወደ ሣር—አምባ ላለመዝለቅ አገር ቆርሮ አደፈጠ ። የሆነው እስቲሆን አዝመራውን ሰብስቦ ምር ቱን ጎተራ እሚከትለት ዘመድ አገኘ ። ሚስቱንም ጎራ ዞሮ አለሁልሽ አላት ።

ያለ ሥራ ውሎ እማያውቀውና ከሰው መዓድ ቆርሶ መብላት ያልለመደው እጁ ፣ ቦዝኖ እየዋለ 'ኑ ግቡ ገበታ ቀርቧል' እየተባለ መጠራቱ ከፉኛ አበሳጨው ።

አሞቱ የመረረ ወኔ አጎነቆለ ። "ነገሩን ከወዲያ ወዲህ አሳክራ ለዚህ ያበቃችኝ እሷ ናት" በማለት ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱን ያማር ራል ። አገልግል ጥሎ መሸሹን ግን ፣ "ደህና ቦታ ላይ መትቶት ቢሆን ኖሮ ይኸ ሁሉ ጣጣ አይመጣም ነበር" በማለት ፍርሃቱን እያድበሰ በሰ ራሱን ይሸነግላል ።

ከሬሣ ጠባቂዎች ጋር አብሮ ያደረለት ሌሊት ፣ ተረተኛው ሽማ ግሌ ስለ አንድ ፈሪ ሰው ተርተው እንደ ፈጸሙ "ጥንቸል አንበሳ ሆነ ፣ ቢዘል እማጀት ፣ ቢወጋ ምንቸት" በማለት የተናገሩት ምሳሌ ከራሱ ሁኔታ ጋር እየተመሳሰለ አስቸገረው ። አንዳንድ ጊዜ ብቻውን ሲያስብ ፣ ከሆነለት በግሉ ፣ አለበለዚያም አንድ ታማኝ ሰው ፈልጎ ምንዳዬን ለመግደልና ለማስገደል ይወስንና ፣ እንደገና ደግሞ ሆዱ ይባባና ሥጋትና ፍርሃቱ ይቀራመቁታል ። ሐሳቡ እየተለዋወጠና ጥርጣሬው እየተዘበ ራረቀ ስለሚያስቸግረው ፣ ጨርቁን ያልጣለ ንክ መሰለ ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ፣ "እንዲህ ያለውን መዘዘኛ በሽማግሌ መታረእም እኮ የማሸነፍ ያክል ይብቃው ። ጌታ ፈርዶብኝና ሰይጣን አሳስቶኝ አጥፍቻለሁ ። ሽማግሌ አቅሜን አይቶ በወሰነ እከሳለሁ ብዬ ለምድር — ለሰማይ

የከበዱ ሰዎች ብልክ እምቢ አይልም ። በየሀ ላይ እሱ ምን ያክል ተነካ? ገደለዪ አልሞተ ፣ ይኸው እሱ ራሱስ ቢሆን ሰው ገድሎ የደም ማድረቂያ ከፍሎ እንደልቡ ይኖር የለም ወይ?" በማለት ከጨመደዱ እማይለቁ ሽማግሌዎች ማሰላሰል ጀመረ ።

አንድ ቀን ከራት በኋላ ፣ ካረፈባቸው ዘመዱ ጋር ጠላ እየጠጡ ሲያወሩ ፣ ጭውውታቸው ዞሮ ዞሮ ወደ ምንዳዪ አመራ ።

"ትላንት እንዳጫወትከኝ ፣ ሽማግሌ ተልኮበት እሺ የሚል ከሆነ ማለፊያ ነው ።"

"አንዳንድዪ ቁንድፍቲያም ቢጤ ነውዪ ፣ ከሽማግሌ ቃልስ አይወጣም ። ሰው ያከብራል ። መምሬ ተክለ ጎርጊስም ዘመዱ ናቸው ። ሀይ ካሉት እምቢ አይልም ።"

"'ትንሽ ሥጋ እንደ መርፌ ትወጋ' ይባል የለ ! የገዛ ሥጋቸው ተጎድቶ አይሽመግሉንም ?"

"እሱማ ሰው ለዘመዱ ነው ። ቢሆንም ለኔም ደጊ ናቸው ። እምቢ አይሉኝም።"

"ሌላስ? እስቲ ደህና—ደህና ሰው አሰላስል ፣ እማያዳግሙ ። እን ዲህ ያለው ነገር ውሎ ቢያድር ደግ አይደለም ። ካሠው መባልህ አይ ቀርም ሽማግሌ በደነባ ትከሠዋለህ ፣ ባይሆን ተወላጁ ሁሉ ይረዳል" እሉ የራሳቸውን ርዳታ በሐሳባቸው እየወሰኑ ።

"እሚካስማ ምን ጠፍቶ! አልታረእም ብሎ ያገረገረ እንደሁ ብዪ ነውዪ ።"

"እምቢ ታለም ምን ችግረህ! እስቲ ደሞ ሌላ ብልሃት ልንገርህ ። እኔ ነገርህም አልጣመኝ ። እንደዪ ጠማማ ነው ፣ እንደዪ ከሽማግሌ አፍ አይወጣም ትላለህ ።"

"እ?" አለ ሐሳቡ ተማቶበት ።

"በጄ እማይልና በከንቱ እሚያታክተን ከመሰለህም— —ና እስቲ ወጣ እንበል" ብለው አብረው ወጡ ።

እየሩ በጣም ይቀዘቅዛል ። የእንጭራሩ ፣ የልዩ ልዩ ነፍሳትና ትላትል ሲርሲርታና ጩኸት ባያደነቁርም ፣ ስሜትን ያውካል ። ጥግ ይዘው ጨለማው ውስጥ እንደቆሙ ፣ "ሴት የሰማው ወሬ ደግ አይደ ለም ብዪ ነው ። እንግዲህ እህ ብለህ ስማኝ ። በሽማግሌ ተሞክሮ እምቢ ካለ ፣ ሌላ ዘዴ አለችኝ ። ጨለማ ለብሰህ ፣ እያደፈጥክ እያስፈራራህ



ብታስበረግገው አንተ እንዳልክ ፣ ታስብለዋለህ ። ይህም የግድያ ያክል ነው ።"

"እንዴት?" አለ ግር ያለው መስሉ ።

"ቢሻህ ከኔ ጋ ፣ አለያም ከሌላ ሰው ጋ ሣር—አምባ እንሔድና..."

"ሔደንስ?"

"ከሔድንማ ምን ያጠያይቃል?"

"ተኩሶ ለመግደል?"

"እኮ ቆይ!— —ቸኮልክሳ? አታረገውሚ ብታረገውማ ተገላገልክ። ያገርህን መግቢያ መውጫያውን ታቀዋለህ ፣ ዛሬ አንዱ ጋ ፣ ነገ ሌላ ጋ እያደፈጥክ ፣ በጀሮ ግንዱ ብታኖጋበት ፣ ይሽ ሰው እያስቀምጠኝም ብሎ አገርህን ጥሎልህ ይሔዳል ።"

"ማ? እሱ? አይ አለማወእ! ግታ ቢተኮስበት ፣ ውድእት ላይ አድፍጦ ሰውም ዝር አያስኝ ፣ ሣር—ቅጠሉን ቢያስስ እቤቱም አይ ገባ ። ሰው መስሎሃል?"

"እንዲህ እምትፈራውማ ከሆነ በቁምህ ገሎሃል? እኔም አብሬህ እሔዳለሁ"

"ኧረ ምን በወጣሁ! እሱ ለራሱ ሴጣን ነው ። ሲገሉህ መጡ ቢሉትም ሆዱ ዱጭ አይል ።"

"እንግዲያውማ ምን ጣጣህን ታበዛለህ! 'ወደው የጣጡት ቅል ጥም ከብርንዶ ይጥም' እሉ ። የሆነው እስቲሆን ዐርፈህ ተቀመጥ ። እንዲህ እንደምትለውማ ናቡቴ ከሆነ ፣ እዚህም ቢሆን እነፍገር መም ጣቱ አይቀር ።"

"እኔም ሥጋቱ ይኸው ነው ።"

"ምን ያለኸው ነህ ወንድሜ! ሰው እንዴት ናዳ እስቲደረባበት ቆሞ ይጠብቃል? ይህን ያክል ፍሪያት ደግም አይደል !"

"የፍሪያት እንዳይመስልሁ ፣ ሰውዪው እኮ ሸፍቶ ነበር ። እንዳይ መተት አለው ። ይልቅዪ ሥር—ሥሩን ደህና ሰው አፈላልጉልኝ"

"እንዴት ያለ ሰው?"

"እኔ ቤት እንደ አራሽ ገብቶ የሚሠራና የኋላ—ኋላም መግቢያ መውጫያውን ተከታትሎ ዱብ አርጎት ዘወር እሚል ሰው ። ያሉኝን እሰጣለሁ ።"

"ይኸን መላ ነው ብለህ ልብህን አታክር ። ይልቁኑ ከበረታህ በየትም—በየትም ብለን ከባላጋሮቹ ጋ እንነጋገርና እምናደርገውን እናርጊ ለማይሆን ነገር ንብረክን አታባህን ። ቀስ ብለው ታማከሯቸው እነሱስ ቢሆኑ ዝም እሚሉ መሰለህ ። ውስጥ ውስጡን እየነደዳቸው መቆጨታቸው አይቀርም" አሉት ።

በመጨረሻም ከባላንጦቹ ጋር ዶልቶ ፣ ምንዳዩን ለመግደል ፣ ካልተሳካም በዚህም በዚያም አዋክቦ አገር ጥሎ እንዲጠፉ የሚደረግበትን ዘዴ ተነጋግረው እንዳበቁ ፣ የአፈሣ ልብ ዳግመኛ የተንኮል ጥንስስ ጠንስሳ ወደ ቤት ገቡ ። እፎይ ብሎ አደረ ።



## ምዕራፍ ሐያ ስምንት

ወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ ፣ የአካባቢያቸውን ሴቶች አለባበስ በመመልከት 'ቶሎ ቶሎ ልበሽ' የተባሉ ይመስል ፣ ሦስት ቅያሪ ልብሶች ገዝተው ሲለዋውጡ ፣ የአካል ፣ የዳሌና የቂጣቸው ቅርፅ አብሮ የሚለዋወጥ መሰለ ። ቀኛዝማች የቤትዮዋን የእግር አጣጣልና አነግሥ ተከትሎ ሽቅብ ቁልቁል የሚርገፈገፈውን የወገብ በታች መቀንዘሪያ እያዩ ቢጎመዡም እንደ ቀድሞው ፋታ አጡ ።

"እንኳንም ትቻት ያልመጣሁ ፣ ይኸነዩ አዳሜ ቀኛዝማች ባገር የሉም እያለ ያማግጢት ነበር" በማለት ራሳቸው በሚፈጥሯቸው ተቀናቃኞች ይቀናሉ ። ባስ ሲልባቸውም ፣ የተለያዩ የማጀቴ ወንዶችን ይወሽሙላቸዋል ። በመጨረሻ ግን ፣ እንደውኑ ዓለም ፍላጐታቸው ፣ ሁሉንም ገፈታትረው የግላቸው ያደርጓቸዋል ። እንደ ምኞታቸውማ ቢሆን ኖሮ የሚፈልጓቸውን ሴቶች እንደ ከብት አንድ በረት ውስጥ አጉረው ሲያስፈልግ ፣ ሲያስፈልግ በየተራ እያስጠሩ የልባቸውን ለማድረስ ምንኛ ሰፊውን በረት ባስከለሉ ነበር ።

የቀኛዝማች በላይነህ ታፈስ ሕይወት ወደ አዲስ የኑሮ ክልል በመግባቷ ፣ የማያውቁት ጉዳይ እየበዛ ፣ ከራሳቸው ጋር የሚያነጻጽሯቸው ሰዎች በልዩ ልዩ ሁኔታዎች እየበለጧቸው ፣ አንዱን ሲያጤኑና ሌላውን ሲከተሉ ኑሮ ዐይን አዋጅ ሆነባቸው ። ምንም እንኳ በአመለካከትና አንድን ፍሬ ሐሳብ አጣጥሞ በመገንዘብ ረገድ ከሌሎቹ እንደራሴዎች እጅግም ባይለዩም ፣ "ካንዳንዶቹስ እሻላለሁ" የሚለው የግል ግምታቸው ግን ያሰቡትን ያህል አልነበረም ። ሆኖም ትክክለኛ ችሎታቸውን ለመገምገም ብዙ ጊዜ አልፈጀባቸውም ። "አዳሜ እናቱ ሆድ አልተማረው ፣ እኔ አብዛኛው እድገቴ በግብርና ነው ። ነገር ሳደራና ስሸምን አልኖርኩ" ብለው ብልሃት አበጁ ። ይኸውም ልዩ ልዩ ሐሳቦችንና ጉዳዮችን ለመረዳት ካንዳንድ እንደራሴዎች ጋር መተዋወቅንና አብሮ መዞዋወርን አዘወተሩ ። በዚህ ምክንያትም ከሚስትና ከቅምጣቸው ጋር የሚያሳልፉት ጊዜ እያደር ተጣበበ ።

ምንም እንኳ የወራቱ ማነስ ለትዝብት ባያበቃም ፣ በሁለቱም ሴቶች ውስጥ ተቀብሮ የኖረው ቅናትና ፉክክር በማገርሸቱ ፣ የከተማው ግብግብ ተጀመረ ።

ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ቅናታቸውን ለማብረድ ፣ የሚመቷት የቤት ልጅ ፣ የሚነርቷት አህያ ፣ የሚገላምጡት ሎሌ በሌለበት ግቢ ፣ ቀኑ በግድ መሽቶ ፣ ሌሊቱ ባግር ይነጋላቸዋል ።

ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑም ፣ በአቶ ወርቅነህ ፊት የተመኩበት የቀኛዝማች ውዴታ ከመጀመሪያዎቹ ሁለት ወራት በኋላ ከዕለት ወደ ዕለት በመቀነሱ ፣ "ይኸ ነገር የጤናም አይደል ፣ ይች ደጋን እግር መቸ በደህናዋ መጣችና ፣ ያቺኑ መተቷን አስመትታ ነው ፣ አለያም አጉል መከራ ገብቷል" በማለት የቀኛዝማችን እግር ጠብቆ የሚገባ ሰው ለማግኘት ይጓጉ ጀመር ። ሰውዬው ግን ፣ ከተቻለ ከንጉሡ ባለሟሎች አንዱ ለመሆን ፣ ወይም ኑሯቸውን ለማደላደል ፣ የዘር ሐረግ እየመዘዙ ፣ የደም ቅራሪና የሥጋ ምታሪ እየፈለጉ ማንጋጠጥ ከጀመሩ ውለው አድረዋል።

ቀኛዝማች በመታያና በእጅ መንሻ ብዛት ፣ ያልነበረውን አስምጠውና አስወልደው ፣ ጎራ ዞረውና ሜዳውን አቋርጠው ፣ ከምንጅላትም ይሁን ከንጃላት ከተወለዱ በኋላ ፣ ባጭር ጊዜ ውስጥ ከመሰላሉ ግርጌ ቆሙ ።

የአቶ ወርቅነህ መዘውር ምክርም ገና ከጅምሩ ልባቸውን ሰርስሮ በመግባቱ ፣ ጥረትና ፍላጐታቸው ሁሉ በምክር ቤቱ ውስጥ ስለሚመክርበት ፣ ልዩ ልዩ ሀገራዊ ጉዳዮች በመሆን ፈንታ በየትና በነማን በኩል ርስትና ልዩ ዕድገት እንደሚገኝ ተግቶ ማነፍነፍ ሆነ ።

ያ—በምርጫ ውድድር ወቅት ለገጠሩ ሕዝብ ፣ 'የመኪና መንገድ አሠርቼ ፣ ሐኪም ቤት አቋቁምልሃለሁ ፣ ተማሪ ቤት አስከፍቼ ፣ ግብር አስቀንስልሃለሁ ፣ ችግርህንም ለንጉሡ አደርስልሃለሁ — —' እያሉ በየገበያና በየቤተክርስቲያኑ ፣ በየሸንጎና በየመንደሩ ያሰሙት ባለ ተስፋ ንግግርና የገቡት ቃል ኪዳን ሁሉ 'ገለል በል' ተባለ ። ከእንግዲህ ዋናው ጉዳይ ሕዝቡና ችግሩ ሳይሆን የግል ኑሮን አደራጅቶ ካመት እስካመት የሚታረስ ርስት ማግኘትና 'ደረተ ሳንቃ ፣ አንገተ መቃ' ቤት ማግረጥ ናቸው ።

* * * *

"ለኔስ ያው ማጀቴዩ ይሻለኝ ነበር" አሉ ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ከቀኛዝማች ጋር ምሳ እየበሉ ።

"እንዴት ?"

"እዚያ ምንም ቢሆን ሰዉ ፣ ሰው ያከብራል ። የሰው ማንነቱ ይታወቃል ።"



"እዚህስ?" አሉ እየሣቁ ።

"እዚህማ ትልእና ትንሹ በምን ይለያል ፣ እንደ ከብት እየተጋፉ መሔድ ነው ። አበስ ገበርኩ እቴ!"

"እዚህኮ ሁሉም የሠለጠነ ነው ፤ እነዚያ ገጠሬዎች ናቸው ፤ ምን ያቃሉ?"

"ባላገር ናቸው ለማለት ነው? ድንቄም እቴ! አይይ! ተሠልጥኖ ተሙቷል! ያለመሠልጠን አይመስልሁ ፣ ሰዉ እስበሱ ይከባበራሊ! አሁን እኔን እዚህ ማ ያቀኛል? አንቱንም ቢሆን እንጃ? እዚያ ቢሆን መጡ መጡ ፣ አለፉ አለፉ ባዩ ብዙ ነው ። ክንብንቡን እሚያወርደው፣ ለጥ ብሎ እጅ እሚነሳው ፣— — ኧረ ምንና ምን? — — አንቱ እንኳ ብቅ ብቅ ብትሉ ምን አለበት? ለካ እንዲህ ይዋደዳሉና መባሉስ ምን ይውጣው? ለዚህ ለዚህማ እዚያው አገሬ የምንዳዬ መልክት በስንት ጣሙ እቴ?" በማለት አማረሩ ።

" 'ሩቅ አሳቢ እቅርብ አዳሪ' አሉ ። እኔ ገና ስንትና ስንት አስቤልሻለሁ ፣ አንቺ በየእንቶ ፈንቶው ትበሳጫለሽ ። ስንቱ ምናምንቴና አባቱን ጠርቶ አያቱን እማይደግም መሰለሽ ዛሬ ቢጠሩት እማይሰማው? ስንቱ ሥርና ግንድ የለሽ መሰለሽ እዚያ ላይ ፊጥ ያለው? እንደኔ ያለው ሞኛ—ሞኙማ ፣ ከገበሬ ጋር አፈር ሲያገላብጥና ጓል ሲከሰክስ የትም ቀልጦ ይቀራል ። ላለፈ ነገር ቢጸጸቱት ምን መላ አለው? ይኸ ነዬ ነው መበርታት ። አንቺ ታዲያ — —" ብለው እንደ ጀመሩ ፣

"ቢሆንም ፣ መጣ ብሎ መለስ ለማለት ምን ያክል ቲያደክምሁ ነው? ሩቅ አትሉ ነገር አፍና አፍንጫ ነው ። እንዲያው ለነገሩ ነዩ ፣ እኔማ ምንም ያጣሁት ነገር የለም ። ዕድሜ ለዘመድ ፣ ቤቴ ሞቆ ፣ ጥርሴ ሥቆ እንደልቤ እኖራለሁ ። አንቱ ግን — —" ብለው በእንጥልጥል ተዉት ። ሰውዬው የብስጭት መሆኑን ያውቃሉ ። እንደ ተለመደው በተስፋና በስጦታ ሸነጋግለው ቢመልሱም ፣ የሴትዮዋ ልብ ግን ሸክክ አለ ።

* * *

አዲስ ኑሮ የገጠማትና አካባቢው የተስፋ እጁን ዘርግቶ የተቀበላት ላቀችን ነበር ። በዕድሜ እኩዮቿ የሆኑት የአቶ ወርቅነህ መዘውር ሁለት ሴቶች ልጆች ፣ ከትምህርት ቤትና ከዙረት መልስ ፣ ሌላው የጊዜ ማሳለፊያቸው የወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ቤት ነበር ። ካደጉና በመጠኑም ቢሆን ሁኔታዎችን ማገናዘብ ከቻሉ ወዲህ ፣ እንደ ላቀች በቀጥታ

ከገጠር መጥቶ እቤታቸው የኖረ ሰው ባለመኖሩ ፣ በአነጋገርና በግልጽነቷ ፣ በአለባበስና አረማመዷ በመደሰት ወደዷት ። በተለይ ገራገርነቷ አስደሰታቸው ። በተውሶ የማይወሰደውንና በምኞት የማይገኘውን ቁንጅናዋን እያደነቁ አቀረቧት ።

አንድ ቀን የወ/ሮ ደጅ—ይጥኑን ርቆ መሔድ አይተው ፣ አንድ ከጉልበት የማያልፍ ቂጥ ወጣሪና ዳሌ አሳጣሪ 'የፓሪ ሞድ' ቅድ አልብሰው አረማመዷን በማየት ከግቢባት ወዲህ ፣ “እታእም ብላችሁ መሰሊያ አደረጋችሁኝ አደል” ብላ ዳግመኛ አልለበሰችላቸውም ።

ቤትዮዋ ግን ፣ የላቀችን ቀና—ቀና እና የወጣቶቹን ጠጋ—ጠጋ እምብዛም አልወደዱት ። አስከትለዋት ወደ ዘመድ ቤትና ቤተክርስቲያን በሔዱ ቁጥር አብዛኛው ሰው እሷን ብቻ ነጥሎ የሚያይ ስለ መሰላቸው ፣ “አንድ ላይ መዞር አበዛን ፣ ሰውስ ምን ይለን” በማለት መታጀቡን እየወደዱ አስቀሯት ።

እሷም ሰውንና ከተማውን ማየት ደስ ቢላትም ፣ በወጡ ቁጥር እንደ ውሻ ተከትላ መጓዙን ጠልታው ስለነበር ፣ “ነይ ተከተይኝ ስለምትሉኝ ነውቴ ምን አረግ እሔዳለሁ” በማለት እቤቷ ክትት አለች ።

የቤትዮዋ በሰበብ ባስባቡ ወጣ—ወጣ ማለትና የላቀች ተለይቶ መቅረት ከሩቅ ሳይሆን ከዚያው ከቅርቡ ፣ በአድናቆትና በጉጉት ለሚከታተሏት የወንድ ዐይን በቂ ጊዜና ምቹ አካባቢ ፈጠረለት ። የሚገርመው ግን ፣ ከማንኛውም ጉዳይ ይልቅ የዚህ ዓይነቱ ነገር ፈጥኖ የመታወቅና የመጠርጠር ልዩ ባሕሪ ያለበት ይመስል፣ ቤትዮዋ ቶሎ ደረሱበት ። ማንነቱን ቀስ ብለው ሲያጣሩ ግን ፣ ተቆጥተው የማይመልሱትና ፣ ተግደርድረው የማያባርሩት በመሆኑ ፣ “ አብሮ የሚጠቅመኝ እጀ—እርጥብ ከሆነ እኔ ምን አገባኝ ። እስክ ዛሬም እስኪ የታባሽ እያልኩ ስቆጣ መኖሬ ፣ እማይረባ ሰው ላይ እንዳትወድቅ ብዬ ነውቴ ፣ ከእንዲህ ያለው ሰውስ እንዳፈቀደው ፣ ለዚያውስ ብታገኘው አደል ! እሷም ብትሆን እንደ ከተማዎቹ ሠልጠንጠን ያለማለቷ ነውቴ ቤቱ ብር ትመስላለች” ብለው በእስቲ ጉዱን ልይ አይቶ—እንዳላየ ችላ—ገለል አሉ ።

የአቶ ወርቅነህ መዘውር ሚስት ፣ የወ/ሮ መንበረ የእኅት ልጅ፣ ላቀችን ካየበት ዕለት ጀምሮ መለስ ቀለስ አበዛ ። ባያት ቁጥር ውዴታው እየጠና በቀረ ቁጥር 'የቶሎ ቶሎ ሒድ' ስቀቀን ያዘው ።

ምንስ እምባቸው ከተለያዩ ቤቶች ጋር እንዳልዋለና ፣ ሐሳቡና ውዴታውን ሲገልጽ እንዳልኖረ ሁሉ ፣ ከላቀች ጋር ተዋውቆ ለመነጋገር ግን ፣ ኃፍረት ይሁን ፍርሃት ያልለየለት ስሜት ተናነቀው፣ ለጊዜው ። ሆኖም ከማይደርስበት ገደል ላይ ተንጠርጋ የምትታይ ብስል



እንኮይ ሆና አልቀረችበትም ። ዘዴውም መሰላሉም እዚያው ነበር ። በወ/ሮ ደጅ — ይጥኑና በአቶ ወርቅነህ መዘውር ሽምግልና ለመጠቀም ወሰነ ። ተስፋውን እያለመለመ ሲመለከታትም ፣ ቁንጅናዋ ብቻ ሳይሆን ፣ በዜማ ስልት የምትናገራቸው ቃላቷ ፣ አካሏን ጠቅሎ ልቡ ውስጥ ከተተው ።

ወይዘሮ ደጅ—ይጥኑም አዝማሚያው ሁሉ ወለል ብሎ ስለታያቸው ፣ ሲመጣ በፈገግታ አስተናግደው ፣ ሲሔድም 'በተመልሰህ ና' ገጽታ ይሸኙት ጀመር ። እሱም ትሕትናውን አሳምሮ ሻሽና ሽቶ አረቄና ኮኛክ እየያዘ ጉራ ማለት ካመጣ ወዲህ መመላለሱን ወደዱለት ። የስጦታው ዋና መነሾ ለሆነችው ለላቀችም ፣ “እስኪ እንቺ ልጄ ! የእህል ውሃ ነገር አይታወቅም” በማለት ድርሻቸውን እያስቀሩ ከስጦታው አጋሯት ። የኋላ ኋላም በስጦታው ምክንያት ጉዳዩ እንደ ገባት ስላወቁ ፣ አመጣጡን ሁሉ ረጋ ብለው ገለጹላት ። ፈገግ ብላ በዐይኗ መለሰችላቸው ።

# ምዕራፍ ሐያ ዘጠኝ

ቀኛዝማች ፣ የምክር ቤቱን የስብሰባ ደንብና ሥነ—ሥርዓት ፣ አር ፍዶ መግባትን ፣ ለፕሬዚዳንቱና ለዓቃቤ—ጉባዔው ነግሮ በሰበብ ባስባቡ መቅረትን ተላመዱት ። ሁሉም የየራሱን ኑሮ ለመገንባት የሚያደርገውን መደጋገፍና ትንቅንቅ ፣ በውጣ—ውረዱ ወቅት የሚው ጠነጠነውን ብልሃት ፣ አንዱ በሌላው ላይ ተፈናጦ ሲንጠራራና ሲጨ ብጥ የሚፈጸመውን ግፊያና ትርምስ በሚገባ አስተዋሉ ። እሳቸውም ነባር የገጠር ልምዳቸውንና ከአዲስ አበባ ወዳጆቻቸው ያገኙትን ምክር አጣምረው ተቀላቀሉ ። ሆኖም ገና ተደላድለው ሳይቆሙ የገጠር ድግስ ውጣ—ውረድ ጣልቃ ገብቶ አዲሱን ጥረታቸውን እንዳያዳ ክምባቸው በማሰብ ፣ ለአያሌ ዓመታት ያስለመዱትን የኅዳር ሚካኤ ልን ድግስ በሥራ ብዛት ምክንያት ወደ ሰኔ ማዛወራቸውን ለንስሐ አባታቸው በደብዳቤ ገልጸው ነበር ።

ሆኖም ሐሳቤን የሚፃረር ነገር ይመጣል ብለው እንኳ ሳይጠራ ጠሩ ፣ መምሬ ተክለ ጊዮርጊስ የሚካኤልን ጉዳይ አስቀድመው ፣ እን ጦጦ ማርያምን አነግሣለሁ በሚል ምክንያት ሳይታሰቡ ከአባ ተክለ አብ ጋር ከተፍ አሉ ።

“የለም ፣ የለም ” አሉ አባ ተክለአብ ። “እግዚአብሔርንና ቅዱሳን መላዕክትን መሸንገል አይገባም ። በዕድሜያችሁ ላይ አንዲት ደቂቃ መጨመርና መቀነስ አትችሉም ማለቱ ለምንድን ነው? እኛ ለእሱ ቀጠሮ ሰጪዎች መሆን እንደማንችል ሲገልጽልን እኮ ነው” አሉ።

“ምን ቢያቀብጠኝ! ሽንገላኮ አይደለም አባቴ ፣ ቀኑን መለወጤ፣ ድግሱን በሰፊው ለማዘጋጀትና ስለቴን በወጉ አጠናቅቄ ለማግባት ነው” አሉ ቀኛዝማች ። በልባቸው ግን ፣ ‘እሱ በሕልሜ እንኳ ያልተ ቆጣኝን ፣ የነኝህ ምን ይባላል’ እያሉ ። በቀላሉ እንደማይላቀቁ ግን ገብቷቸዋል ።

“እማይሆነውን! ኧረ በሊቀ—መላኩ! እኛ እንዳስፈለገን የምንል ከሆነማ ፣ ምኑን ለጌታ ተገዛነው? ስለትን በዕለቱ ፣ ጸሎትን በሰዓቱ ነው ። የኅዳር ሚካኤሉን ለሰኔ ፣ የጥር ሥላሴን ለሐምሌ ማዛወር የኛ ሥልጣን አይደለም ። የተለመደው ጊዜ በመተላለፉ ፣ ስንኳንና ቅዱስ ሚካኤልን እኛንም አሳዝኖናል ። የተቸገረና ሐሳቡ ያልተፈጸመለት ሰው ፣ ጉዳዩን

በንጹሕ ልብ ለካህን ነግሮ ስለትና ድግስ ቢዘገይ ምንም አይደለም ። የእርስዎ ግን ፣ ሐሳብዎ ተሟልቶና ጸሎትዎ ተሳክቶ እያለ ፣ ሊቀ—መላኩ ምን አጠፉና ቀጠሮ ይሰጠዋል? ስጠ እንጂ ስጡኝ እኮ አላለም ። አሁንም የሚጠብሉት ረድኤቱና በረከቱ እንዳይለይዎ ነው ። እሱማ ምን አጥቶ ፣ 'መሪዬና ተስፋዬ አንተው ነህ' እያሉ የሚገባውን በማድረግ ፈንታ ፣ ተራዳኢውን ማስቀየም ተገቢ አይደለም" አሉ አባ ተክለአብ ።

መምሬ ተክለ ጊዮርጊስ ፣ በነገረ—ሃይማኖት ክርክር ተሟግተው የማይቻነቶትን ግትሩን አባ ተክለአብን ይዘው በመምጣታቸው ደስ ብሏቸዋል ። ቀኛዝማች ፣ "ገና ሥራ ከመጀመራችን" ከማለታቸው ፣

"እሱኮ ማንም ጥብቅና እንዲቆምለት አይፈልግም ። እኔም ኢምንት ፍጡር ነኝ ። ካልመሰለው ሁሉንም ያውቅበታል ። ይሰጠውና ይነሳው እያጣም! የዘረጋውን የረድኤት እጁን እንዲያጥፈው ማድረግ አይገባም ። 'ሰብእሰ እንዘ ክቡር ውእቱ ኢያእመረ' — 'ሰው እያወቀ እንዳላዋቂ ሆነ' ተብሏል ። እፍኦ ለስጠ ቸር ጌታ አደርጋለሁ ያሉትን በዚያው ባሉት ቀን ማድረግ ተገቢ ነበር ። እንኳንና ላንዱ ለውቢት ሚካኤል ፣ ለሌሎቹ ሁሉ ቢደገስስ ምን ጠፍቶ ነው" አሉ አባ ተክለ አብቀኛዝማች ቶሎ እጅ ባለመስጠታቸው እየተናደዱ ።

"የጎዳሩም ሆነ የሰኔው ምንም ልዩነት የለውም ። ልማድ ሆነና—" እንዳሉ ቀኛዝማች ፣

"ለሱማ ልዩነት የለውም ፣ አገሬውስ ምን ይላል ፣ ዘንድሮ የልባቸው ሲደርስ ጊዜ እሱንም ችላ አሉት — —ነው የሚሉን" አሉ ንስሐ አባታቸው ፣ 'እኔንስ ለምደውኛል በጀም አይሉኝ' በሚል ስሜት ።

"እኔ በሌለሁበት ፣ ይኸ አነሰ ይኸ ጎደለ እያለ ማን የልቤን ያደርሰዋል ብዬ ነዋ!"

"ኧረ በሥላሴዎች! ያ ሁሉ የሰው መንጋ የት ሔደ? በብጣሽ ወረቀት 'ይኸን—ይኸን አሰናዱ' ብለው ካዘዙ ፣ አሁን ያ ሁሉ ሰው ጉራ አይገፋምን? እንኳንና ታዛችኋል ተብለው ይቅርና እዚያው እቤት ላሉትም ቢነግሩዋቸው ይበቃል ። በዚህ ላይ የቤቱ ምሰሶ ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱ አለች ። እርስዎም ከቻሉ የከተራ ዕለት ፣ ካልሆነም የጥምቀት ዕለት ከገቡ ይበቃል ። እኔ እንግዲህ ጨርሻለሁ" ብለው ወደ መምሬ ተክለ ጊዮርጊስ አዩ ።

"እኔም ከዚህ በላይ እምለው የለኝ" አሉ ንስሐ አባታቸው ።

ቀኛዝማች ሁለቱ ሰዎች ተስማምተው የወሰኑትን የጥር ቃና ዘገሊላ ሚካኤልን ድግስ ወደ ሰኔ ይሸጋገር ብሎ በግትርነት መከራከር



አስፈላጊ ስላልመሰላቸው ፣ ከጥቂት ዝምታ በኋላ መስማማታቸውን ሲገልጹ ፣ የሰዎቹ ልብ በደስታ ወረበ ። መምሬ ተክለ ጊዮርጊስ ወዲያው አሳረጉ ። ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱ ግን በጣም ተከፉ ። ምግብና መጠጥ ሲያስቀርቡም ፣ "አፈር ብሉ እቴ ፣ አፈር ያስበላሁ! ይዘሁልኝ ኑ ያልኳቸው ይመስል ፣ የማንንም ዘባሪቆ ይዘው መጥተው ፣ ያረበርቡብኛል" በማለት ውስጥ—ውስጡን ተነጫነጩ ። ደህና በማያውቃቸውና በማያውቁት አካባቢ ተሰውረው ከአሚታና ካሉባልታ እፎይ ብለው የሰነበቱት ሴትዮ ፣ እንደገና ደግሞ ከአፈማና ከምንዳዬ ፣ ከአስካደችና ከልኬለሽ ጋር ፣ በስውርና በግልጽ መፋጠጡን ስለ ጠሉት ፣ ሰዎቹን ከፋኛ ጠሏቸው ። ድግሱን ለማዘጋጀትም ቢያንስ ከአንድ ወር በፊት መድረስና ፣ በኋላም ያንኑ ያህል እንደሚቆዩ ስለሚያውቁ በንዴት ጨሱ ።

የፈሩትም የጠሉትም አልቀረ ፣ አዲስ ልብስና መጠምጠሚያ ካስገዙት ከመምሬ ተክለ ጊዮርጊስ ጋር ታኅሣሥ ፫ ቀን ማታ ማጀቴ ገብተው አደሩ ። በማግሥቱም ጠለስለስ እንዳለ ፣ ቸርነት ተልከበት ባመጣላቸው በቅሎ ተቀምጠው ሣር—አምባ ሲደርሱ የገዛ ቤታቸውን ከሩቁ ጠሉት ። ከበቅሎ ወርደው ባለፉበት መንገድ ያገኟቸው ሰዎች ሁሉ ፣ እኩዮቻቸው ጉንጫቸውን ፣ ልጅ—ልጅ እግሮቹ ጫማና ጉልበታቸውን እየሳሙ ፣ ከፊትና ከኋላ አጅበዋቸው ከግቢያቸው ሲደርሱ ልኬለሽና ምንዳዬ ጫጫታውን ሰምተው ከቤት ወጡ ።

ልኬለሽ ገሥግሣ ጉልበታቸውን ልትስም ስትል አፈፍ አድርገው አነሡና አገላብጠው ሳሟት ። ምንዳዬም ቂምና ጥላቻውን ይሉኝታ ሰንከሉለት ፣ ውስጥ—ውስጡን እልህና ሲቃ እየተናነቀው ፣ ከባለቤቱ ቀጥሎ ጉልበታቸውን ለመሳም ጎንበስ ሲል ፣ እሱንም እንደሷ ፈጠን ብለው ሳሙት ። 'የንከሻ ያክል ነው' አለ በልቡ ።

አዳራሹ በር ጋ ሲደርሱ አረጋሽ ጉልበታቸውን ስማ ቀና ስትል በሆዳቸው 'ቅርናታም ! የሰው ቅርናታም !' እያሉ ሳሟት ። ሸዋርካብሽ በሌለችበት ቤት ፣ አረጋሽ ብቻዋን እንደልቧ ፣ 'በገዛ እኅቴ ቤት' እያለች ለወደደችው ስጥታ ፣ ላልመሰላት ነሥታ በመቀመጧ ፣ ገና ከመግባታቸው በክፉ ዐይን አዩዋት ። አገልግሉ ባስከተለው ጣጣ ምክንያት ደንግጠውና አስደንግጠው ፣ "በይ ደሞ ባንዱ እጅ ሰበብ ትሆኚና ነገር ታመጪብኛለሽ ፣ የሆነው እስቲሆንና አንዱ እስቲለይ እዚያው በሩቁ ሆነሽ እቴዋ በይኝ ። አዝማሚያቸውን አይቼ አስጠራሻለሁ" በማለት ሸዋርካብሽን ቀደም ብለው በዘዴ ወደ ደጋው ስደዋት ስለነበር አልነበረችም ። የሷ መሔድ ግን ጥርጣሬና አሉባልታውን አባባሰው እንጂ አልቀነሰውም ።

የጎረቤት ሰዎች አንዱ ላንዱ እየነገረ ፣ ውሎታ ያለበትም የሌለበትም ጠላውን በገንቦ እያስያዘ ሔደ ። ያልነበራቸውም አልቀሩ ።

በእከልና 'ተንግዲህስ መሽቷል ነገ ሒጄ እጠይአቸዋለሁ' ብለው ከቀሩት በስተቀር ፣ ሁሉም እየበላና እየጠጣ ሲደሰት ፣ እህል ውሃው እየተናነቀ ያስቸገራት አስካደችን ብቻ ነበር ። ምንዳዩና ልኬለሽ ግን በየአቅራቢያቸው ከነበሩት ሰዎች ጋር እንደልብ ሲያወሩ አመሹ ።

*   *   *   *

የጥር ሚካኤል ዝግጅት በሰፊው ተጀመረ ። እርም—አይቀሬ የተ ካከለትን ደብዳቤ በተደጋጋሚ አስነብቦ ትዕዛዝና አደራውን በቃሉ አጥንቶታል ። ከቤት ውጭ የሚመጣው አስፈላጊ ነገር ሁሉ ፣ በየዕ ለቱ ከያቅጣጫው ሲጎርፍ ፣ ሁሉም ከተነገረና ከታዘዘው በላይ ፣ አንዳ ንዱ ወደ ፣ አብዛኛው ተገዶ ጭና ከተፍ ሆነ ።

አስካደች ፣ በወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ላይ ጥርሷን ነክሳ ፣ በምንዳዩ ላይ የጥላቻ ቀስቷን እንደ ቀሰተች የጥር ሚካኤል ቶሎ ደርሶላት ቀኛዝማች ምንዳዩን ወደ አዲስ አበባ ወስደው ደብዛውን እንዲያጠ ፉላት ለማር—አምባዋ ደብረ—ወርቅ ማርያም ተስላለች ።

ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱ በበኩላቸው ፣ ምንዳዩ ከነእርም—አይ ቀሬ ጋር ተፍ ተፍ እያለ ስለ ድግሱ ሁኔታ ሐሳብ ሲሰጥና ሥራ ሲያ ደላድል በማየታቸው ተናደዱ ። ቀኛዝማች ወደ አዲስ አበባ ይወስዱ ታል የሚለውንም ሐሳብ አስታውሰው ፣ በታማኝነት ስም እዚሁ እንዲ ቀር ለማስደረግ ከነእርም—አይቀሬ ጋር መመሳጠር ጀመሩ ። እርም— አይቀሬ ግን ፣ ሴትዮዋን መቃወም ፈርቶ እንጂ ምንዳዩን የመሰለ የቅርብ ታማኝ ተፎካካሪ እንዲጋፋው አይፈልግም ።



## ምዕራፍ ሠላሳ

ቀኛዝማች ፣ የሚካኤል ድግስ ወደ ሰኔ እንዲተላለፍ ምክንያት ተንትነው ያልተከራከሩትን ያህል ፣ የኋላ—ኋላ ደግሞ ሐሳባቸውን ለውጠው ተደሰቱ ። ከወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ ጋ እንደልብ እየተዝናኑ መንፈላሰሱንና ያላንዳች ሥጋት ወደ ቤታቸው እየወሰዱ አውሎ ማሳ ደሩን ሥራዩ ብለው ተያያዙት ።

"ለራስሁና ለሚስትሁማ ታኡበታለሁ ፣ እኔ ነኝ ፣ እኔ ተላሊቷ ፣ እንዳሮጌ ቀርበቦ የትም የተጣልኩት" አሉ የቀኛዝማችን መኖሪያ እያዩ ።

"አይ ያንቺ ነገር! ኧረ ተይ የእግዚሐርን ዐይን አትንጉጪ ? እሷ ማን አላት ? አንቺ እንዴት እንዴት ያሉ ዘመዶች አሉሽ ፣ እንኳን ለራስሽ ለሌላ ትተርፊያለሽ ። በይ በይ ባይሷትና እልሀ ባይዛት ኖሮ እንዲች ብላ አትመጣም ነበር ። እሷ ጣራና ግድግዳው ምኗም አይደል" በማለት ሲያኩራሯቸው ስሜታቸው ገርገብ አለ ።

የወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ እንደልብ ውሎ መግባትና ማደር ፣ ለሞገስ አምባቸው አፍላ ፍቅር በቂ ጊዜ በማስገኘቱ ፣ እሱም ሁኔታውን እያዩ መዝናናቱን ቀጠለ ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህም ለምን በየቀኑ እንደሚመ ላለስ መላ—የአቶ ወርቅነህ ቤተሰብ ዐውቋል ። አቶ ወርቅነህና ባለቤ ታቸው ወይዘሮ መንበረ ተፈራ ፣ ሞገስ ሁለት ጊዜ ሚስት አግብቶ በመፋታቱና ሁለቱም ሚስቶቹ ፣ ገንዘቡን ከስክሰውና ንብረቱን አባክ ነው መቅኖ ስላሳጡት በጣም ያዝኑለታል ። እሱም ሆነ እነርሱ ፣ ለት ዳር የምትሆን አንገተ ሰባራ ከመፈለግ ቦዝነው አያውቁም ። ዛሬ ግን መለሎዋና መልከ — መልካሟ ላቀች ተገኔ ባጋጣሚ በመገኘቷ "መበርታት ይኸነዩ ነው" ከማለት በስተቀር ፣ ሰው ናቀ ፣ የጨዋ ግቢ ደፈረ ብሎ የሚቆጣና የሚቀየመው አልነበረም ።

ለወጉና ለቤተ ሰባዊ ክብሩ ያህል እንደ ዐይነ ዐፋር ወጣት በሹልክታ ገብቶ ከላቀች ጋር ሲያወራ ፣ አንገቷን ጥምዝዝ አድርጋ ታቀረቅራለች ። አይከፋውም ። እንዲያውም ነፍስ የገባበት ኑሮው ደህና ነፍስ የሚዘራበት ወቅት እንደ ተቃረበ ታየው ።

"ምን ላርግልሽ ?" ይላታል ወይ ከንፈሯን ወይ ጣቶቿን እየደባበሰ ።

"እኔ ምን አእልኋለሁ! ኧረ ወሒዱልኝ ወንድሜ! እኔ ወጣ ከማለቴ ቤቱን ስትዳራበት ዋለች ታስብሉኛለሁ ። ደሞ ደህና ተነ ስሜ እንዳልከርምበት" ብላ ገለል ትላለች ።

"ማነው እንደሱ እሚልሽ?" ይላታል ዐይን—ዐይኗን እያየ ።

"እቴዋ!" ትለዋለች እንዳቀረቀረች ።

"እባቸውስ ምንም አይሉ ። ምነው እዚሁ እያሉስ እመጣ የለም እንዴ? እንዲያውም በጣም ነው ደስ የሚላቸው ። የማያውቁ አይም ሰልሽ፣ ያውቃሉ ። ይልቅ ምን ሳርግልሽ?"

ያላወቀች ብትመስልም፣ የሞገስን ፍላጐትና ከአቶ ወርቅነህ መዘውር ጋር ያለውን ግንኙነት ሁሉ ዐውቃለች ።

ዝም ስለምትል፣ "ምነው ዝም አልሽ? ንገሪኝ እንጂ ምን ሳርግልሽ?"

"እኔ ምኑን አእልኋለሁ? አንቱ ደስ እሚልሁን፣——እኔ እንደሁ አሁንም ልቤን ፍሪያት ፍሪያት ብሎታል ። ሰው እኮ አፉና ሆዱ አንድ አዶለም ። አንቱ የሳቸውን ጠባይ የት ታኡታለሁ? በያ ላይ ደሞ ዘመዶቻቸው አሰማምረው ይነግሯቸውና ጉድ ያፈላሉ ።"

"ግድ የለሽም አትፍሪ! ሁሉም ያውቃሉ ።"

"ምኑን?" አለች ደንግጣ ።

"እኔ እዚህ እንደምመጣ ነዋ!"

"እ — እ!" አለች በመረጋጋት ።

"እኔ እኮ ትልቅ ነው አሳቤ" አለ እንዴት ብሎ እንደሚያስረዳት ግራ ገቧቶት ። "ይልቅ ለማይጠቅም ጉዳይ መስሎሽ አትጠራጠሪ፣ ሴት ልጅ ደሞ በቁም—ነገር ስትለመን ይህን ያክል አትጨክንም" አለ አፉ እንዳመጣ ።

"ፈርቸሁ ነውዴ ጥብአ" እኮ ነኝ፣ ወንድ ሔጅም አላእ!" አለች አቀርቅራ ።

"እኔ መቼ ወጣኝ?" አለ፣ እየደነገጠም እየተደሰተም ።

"ምን ልበል ኋላ? ነገርሁ ሁላ ————"

"የምትፈልጊው ነገር ካለ፣ ልግዛልሽ ነው ያልኩሽ ። ሌላ ነገርማ" ብሎ ሣቅ አለ ።



ፊቷ ቢቀላም ስሜቷ ረገበ ። "እያ እኛ አገር እምንፈልገው፣ እየሀ እናንተ አገር የለ?"

"እስኪ ምን ምን እንደሆነ ንገሪኝ?" አለ ፈገግ ብሎ ጣቷን እያፍተለተለ ።

"ብነግርሁ ምን መላ አለው?"

"እናንተ ጋ የምታጌጡት በምንና በምን ነውኣ?"

"ምን ያረግልኋል? አምባር፣ አልቦ፣ መስቀል፣ ድምብል ——" ብላ ልትቀጥል ስትል፣

"ይኸማ ቀላል ነው ። ከዚያ የበለጠ ሞልቷል ።"

"አይ አንቱዬ! ቢበላጥ ምን ያረጋል? እንዲያው አለኝ ለማለት ታልሆነ የት ኮኚ ላጌጥበት? ሰው እንደልቡ ቲኖር ነው ላጊጥ ልኳኳል እሚለው" ብላ እምቢታዋን ሳይሆን ፍርሃቷን ገለጸችለት ።

ከዋል አደርና ከምልልስ ብዛትም፣ ፍርሃትና ኃፍረቷ እየቀነሰ፣ ካንገቷ ቀና፣ ከፊቷ ፈገግ — ፈካ እያለች ለጥያቄዎቹና ለአስተያየቱ መልስ መስጠት ጀመረች ።

የወሬው ሰዓት እየረዘመና መደባበሱም እየጨመረ በሔደ ቁጥር፣ ጠጋ ብላ ትቀመጥና፣ ሮመር ሰዓቱን፣ ባለ አክሱም ሐውልት የወርቅ ቀለበቱን፣ ባለ ልሙጥ መስቀል ሐብሉን፣ ልብስና ጫማውን መመልከት ጀመረች ።

ቀስ በቀስም ንግግሩ እየሳባትና አቀራረቡ እያስደሰታት መንፈሷ ወዶት፣ አካሏ በፍትወት ነደደ ። በተከፈተው የልቧ በር ሞገስ ሰተት ብሎ ገባ ።

ጉዳዩ እየሠመረለት መሔዱን እንደ ተረዳም፣ ከመቃጠል መጠቃለል ብሎ መላ ፍላጐቱን ለአቶ ወርቅነህ መዘውርና ለባለቤታቸው ገለጸላቸው ።

ምንም እንኳ ጉዳዩ በቀላሉ እንደሚፈጸም ቢያውቁም፣ አቶ ወርቅነህ መዘውር ላዲስ ጥቅም በር ከፋች የሚሆን የሽምግልና ውለታ ስለሚያገኙ፣ ባለቤታቸውም እንደ ልጃቸው ላሳደጉት ለሞገስ የምትስማማ፣ ያውም በሳቸው አባባል፣ "ባሏ እንዳላት ሆና የምታድር አንገተ ሰባራ ያገር ቤት ልጅ" በመገኘቷ በጣም ደስ ስላላቸው፣ ጉዳዩን እንደ ቤተሰባዊ ምክክር አስመስለው ለወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ ነገሯቸው ።

የዝምድናቸውን ደረጃና አስተዳደጓን ረጋ ብለው በጉራ እየኳኳሉ ከተናገሩ በኋላ፣ "አንድ አግብታ ፈታለይ" አሉ ሴትዮዋ ።

"በምን ምክንያት ነበር የተፋታቺውን? ቆንጆ ሴት'ኮ አትታመንም ። የዚያ አገር ሰዎች ሴቱም ወንዱም ቀናተኞች ናቸው" አሉ አቶ ወርቅነህ ።

"እሷ እቴ! የቆንጆ እመቤት ነች ። በዚህ በዚህስ አትጠረጠርም ። የሠራባትም አትመስል ። የዚህ ዓመል ቢኖራትማ ስንቱ ነበር ይረግጠው እስቲጠፋው ያንዣበበው ። ባሏ የሚረባ ሰው አልነበረም መሰል፣ አይታና ታዝባ ንቃው ምንጥቅ አለች ።"

"እንዴት?"

"ምን ታርገው ? ወይ በርትቶ ካላረሰ፣ ወይ ከቆላ ደጋ ብሎ እንደሚነግዱት ካልነገደ፣ ወጣ ገባ እያለ ዐይንና ከናፍሯን ቢያየት ምን ያረግላታል? ባንዲት ቀሚስ ተጣብቃ እስከ መቼ፣ ጥጡም ቢሆን ተሸምቶ ነው ። ወይ ቁና ባኤላ ወይ ቁና ገብስ ታልሰጡ፣ አንድ ነጥር ጥጥ አይገኝም ። እዚያው ቢጤህን ፈልግ ብላ ጥላለት ውልቅ አለቻ ።"

"እ! ኮብልላ ነዋ ?"

"ኧረ እሷ እቴ! —— ምን አስኮበለላት!"

"አሁንም ከነፈርማዋ ነች ማለት ነው ?"

"እሱማ እንገራግሮ ነበር፣ በጭቃ ሹም ተገዶ ነው የቀደደላት።"

"በኋላስ ዝም አለ ? ልተናኮልም አላለ ?"

"ኧረ ንቪ ሰዎች! እተናኮላለሁ ቢል ማባቱ ይለቀዋል ? እሰና ዘራለሁ ካለም፣ ከሰማይ ወፍ የሚያረግፉ ወንድሞች አሏት ። እኔም ጋ የተጠጋችው እሷው ትሻለኛለች በማለትና ቀኛማችንም ትልእ— ትንሹ ስለሚያከብራቸው፣ ለክብርቱ ብላ ነወዪ ዘመድስ ሞልቷታል" ብለው ቆጠብ ያለ ሣቅ ሣቁ ። ጉዳዩ ገፍቶ መምጣቱ ገብቷቸዋል ።

"የጨዋታችንን አዝማሚያ ሳታውቂው አልቀረሽም" አሉ አቶ ወርቅነህ ባለቤታቸውንና ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑን እያዩ ። "ወጣ—ገባ ሲል ጉዳዩ ገብቶሽ ይሆናል ። የእህል ውሃ ነገር አይታወቅም ። ሰው ውሃ አጣጩን አያጣም ። ሁለቱም አላሰቡት ። ያንዳንዱ ሰው ዕድል ገና እንጥስ ሲል ነው የሚያምርለት ። እንደምታዪው ስንትና ስንት ሥልጡንና የተማሩ የከተማ ሴቶች ሞልተው ተርፈው ሳለ፣ ገና ምኑንም ምኑንም ያላየችው ባላገር እንዲህ ያለ ድንቅ ዕድል ሲገጥማት በጣም ደስ ይላል ። ቀን ይውጣልሽ ሲላት ነው ። ዐይን የሚያሹበት ቤት



አይምሰልሽ ። ካወቀችበትና ነቃ—ነቃ ካለች ሰው ሆነች ማለት ነው ። እኔ ገና መጀመሪያ ሲነግረኝ፣ የሚቀልድ መስሎኝ ነበር ። ይቺ ገና የምትበላው ብዙ እንጀራ አላት ። 'አትሩጥ አንጋጥ' ይሉሻል እንዲህ ነው ። እኔ ባልወልደውም የልጂ ያህል ነው" አሉ ።

ሦስቱም ምሳ በልተው፣ በእግረ—ረጃጅም ሆደ ሰፊና አፈ— ጠባብ መለኪያ ኮኛክ ሲጠጡ፣ "ልጅቱም ብትሆን የምታስመሰግን ነች" አሉ ወ/ሮ ደጅ— ይጥኑ፣ ፉት ያሉትን ኮኛክ ውጠው ። "በያ ላይ ጥፍፍ ያለች የሰው ልጅ ነች ። እስቲ ቆይ ዋል አደር በሉና ትታዘቡኛላችሁ፣ አሁን እንኳ ከምንየዋ የናንተን ልጆች ሥልጧኔ ልቅም አርጋ ይዛዋለች። ለያውም እኔ ፊት እየነሣኋት ። ጥኢት ሰንበትበት ስትልማ ማንም አይታከላት ። ያየችው ሁሉ አይጠፋትም ። ለቀም ነው ። አለመማሯን አትዩ ። ልበ—ብሩህ ናት ። ቀሚስ ያጠለቀችና መቀነት ያዞረች ሁሉ ሴት አይደለችም ። ይቺ እኮ ካልመሰላት ወንዱ ሁሉ ወንድ አይመስላትም ። እንዲህ የዋዛ፣ ነብር ነች! ይኸ ሞገስ ታዲያ እኔ ጋ እየመጣ፣ ወጣ—ገባ ሲል፣ ጠባዋን ሳያቅ ይናገራትና 'የሰው ሰው ታዋርድብኝ ይሆን ጌታዬ' እያልኩ ፍርያቴ አይጣል ነበር" ብለው ድጋሚ የተቀዳላቸውን ኮኛክ ጨለጡ ።

"እውነትም ልበ ቅን ነች ። ከስንት አንድ ነች እንዲህ በክብርት ደህና ባል የምታገኝ፣ የተማረ የከተማ ሰው የባላገር ሴት አይፈልግም ። ደስ ካለችውም ላንድና ለሁለት ቀን ጉዳዩን ፈጽሞ ዞር በይ ይላታል" ብለው ወ/ሮ መንበረ ከሣቁ በኋላ፣ "ዘመዴ በመሆኑ ላሰማምረው ብዬ ሳይሆን፣ እንዲህ እንደ ዘመኑ ሰው አይምሰልሁ ። የዘመኑ ሰው ስንትና ስንት ዐመል አለበት መሰለሁ ? አብሶማ የከተማ ወንዶች! እንቱም እያደር ትታዘቡኛለሁ ። እንግዲህ ነገሩን ታነሣነው አይቀር፣ ግልጥልጥ አርገን ነው መነጋገር" አሉ ወደ ባለቤታቸው እያዩ ። ባልዬው 'እውነትሽን ነው' ለማለት ራሳቸውን ሽቅብ ቁልቁል ነቀነቁ ።

"ሁለተዬ አግብቶ ፈቷል፣ ይኸነዬ የትናየት በደረሰ! ባያድለው ነው ። ያዲሳባ ሴቶች ምናቸውም፣ ምናቸውም አይታመን ። እየዛቁ ቢሰጧቸው፣ በጎን ይቆነጥራሉ——" ብለው ንግግራቸውን ሳይጨርሱ፣

"ይቺ አፏም ላይ ማር አይሚሚባት፣ አትጠረጠጠርም ፣ ለዚህስ እኔ አለሁ ። ጥኢትም ቅር የሚለኝ ያው ኃይለኝነቷ ነውዪ፣ በስለትም አትገኝ ። በያላይ ባለሙያ ነች ። ወጡን የሠራችው፣ ጠላውን የጠመኧችው፣ እንጀራውን የጋገረችው እንደሁ —— ኧረ ተዉኝ እቴ! እኔማ ጥሎብኝ ስወዳት! ስንቷ እግሬ ላይ ስትነጠፍ፣ እሷን ይገፑ መምጣቴ በጠባዋና በሙያዋ ነው ። በየህ ላይ ወዲያ — ወዲህ ወለም—ዘለም

የለም ፡፡ እኔ ካለ ነገሬ ዐይነ—ቀላዋጭ ሰው አልወድም’’ በማለት አቋርጠው ተናገሩ ፡፡

“እኛስ ይሁን ይሁን ተባባልን ፤ እሷስ ምን እምትል ይመስል ኋል?’’ አሉ ወ/ሮ መንበረ ፡፡

“እሷ እንዲች ብላ ተኔ አፍ አትወጣም ፤ እዬ ጉድ እቴ! እማጋ ብላ የመጣች መሰለሁ? ይልቅዬ ለዘመዶቿ ስልህባቸው ደስ እንዲለኝ፤ እሷም ልቧ እንዲረጋላት ፤ ያው እናንተው ታኡበታላችሁ ወረኤት ቢጤ እንድታጣጥፏቸው ፡፡’’

“ቀኛዝማችስ ምን ይላሉ? አልነገርኳቸውም እኮ?’’ አሉ አቶ ወርቅነህ ፡፡

“እሳቸው ምንም አይሉ ፡፡ ዋናይቱ እኔ —— ነጋ ጠባ አደራሽን እንዳታስቀይሚያት ፤ የበደሉት ያገር ሰው መግቢያ ያሳጣል ፤ ክፉ ነገር አይውጣሽ ነው እሚሉኝ ፤ ይኸንማ ሲሰሙ በጣም ነው ደስ የሚላቸው ፡፡ የዘመዶቿም ውለታ አለባቸውኮ!’’ ብለው ደመደሙ ፡፡

በሦስቱም ፊት ላይ ሙሉ ፈገግታ ሰፈነ ፡፡ እነ አቶ ወርቅነህ ለብ እስኪላቸው ጠጥተው ወደ ቤታቸው ሔዱ ፡፡ ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ከምሽቱ ሦስት ሰዓት አካባቢ ከእንቅልፋቸው ሲነቁ ፤ የነጋ እንጂ ገና ምሽት አልመሰላቸውም ነበር ፡፡ ያን ለት ማታ ለመጀመሪያ ጊዜ ከላቀች ጋር አብረው ራት ስለበሉ ፤ “ዛሬ ምን ታያቸው እኚህ ሴትዮ’’ አለች ተገርማ ፡፡

ከራት በኋላ አልጋቸው ላይ ዘርፈጥ ብለው ፤ ከፊት ለፊታቸው የጥቅምት ጥንቅሽ መስላ የቆመችውን ላቀችን ፤ በትዕዛዝ አንደበትና የእርሷንም ዕድለኛነት በመግለጽ እንዴት ያለ ጨዋ ባል እንደመጣ ላት ፤ አሳምረውና አጣፍጠው ረጋ ባለ ስሜት ነገሯት ፡፡

የልቧን በልቧ ይዛ ፤ “አንቱ እንዳልኩ ፤ እኔ ምን ዐቃለሁ’’ አለች አንገቷን ሰበር አድርጋ ፡፡

“እኔማ ሸጋ አማች ሲመጣልኝ ምን እላለሁ ፤ እሺ ነዋ!’’ አሏት እየሣቁ ፡፡ ፈገግ ብላ አየቻቸው ፡፡ መልስ መስጠቷ ነበር ፡፡

ውሎ ሳያድር ጉዳዩ ለቀኛዝማች ተነገራቸው ፡፡ አጅሬም በምርጫ ውድድር ወቅት ዘመዶቿ ለዋሉላቸው ውለታ ጥሩ የማካካሻ ዘዴ በማግ ኘታቸው ተደስተው ፤ ከአቶ ወርቅነህ መዘውር ጋር በመመካከር ፤ ላቀች ተገኔና ሞገስ አምባቸው የሚጋቡበት ጊዜ ተወሰነ ፡፡



## ምዕራፍ ሠላሳ አንድ

የአንቃሩ ውቢት ሚካኤል ድግስ ፤ በኑሮ ችግር በተመገዙ ፤ ዐመድ መስለው የቆሙበትን አፈር በተጋዙ ፤ ጉልበታቸው በርካሽ በሚዘረፍ ፊተ—ጨምዳዳ ፤ እጀ ቆርፋዳ ፤ ቅንና ገራገር ሰዎች ሌት ተቀን እየተሠራ አስፈላጊው ነገር ሁሉ ተሰናዳ ፡፡ በተለይማ ሴቶቹ እንደ አጋሰስ ተጭነው ፤ እንደ እርሻ በሬ ለፍተዋል ፡፡

ቀኛዝማች ፤ በወዲያኛው ዓለም ጸጋ ጽድቅ ተጎናጽፈውና ከፀሐይ ሰባት እጅ አብርተው ለዘለ—ዓለም ሊኖሩበት እያለሙ ፤ የሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አጥር ፤ በምድረ—ድኃ ጉልበት ልምጭ እንዳያሾልክ ተደርጎ ታጠረ ፡፡

የድግሱ ጋን ከብ ዝርግ ከንፈር ፤ በከርከርም ገልና በድስት እፊያ እየተመረገ ፤ ጀሮና ጆሮው እየተገናኘ ፤ ካዳራሾቹ ውስጥና ውጪ ጥግ—ጥጉን በጥንድና በሦስትዮሽ ረድፍ ተገጥግጧል ፡፡ ጎላና በገ—ፈጁ ድስት ፤ ከያለበት ተሰብስቦ ፤ ለወጥ መሥሪያ በተዘጋጀው አነስተኛ ዳስ ውስጥ ፤ የዐመድና የጥቀርሻ ብናኙን ለብሶ ፤ ከፊሉ ባለ ጉትያ የእፊያ ቆቡን ደፍቶ የጉልቻ ላይ አሳሩን ይጠባበቃል ፡፡

ምድረ—ግቢው ፤ እንደ አውድማ ተጠርጎና ተለቅልቆ ፤ ባራት ረድፍ የተተከሉት ወፍራምና ምሰሶ አከል ባላዎች ወራጆቻቸውን ተሸ ክመው ፤ ሙሉ ዳስ ለመሆን የእርጥብ ጨፈቃ ድራቢ ይጠባበቃሉ ፡፡ ለመቀመጫነት የተመረጡ ጠፍጣፋ ድንጋዮችም በረድፍ በረድፍ ተደርድረዋል ፡፡

መሰንበቻውን የሣር—አምባና ያካባቢው ጎረምሶችና ሳዱሎች ፤ ጎበዛዝትና ቆነጃጅት ፤ ባለ ውሽሞችና ተከጃጃዮች ፤ ያለው አዳዲ ስና የክቱን ፤ የሌለው ጥቅምቅሙን ይለብሱና ፤ ወንዱ ከመኻል እናቱ ወደፊት ገፋ ብላ አራት ማዕዘን አይሏት ክብ ጎፈሬውን አበ ጥሮ ፤ ቀሪውን ተላጭቶ ወይም ተከርክሞ ፤ ያለው መሐረቡን የሌላው ሻሹን አብቶ ፤ እህል ውሃ እማያሰኝ ዱላውን ይይዝና ፤ ሴቶቹም ሻሻቸ ውን ሸብ ፤ ቀንዳላቸውን በተን ፤ ጎፈሬአቸውን ከምከም ፤ እንሶስላቸ ውን ሞቅ ፤ አንባራቸውን ደረግ ፤ አልቧቸውን አሰር ፤ መስቀልና ድንብ ላቸውን በሐር ቋድ ማተብ ዥርገድ አድርገው በጉጉት የሚጠባበቁት፥

ባጋጣሚና በቀጠሮ የሚገናኙበትን የጥምቀትና የቃና ዘገሊላን በዓል እንጂ የቀኛዝማችን ድግስ አልነበረም ።

እዚያው በዚያው ደግሞ፣ ካህን ለወረብና ለፍትፍቱ፣ ገባር ለመጋዞ መሬቱ ሲል፣ አንዱ ወገን ኀጉቶ፣ ሌላው ወገን ተንገላቶ ይጠባበቃሉ ።

ቀኛዝማች በላይነህ ታፈሰ፣ ጥር 8 ቀን ማር—እምባ እንደሚገቡ ቀደም ብሎ በመታወቁ፣ ቸርነትና ምንዳዬ ሁለት በቅሎዎች ጭነው፣ መምሬ ተክለ ጊዮርጊስና አባ ተክለ አብም ቃላቸው በመከበሩ ተደስተው፣ እንዲሁም ሌሎች ሊቀበሏቸው ወደ ማጀቴ ወረዱ ።

የሔዱት ሰዎች ከገቢያው ምዕራብ ዳርቻ ሰብሰብ ብለው ቆመው ወደ ኮረኮንቻማው አባራማ የመኪና መንገድ አሽቆልቁለው ያያሉ ።

አውቶቡሱ ከሰፊው ግንባሩ ግርጌ ሁለት ትላልቅ ዐይኖቹ የአቧሯ ዐይናራቸውን እንደ ተሸከሙ፣ የደሃ ቤት በር የሚያክል የመስተዋት ፊቱን እያጥበረበረ፣ ጠፍጣፋ አናቱ ላይ የተቆለለው ጓዝ ባረንጓዴ ሸራና ገመድ ተቀርቅቦ፣ ግማታም ጪሱን እያቦለለና እየተንጣጣ፣ እየዘመመና እየቀና፣ ከተሰበሰቡት ሰዎች ፊት ደርሶ ሲቆም፣ ዙሪያውን ከበቡት ። የአብዛኛው ሰው ዐይን ትክታ የመስኮቱን መስተዋት እየነደለ ገባ ።

ቀኛዝማች፣ አቶ ወርቅነህ መዘውርን አስከትለው በፊተኛው በር በኩል ዱብ ሲሉ፣ ሊቀበላቸው የመጣውን የሰው ብዛት በማየት ልባቸው በደስታ፣ መንፈሳቸው በኩራት ተሞላ ። ሰዉ እንደየደረጃው ግዴታውን ፈጽሞ ውዴታውን ከገለጸ በኋላ፣ ልቅደም ያለ ከፊት፣ ልከተል ያለ ከኋላ እየሆነ ጉዞ ተጀመረ ። ሁለቱ በቅሎዎች በጫጩቶች መኻል እንደሚራመዱ ዐውራ ዶሮዎች ጉልተው እየታዩ ወደ ቤታቸው ሲያቀኑ፣ ቀኛዝማች ምንዳዬን ዳግመኛ አነጋገሩት ።

ማር—እምባ እንደ ደረሱም፣ በቤቱ አጠገብ ያለፉለት ካጥሩ ውጪ ቆሞ፣ የወደደ ካንጀቱ፣ ቅር ያለው ካንገቱ፣ ዘመድ—ከባዳ እጅ እየነሳ ተቀበላቸው ። እግቢያቸው አጠገብ ሲደርሱም፣ ሰዉ ለማየትና ለመታየት እየተጋፋ ጠበቃቸው ። ዘውድ—ቀረሽ በዓለ—ንግስ መሰለ ።

እነ ቀኛዝማች ከበቅሎ ወርደው ወደ ግቢ ሲገቡ ታቦት ሸኚ ይመስል ተከትለዋቸው የነበሩት ሰዎች፣ በጠባብ የቅል አንገት እንደሚንቆረቆር ጥሬ አራትና — አምስቱ ባንድ ላይ እየተጋፋ ወደ ውስጥ ገቡ ። እነ ቀኛዝማች አዳራሾቹን አልፈው እልፍኝ እንደገቡ፣ ዘግይቶ የደረሰውና ፈርቶ ያፈገፈገው ደሃና ዘመድ፣ እንዲሁም 'ባልሾምና



ባልመረጥስ ከሳቸው አላንስ' የሚለው ጭምር እንኳን ደህና መጡ በማለት ደስታውን ገልጾ፣ ከፊሉ ወደየቤቱ ሲመለስ፣ የቀረው ደግሞ አዳራሽ ገብቶ ተቀመጠ ።

ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱ፣ ወለልና ግድግዳውን በተደጋጋሚ አበት አስለቅልቀው ባስጸዱት እልፍኝ ውስጥ መደቡና የጠፍር ወንበሮቹ አጎዛ ተነጥፎባቸዋል ። ከአዲስ አበባ የተላኩ ጠረጴዛና አራት ወንበሮችም አንዱን ጥግ ይዘው ተደርድረዋል ።

“እኔ የቆርቆሮ እልፍኝ አይቼም ሰምቼም አላቅ ። እንኳን እልፍኝ እዳስም የገባሁ አይመስለኝ” ብለው ቤትየዋ ስለ ተቃወሙ ጠረጴዛና ወንበሮቹ ማር—ክዳን እልፍኝ እንዲገቡ ተደረገ ። በየዕለቱ ብክቡካ፣ ብርጉድና ወይራ ስለሚጨስበት መዓዛው ደስ ይላል ። አዳራሽና እልፍኝ ውስጥ የሚበሩት ማሾዎች የሚሰጡት ብርሃን ከተለመደው የኩራዝ አቅም ጋር ሲነጻጸር ቀኛዝማች ሁለት ሙሉ ጨረቃዎች ይዘው የገቡ እስከሚመስል ፏ ብሎ ደምቋል ። መስተንግዶው እስከ መንፈቀ ሌሊት ተካሔደ ።

ከአዲስ አበባ የተላከው ሁለት የብረት አልጋና ፍራሽ ቆርቆሮ ቤት ውስጥ ሰሜንና ደቡብ ግዶ ለግዶ፣ ብርድ ልብሱን አንዘርፎ ተነጥፏል ። እንግዳው በስተደቡብ፣ ባለቤትየው በስተሰሜን ተኙ ።

ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ፣ እነ ቀኛዝማችን ሲቀበሏቸው፣ ቀኛዝማች፣ “ትልቅ እንግዳ ይገፎልሽ መጥቻለሁ፣ ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ” አሏቸው ።

“ታዲያ ምናለ ደስ ይለኛል” ከማለት በስተቀር፣ “ይግቡ አቶ ወርቅነህ” የተባሉትን ሰውዬ ፈጽሞ አያውቋቸውም ። የሰውዬውን ወሬና አኳኋን ደጋግመው ከሰሙና ከተመለከቱ በኋላ፣ “እግራቸው ይገባበት እያጣ! እኚህን ደሞ ከየት ቲያንዘላዝሉ አመጧቸው? ይኸነዬ የሳቸው ቢጤ አረብራቢ ይሆናሉ፣ አበስ ገበርኩ እቴ!” በማለት አሙ ።

* * *

የውቢት ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በሚባረደው የጥር አየር ውስጥ የንጋት ጸዳል ተጐናጽፎ፣ የመስቀል ተሸካሚውን ጉልላት የቆርቆሮ ትልታይ እያንፀፀ፣ ትልቅ ዐፌርማ መሶበ ወርቅ መስሎ፣ ዙሪያውን በከበቡት ዕፅዋት ውስጥ ከወትሮው በተለየ ባሕሪ ጸጥ—ረጭ ብሏል ። በዝግታ የሚዋበው የማለዳ አየር የዛፎቹን ቅጠሎች በቀስታ ቢያንቀሳቅስም፣ ከየት—ወዴት እንደሚነፍስ አያስታውቅም ።

ቀደም ሲል እያዜሙ መንጫጫት የጀመሩት አዕዋፋት ፣ እንደ ተለመደው አጃቢ ከበሮና ጸናጽል ባያገኙም ፣ የራሳቸውን የዘወትር ማሕሌት እያደረሱ አዲሱን ዕለት ተቀብለውታል ።

የቅዱስ ሚካኤል ታቦት የከተራ ዕለት የወጣ ተመልሶ አልገባም። መዐልት የብርሃን አክናፏን ዘርግታ ስትገሠግሥ ፣ ጽልመት ጥቁር በርኖሷን እየጠቀለለች ስትሸሽ ፣ ፀሐይ ሙሉ ጨረቃ መስላ በጭጋጋማው አድማስ ብቅ አለች ። ለጋ ጨረርዋ አግድምና በሰላች በዕፅዋቱ ውስጥ እንደ ሠረፀ ፣ ሐመልማላዊው ውበት በቅጠሎች ላይ ጎልቶ ታየ።

የውቢት ሚካኤል ወደ መንበረ ታቦቱ የሚገባበት ፣ የተሳለ ስለቱን የሚያቀርብና ምስጋናውን የሚያሰማበት ሰዓት ደረሰ ።

ከሚካኤል ታቦት እፊት — እፊት የጉረምሶች ጭፈራና ሆታ፣ የሳዱሎች ዘፈንና እልልታ ፣ የእናቶች 'አለው—አለው የብር ዋንጫ' ——የካህናትና ዲያቆናት ሽብሸባ ፣ ጸናጽልና ከበሮ ፣ እንዲሁም በሕዝቡ አጀብ ደምቆ በሚጓዝበት ሰዓት ፣ ቀኛዝማችና አቶ ወርቅነህ መዘውርም አጅበው እየታጀቡ ከታቦቱ ኋላ—ኋላ ጥቂት እርምጃ ቀረት ብለው በርጋታ ያዘግማሉ ። ቸርነትና ምንዳዬ ጠበንዣ አንግተው ይከተላሉ ። አንዳንድ የቀኛዝማች ቤተኞች ታቦቱን በመንፈሳዊ ትሕትና ይመለከቱና እሳቸውንም ያያሉ ። ድግሱን ሲያስታውሱ ደግሞ በሚካኤልና በሰውዬው መካከል ልዩ ግንኙነት ያለ ይመስላቸዋል ። ቀኛዝማች ቢጠየቁማ ፣ "ነው እንጂ" ማለታቸው አይቀርም ።

ታቦቱ በጉዞው መሐል ሔድ ሔድ ፣ ጥቂት ቆም ፣ እንደገና ሔድ፣ ሔድ ፣ ጥቂት ቆም ፣ ዝግ ማለት ስላበዛ ፣ የብዙ ሰው ልብ ተሸበረ ። ከሚታየው ገሃድና ጉልህ ነገር ይልቅ ፣ የማይታይ ስውር ኃይል የሕዝቡን መንፈስ እያብረከረከ ይገዛዋል ። ታቦት ተሸካሚው ካህን ካዘገመ የሰዉ ኃጢአት በዝቶ ፣ እግዚአብሔርን አስቆጥቷል ማለት ስለሆነ ሕዝቡ ከዳር እስከ ዳር መንፈሱ ይናወጻል ።

"የዛሬው ለብቻው ነው! እናቴ ተወለደችኝ እኔ እንዲህ ቲሆን አይቼም ሰምቼም አላእ! ያንዳይ ነው" አሉ አንድ መንማና ቁመተ ውዝግዝግ ሴት ፣ ከሴቶቹ መኻል ።

"እሱ ምን ያርግ? ጊዜያችን ተበላሽቷል ፣ አባይ ወስላታው በዝቷል ፣ በንጡህ አይመጡ ፣ በያላይ አይጠሙ አይጠልዩ ፣ እሱ ብቻ ይሁነን" አሉ ሌላ ባልቴት ተቀብለው ።

"ስለታቸውን አላገባና በምንታቸው አልጠና እያሉ እኮ ነው እሣራችንን እሚያስጨልጡን ፣ ላመል ታህል አፈፍ ያረጋቸውለት



ዐሥሩን ይቀባጥራሉ ። ፊቱን መለስ ሲያደርግላቸውና የልባቸው ቲደርስላቸው ደሞ ይሆኑትን ያሳጣቸዋል ። እጅሬ ታዲያ አይረሳ ። እንኳንና ትትልሑን ጉዳይ ፣ ጉድፍ መጣያ የሞተችበትን ቅምቡርስ ያቃታል ። አሁን ተይ ያነስ ምን አለ? ችሎ ችሎ መዐቱን ያመጣውለት ፣ ቶድድ ቶድድ ቢሉት ምን መላ አለው? እሱ ይቅር ይበለኔ ——" አሉ ሌላ ድምፀ ጉርናና የፈጫይ እየፈጩ የሚኖሩና ያገሬው ሰዎች "እማማ መጂቱ" የሚሏቸው ሴትዮ ።

ፍቅር ይዟቸው በቀጠሮ የተገናኙ ፣ ዐይንና እግራቸው ቆንጆና ደም ግባታም ፍለጋ የሚራወጥ ወጣቶች ፣ ታቦቱ ይቁም—ይሒድ ፣ ሰዎች ይጨነቁ—ይደሰቱ የሚያውቁት ነገር አልነበረም ።

"ምናለበት ጥይቱን ቢያንዷዱለትና ከበሮውን ቢያደምቁት ፣ ዕልልታና ሆታው ለመቼ ሊሆን ነው?" አሉ ከቀኛዝማች አጠገብ የነበሩ አንድ ሽማግሌ ።

"ጥይቱስ ቢሆን ለመቼ ሊሆናቸው ነው? ነገ አረሀ—ላረሀ በያውሬው ላይ ቲያጨሁት ሊውሉ! ——ዋ! እጅሬ ሆዬ! ችሎ ችሎ እንኳን ከእጅ ፣ ካፍ ይመነጭቃል" አለ አንድ የፈራ መሳይ ።

ቀኛዝማች ወደ ኋላ ዘወር ብለው ምንዳዬን ሲጠቅሱት ፣ ነገሩ ገባው ። ከቸርነት ጋር ከሕዝቡ መኻል ወጣ ብለው ፣ ተራ በተራና ባንድ ላይ ወደ ሰማይ ሲተኩሱ ፣ ሌሎችም ከያቅጣጫው አንዷዱት ። አየሩ በባሩድ ሽታ ታወደ ። ሁሉም ታቦቱን አየ ።

ቀኛዝማችም "እኮ ሒድ የኔ ጌታ ! እኮ ሒድ አባቴ ! የኔ ጎዳዳ! ምን አጠፋን? ምን በደልን? መቼም የኛ ነገር —— የኛ አበሳ ማለቂያ የለው!" አሉ ለራሳቸውና ለሚካኤል ብቻ በሚሰማ ድምፅ ። ያ እጅግ የሚያምኑትና የጠየቁትን ሁሉ እንደሚፈጽምላቸው የሚተማመኑበት ሚካኤል ፣ በአቶ ወርቅነህ መዘውር ፊት እንደ ቀድሞው እንዲያከብራቸው ተማፅነው ስለታቸውን አደሱ ።

እልልታው እየቀለጠና ተኩሱ ከገምገም—ገምገም እያስተጋባ ፣ የሚካኤል ታቦት ከቤተ ክርስቲያን ቅጥር ገብቶ ሦስት ጊዜ ዞር ቆመ ። ታቦቱ ወደ ሕዝቡ ፣ ሕዝቡ ወደሱ ሲያይ ፣ እልልታና ሆታው ደምቆ ጥይቱ በተከታታይ ሲተኮስ ቀኛዝማች ያቀረቡት ሙክት ታረደ ። ካህናቱ ፣ ደብትርና ዲያቆናቱ ተደስተው ታቦቱ ሲገባ ፣ ቀኛዝማች በፈገግታ አዩት ።

* * *

የከተራና የጥምቀት ዕለት ከገቡት ሌላ ፣ በዕለተ—ቀኑ የደረሱት
ታዳሚዎችና ድግሱን በልማድ የሚያውቁ የማር—እምባና የአካባቢው
መንደር ነዋሪዎች ፣ ግቢውንና ትልቁን ዳስ አጣበውታል ።

ረፋድና እኩለ ቀን ያክል ከሚያስኬዱ አብያተ — ክርስቲያናት
የመጡ ልዩ ልዩ ማዕርግ ያላቸው የቤተ—ክህነት ሰዎች በስተሰሜን
ወገን መደዳውን ፤ ሙክት ሰበው ፣ ማርና ቅቤ ተሸክመው ፣ ካቅማቸው
በላይ ተገደውና ተለቅተው የሚያመጡ ተጋዥ ገበሬዎች ፣ ባምስትና
ስድስት ጭንቅንቅ ረድፍ በስተደቡብ ወገን ፤ ካዳራሾቹ ፊት—ለፊት
ግራ ቀኝ ባወረደ ጫፍና — ጫፉ ካህናትና ገበሬዎቹን የሚያዋስን ፣
ባይጠሩም የማይቀሩ ዘመድ አዝማድ ፣ አደራ ተብሎ ተልኮባቸው
የመጡና በተለይም በውድድሩ ወቅት ልዩ ልዩ ድጋፍ የሰጡና የረዱ
በስተምዕራብ ወገን በደረጃ መልክ በተደለደለ ቦታ ላይ ሲቀመጡ ፣
ቀኛዝማችና አቶ ወርቅነህ መዘውር በነዚሁ መኻል ዙሪያውን ገለጥ
ብሎ ከፍ ባለ ወንበር ላይ ፣ ከፊት ለፊታቸው አጠር ያለ ጠረጴዛ ተደ
ርጎላቸው ተቀምጠዋል ።

ወደ ዳሱ በሚያስገባው በር ግራና ቀኝ እንደ ኮረትና እንደ ተናደ
ካብ አንዱ ባንዱ ላይ ተቀምጠው እርስ—በርስ የሚጋፉት ደግሞ ፣
ከመጡ የማይከለከሉና ከቀሩም ወዴት ሔዱ የማይባልላቸው ዝግን
ትል ለባሽ ጎስቋሎችና ፊተ—መጣጣ የዕለት ጉርስ የለሾች ፣ ከነቀኛ
ዝማች ፊት—ለፊት በስተምሥራቅ ተቀምጠዋል ። የዳሱ መኻል ክፍት
ሆኖ ታዳሚው በየተራ እየተሠራ የሚበላበት ባለ ሦስትና ባለ አራት
እግር የመቃ ገበታ ዐልፎ—ዐልፎ ዙሪያውን ተደርድሯል ።

በአራትና በአምስት ሴቶች ያለፋታ የሚቀዳው ጠላ ፣ በትላልቅ
ማንቆርቆሪያ እየተወሰደ ፣ ባለቀው ፣ በጎደለውና በተከነበለው ሽክና ላይ
ያላንዳች ሐሳብ ይሞላል ። ሽሮ ተጨምሮበት በመረቅ የተሠራው ቀይ
ወጥ በትልልቅ ጭልፋ እየተጨለፈ ፣ ባንድ ላይ ለተሠሩት ሰባትና ስምንት
ያህል ሰዎች ይወጣላቸውና ፣ ከወጥ—አውጪው ኋላ—ኋላ በትላልቅ
ንጹህ ቆሪ ተሞልቶ በየገበታው ከሚዞረው የተከተፈ ሥጋ ዝግን
ደግሞ ፣ ሁለት — ሁለት ጊዜ እየተዘገነ በያንዳንዱ ሰው ፊት ይደረ
ግለታል ። አንዳንዱ በእንጀራ አጣብቆ ከወጡ እያጠቀሰ ፣ ሌላው
ደግሞ ሁለት ሦስቱን ምታሪ እያነሣ ይጎርሳል ። አዳዩ ለሚያውቀውና
ለሚወደው ፣ አስተፋፊሱን አመቅ—በዛ ፣ ከሥጋው መርጦ ወዛ ያለ
ውን ያደርግለታል ። የራሱ ፣ ወይም የጎረቤት በሬ ገደል ገብቶ ፣ አለበ
ለዚያም እጣቆ በልቶ ፣ ወይም የዓመት በዓል ደርሶ የቅርጫ በሬ ካል
ታረደ በቀር እጅግም ሥጋ የማያገኘው ተርታው ድኃ ፣ የተሰጠውን
ይዞ ቆሪው ውስጥ የተቆለለውን ሥጋ አሻግሮ ያያል ። ከዚያ በላይ
እሚያቀምሰው ግን የለም ።



ሰዉ እንዳሰኘው ገብቶ እንዳሻው ይወጣል ። የጥምቀት ለት የገቡ
ሁለት አዝማሪዎች ፣ ለብቻቸው በልተውና እንዳገር ጠጥተው ፣ በሕዝቡ
ፊት ወዲያ—ወዲህ እየተዘዋወሩ ማሲንቋቸውን መምታት ይዘዋል ።
ካሞጋሹም ካፋዳሹም የተለያየ ግጥም ይቀበላሉ ። ቀኛዝማች ያንን
እየሰሙ በተደጋጋሚ ሣቅ—ፈገግ—ሣቅ—ፈገግ ሲሉ ግጥም ሰጪውና
አዝማሪው ደስ ይላቸዋል ።

እነ ደብቴ ካሉበት አካባቢ ደግሞ ፣ በመጠጥ የናረና በጣዕመ—
ዜማ የተሸሞነሞነ ድምፅ ጎላ ብሎ ይሰማል ። "እግዚአብሔር ዘያቀ
ንተ፡ ኃይለ" ብሏል ቅዱስ ዳዊት ። እናም ለቀኛዝማች ኃይልን እንደ
ዝናር ያስታጠቀ ልዑል እግዚአብሔር ነው" ሲል አንዱ ፣ "ፍትወተ
ነፍሱ ወኃብኮ ፣ ወስእለተ ከናፍሪሁ ኢከላእኮ" ሰውነቱ ወድዶ የለመ
ነውን ሰጠኸው ፣ ባንደበቱ የለመነውን አላስቀረህበትም" የሚለውም
በሊቀ መላዕክት አማካይነት ለቀኛዝማች ተፈጽሟል" አለ አንድ
ከቁመናው ለዘግ ፣ ከጥምጥሙ ቀለል ያለ ውሃ የበላት ሸማ የለበሰ
የካብ ሥላሴ ካህን ።

ሰፋ ያለ የቤተ ክህነት ትምህርት ያላቸው አቶ ወርቅነህ መዘውር፣
ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ—ክርስቲያን 'ካራሽ ወዲያ ፈር ቀዳጅ'
እንዲሉ ፣ ተቆርቋሪነትና ጥብቅናውን ያበዙታል ። ከእምነታቸው ጽናት
የተነሣ ፣ የሚቀል— የሚቀለውን በቃል ፣ አየል የሚልባቸውን በኃይል
ከመመከትና ከመቃወም የማይመለሱ ፣ ክርስትና ከክርስቶስ በፊትም
ነበር ብሎ የሚሰብክ ቢያገኙ የሚያብሩ በመሆናቸው ፣ በወቅቱ ዐይ
ናቸውን ተክለውና ጆሯቸውን አቁመው የሚሰሙት የካህናቱን እንቅ
ስቃሴና ውዳሴ ነበር ።

"ቀኛዝማች" አሉ አቶ ወርቅነህ ፣ ፊታቸው በፈገግታ መንፈሳ
ቸው በደስታ ተሞልቶ ። "ያን እዚያ ማዶ ፣ ጥቁር ቆብ ካደረጉት መነ
ኩሴ ጐን የተቀመጠውን ካህን ቢያስጠሩልኝ ? እንዴት ያለ ዐዋቂ
መሰለዎ ! ንግግሩን ከቃለ እግዚአብሔር ጋር እንዴት አድርጎ አገና
ኝቶ የገለጸው ይመስለዎታል !" አሉ መቀመጫው እንደ ቆረቆረው ሰው
እየተቁነጠነጡ ። ቀኛዝማች በጣም ደስ አላቸውና ከቋሚዎቹ አንዱን
ጠርተው ፣ ከካህናቱ መኻል የቱን እንደሚጠራ ነግረው ላኩት ።

ቀላ ያለ ሰልካካ ፊተ—ግርጡ ቀጭን ካህን ፣ ለመጠምጠሚያ
የማትበቃ ዐርበ—ጠባብ ነጭ ሻሹን እንደነገሩ እያስተካከለ መጣና ፣
እጅ ነሥቶ እነቀኛዝማች ፊት በትሕትና ቆመ ። አቶ ወርቅነህ መዘውር
ከመቀመጫቸው ተነሥተው ቀደም ሲል ያዘጋጁትን 10 ብር በጭበጣ
ሰላምታ ካህኑን ሲሸልሙ ሁለመናቸው በጉራ ተፍነከነከ ። ካህኑ ስጦታ
ውን ገልጦ እንዳዩ በጣም ደስ ብሎት እጅ ነሣና ፣ ብሩን ከፍ አድርጎ አሳየ።

የቀናም የተደሰተም አብሮ አጨበጨበ ። ካህኑ ከዚያ ቀደም ስንትና ስንት ጥቅሶች የጠቀሰና ቅኔ እየዘረፈ የተቀኘ ቢሆንም ፣ 'ይበል' ከመባል ዐልፎ ተሸልሞበት አያውቅም ።

"እንዴት ያለ ዐዋቂ ካህን መሰለዎት ? ከዚህ ቀደምም አስደስቶኛል" አሉ ቀኛዝማች ነገሩን ለማጋነን ወደ ካህኑ እያዩ ።

"እርስዎ አልሰሙትም እንጂ ፣ ስንት አስደሳች ነገር ተነግሯል ። እኔማ ምንም ያህል አላመለጠኝ ። ጫጫታ ባይበዛና አዝማሪዎቹ ዝም ቢሉማ ኖሮ ፣ ሁሉንም እሰማ ነበር" አሉ አቶ ወርቅነህ የሚተራመሰውን ሰው እየተመለከቱ ።

ካህናቱ በይገባዋልና አይገባውም እርስ በርስ አጉረመረሙ ። ከአይገባውም ነበር ባዮቹ መካከል ሁለት ደብተሮች ተነሥተው በግዕዝ የመወድስ ቅኔ ተቀኙ ። የገባወም ያልገባውም አጨበጨበ ። የተሰጠ ሽልማት ግን አልነበረም ። ከነቀኛዝማች ራቅ ብለው ተራ በተራ ማሲንቋቸውን የሚከረክሩት ሁለት አዝማሪዎች ፣ ደብተሮቹን እንደ ተቀናቃኝ ስላዩአቸው እንደገና ተመልሰው ቀኛዝማች ፊት ቆሙና አንደኛው:—

"ያርሳል ያሳርሳል ያስወጣል አዳሪ ፣
ሚስቱን አይላትም በቅጥብ እደሪ ፣
ቀኛማይ በላይነህ አጥግቦ አሳዳሪ ፣
የድሆች ጠበቃ ፣ የንጉሥ አማካሪ" ከማለቱ
"አበራሽ ለልጅዋ ስም ማውጣት ታውቃለች ፣
ከስም መኻል መርጣ በላይነህ ብላለች ።
ያሙት ግብር ነወዪ ሁሉ ቢያሙቱ ፣
ቀኛማይ በላይነህ መይ ቀረ መስጠቱ
አባ በቃ አያውቄ ጐአባ እንኩ ፍትፍቱ" ብሎ አወደሰ ።
ቀኛዝማች ለሁለቱም አዝማሪዎች አምስት — አምስት ብር ሸለሙ ።

ሰዉ እንደልቡ ሲገባና ሲወጣ ሲበላ ሲጠጣ ፣ ፀሐይ አሽቆለቆለች ። ዐልፎ—ዐልፎ አንዳንዱ ከዐቅሙ በላይ ጠጥቶ በመስከሩ ጫጫታና ውካታ በዛ ። ቀደም ሲል በይሉኝታና በፍራቻ የጠገገው ቂምና ቁርሾ ፣ በስካር ሰዓት ያመረቅዝና ፣ በፉከራ ፣ በቀረርቶና ባሾገር ስድብ ያበጣብጣል ። አንዳንዱማ የቆየ ቅናትና ጥቃቱ ወለል ብሎ የሚታየው፣ የጠጣው መጠጥ የሕሊናውን ልጓም ነጥቆ ፣ እንደበቱን መረን ሲለቀው በመሆኑ ፣ ነሸጥ ያረጋቸውና ለብ ያላቸው ገበሬዎች ተራ በተራ እየተነሡ ሽለላውን አቀለጡት ። ስካራም የልቡን አይስትም የሚለው የዋንጫ 'ሥነ—ምግባር' ከኑሮና ከሰብአዊ ግንኙነቶች ጋር ተሳስሮ



የራሱ የማስጠንቀቂያ ምልክት ያለው ይመስል ፣ ከተነሡት ሰዎች መካከል ፣ ላመል ታህል እንኳ ሳት ብሎት ቀኛዝማችን የምትነካ ቃል ያመለጠው አልነበረም ።

"ያቺን መጋዞዱን ወንድሜ አትከልክለኝ ፣
አንተ ባላባት ነህ እኔ አባትም የለኝ ።
አውድማው ይለቅለቅ ከምሩን ዘርጥጡ ፣
እኑ እያ እርም—አይቀሬ ከጢሻ ሳይወጡ" አለ አንድ በንክነቱ የታወቀ የራሱን መሬት እርሶ የሚኖር ደሃ ገበሬ ። ልማዱ ነው ቢባልም ፣ አንዳንዱ በሰበቡ አንጀቱ ርሶ ተንከተከተ ።

"ኧረ ተወኝ ሆዴ ፣ ተወኝ እንናደድ ፣
ገብተናል አውድማ እየጠፋ መንገድ ።
ብለነው ብለነው ፣ ታልሆን ነገሩ ፣
የተበደለ ሰው ሜካ ነው አገሩ ።
ዱላው ሳይሰበር ፣ ጨቤው ደም ሳይወርሰው ፣
እንዴት ማርከኝ ብሎ እጁን ይሰጣል ሰው ።
ገበሬ ሲጠቁር ፣ አፈሩ እየቆላ
ተው ነገር ያመጣል የኋላ—የኋላ" ብሎ አንዱ ሸልሎ እንደ ጨረሰ ፣ ተመሳሳይ ብሶት ያላቸው አጨበጨቡለት ። አንዱ ሲቀመጥ ሌላው ይተካል ። ፎካሪው ወይም አቅራሪው የቀኝ ወይም የግራ እጅ ሌባ ጣቱን ጆሮው ውስጥ ወሽቆ ፣ ራሱን ትንሽ ዘምበል በማድረግ ሽቅብ በስላች እያየ ፣ ከወዲያ ወዲህ ይንቆራጠጣል ። ትከሻውን እያርገፈገፈና መላ አካሉን እያንቀሳቀሰ ሲፎክር ፣ ወዳጅና አድናቂዎቹ "ለካ!" በማለት ያበረታቱታል ።

በሥራ ብዛት ሲባትል የዋለው ምንዳዬ ፣ ፀሐይ ዘቅዘቅ እንዳለች ጥቂት ወራውሮ ከዳሱ በስተ ደቡብ ከቸርነት ጋር እንደልቡ ያወራ ነበር ። በሰማው ፉከራና ቀረርቶ ልቡ ናጥ ፣ ስሜቱ ቀበጥ ማለት ጀምሯል ። ቀኛዝማች እንዳጋጣሚ አሻግረው ሲያዩት ፣ ዐፈር—ፈገግ እያለ ዐይኑን በትሕትና ይሰብራል ።

"አስታውቀብኛል እንዴ ቸሬ?" አለ ምንዳዬ ለብ እንዳለው ስለ ገባው ።

"ኧረ ከየቱ ? በጅጉ የጠጣህ እየመሰለህ ፣ ፍሪያት—ፍሪያት ብሎህ ነው ፣ ቅር ካለህም ቦታ እንቀይር — ከዚህ ዞር እንበል" አለው ቸርነት ።

ቸርነት በቀላሉ አይፈታም ። ጠላ በተንቦ እየደበቀች የምታቀምጥለት አረጋሽ እንኳን ፣ "የኔ መጠንሰኛ ፣ ሸንቁር ጋን ይመስል አትሞላ" ትለዋለች ።

“ሰውዬው አሁንም—አሁንም ቲያዩ ጊዜ ፥ ያወቁብኝ መስሎኝ ነው” አለ አቀርቅሮ ።

“መስሎህ ነውዴ ያው ነህ ። ዱሮም ቢሆን ሰው ታልበዛና ታላመቻቸው በሾር ፥ ካንተ ጋ ማውጋት ይወዳሉ ። ብትሰክርስ ምን እንዳይሉ ብለህ ነው ። ቲወዱህ ባየህ! እንዲያው ቆዳህ ስስ ነው ። ሥጉ ነህ ። — —አይ ያንተ ነገር” ብሎ ሣቀበት ።

“ዛሬ አለወትሮዬ ፍሪያት—ፍሪያት አለኚ ——”

“እንኳን የሌላ ፍሪያት አልሆነዴ ፥ እሳቸውስ ብትጠቀምላቸው ይወዳሉ ” አለው እየቀለደ ።

“የምን የሌላ ፍሪያት አመጣህብኝ? ካልከስ እኔ እምፈራውም የለኝ ። ለዚህ ሁሉ ጎንበስ ቀና ያበቃኝ ፥ አልሄና ካገሬ መውጣቴ ነውዴ ፥ ማባቱ ቀዶ ሲያለብሰኝ ፥ ማባቱ ቆርሶ ሲያጎርሰኝ ነው ቸሩ” አለው ስሜቱ ናር—ናር እያለ ።

“ወጣ ያለ ሰው አያሠጋም ብለህ ነው?” አለው ካንገት በላይ እየሣቀ ።

“እንዴት ማለት?” አለ ነገሩ ግር ብሎት ።

እንዲያው በዚህ ግርግር መኻል ያ አፈሣ ታይቶህ እንዳይሆን ብዬ ነዋ?” አለው አፉን ወደ ምንዳዬ ጆሮ ለግቶ የቀልድ መሆኑ የሚያስታውቅ ሣቅ እየሣቀ ።

“አሃሃሃ!” ብሎ የሥላቅ ሣቅ ሣቀና ፥ “ቁቅም ከፈስ ተቆጠረችና? ይልቅዬ ነሽጦኛል?”

“ታዲያ ማን ከለከለህ? አታስነካውም እንዴ? እንኳን አንተና ስንቱን ወገኛ የጉሎ ዘንግ አላየኸውም እንዴ? እስቲ ዐፈር ስሆንልህ አዳሜን አብግንልኝ!”

“እኔ ልሙት?” አለው ከምሩ መሆኑን ለማረጋገጥ ።

“እሻጋሪ ይሙት!” ከማለቱ ፥ ቸርነት

“ዘራፍ!” ብሎ ወደ ዳሱ መኻል ዘው ሲል ፥ የቀኛዝማች ፊት በፈገግታ በራ ። አብዛኛው ሰው ጸጥ አለ ። አዳራሹ በር መቃን ላይ ለጠፍ ብላ የቆመችው ልኬለሽ አካላቷ በሥጋትተንቀጠቀጠ ። እዚያው ባካባቢው ከወዲያ ወዲህ ይሉ የነበሩት ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ፥ “ይኸ መዘዘኛ ጀመረ” አሉ በምን ይል ይሆን ተሸብረው ። ግራ—እግሩን አስቀድሞ ሞላ አካሉን እያነዘረ ፥



“ምናረገ? ! ምናረገ ጃራ ፥— — ምን አረገ ወንዙ? !
ምን በደለ ገሌ ፥ አረህ — ወንዛ ወንዙ
ዐፈር ነው ጦሰኛው ድንበር ነው መዘዙ!
ተው ተንግዲህ ይብቃህ ፥ ያመጡትን ያምጡ
አንተ አገር ከሌለህ በመቆረር ይውጡ
ሐ.ደህ ገላግላቸው ፥ ምንዳዬ አባ—ነውጡ ።
ተው እምቢ በላቸው ፥ ተው በቃኝ በላቸው!
ጥጥ ፈረስ ላይ ደፍጠህ ምንሽር ጋታቸው ።
ባንድ ሰው ጥጋኔ ፥ ባንድ ሰው ተራዳ
አይኖርም በላቸው አባ—ገልግል ምንዱ ።
ዘራፍ!— — ዘራፍ! — — ዘራፍ!
ዘራፍ ቆፍጣኔ! ዘራፍ — — ገላግሌ!
አናት በርቃሹ! — — አስመሳይ ኮሌ!
ዘራፍ! — — ዘራፍ — — ዘራፍ!
ወድቆ አይረቴ!— — አነጣጣሪ!
ገንዳ ውሃ ላይ ሲያስፈታ ሱሪ!
“ለካ!” አሉ እነ ቸርነት ።
እማኝ አስምሶ ቡከን ቀባሪ!
ዘራፍ! — — ዘራፍ! — — ዘራፍ!
የበላይ አሽከር! የበላይ ጋሻ!
የጠላት ጠሮ! — — የወዳጅ ዋሻ!
ቦለድ ገላጋይ ገሌ ገላጋይ!
እሞተ ቆራጥ! ባላንጣ ዘልዛይ
ዘራፍ! — — ዘራፍ! — — ዘራፍ!
ጥቃት አይወዴው! ትንታጉ ምንዳ!
ሽፍታ አስተናጋጅ! በጥይት ናዳ!
“ለካ!” አሉ እነ ቸርነት ጮክ ብለው ።

ዘራፍ! — — ዘራፍ!— — ዘራፍ! እያለ በዝግታ ወደ መቀመጫው ተመለሰ ። አብዛኛው በምንዳዬ እንቅስቃሴና በቃሉ አወጣጥ ሲደሰት፥ አንዳንዱ ደግሞ ፥ “ኤዲያ! አገር ብሎ ነገር! ደሃ ደሞ ምን አገር አለው? ደሃ አገሩ የትም” ሲል ፥ ሌላው “እውነቱን ነው! ምንም ቢሆን የገዛ አገርን የመሰለ ነገር የለም! ሰው አላገሩ ምን ክብርት አለው? አሁን ትልእ ዛፍ ተነእሎ እሌላ ሥርፋ ቢተክል ምን መእኖ አለው? አያቆ ጠቁጥ — — እያጉነቁል ” ሲል ፥ አንዳንዱ ደግሞ ፥ “እንዲያው ቢፎ ከሩትምን ያረጋል? ተመልሰው አይገቡበት አገር በሞት የተለዩ ያክል ነው ። ያርሱት ተተገኘና የሰው እጅ ታልታየ — —” ይላል በተምታታ ሐሳብ ።

ቀኛዝማች ፣ ባድናቂዎቻቸውና ውስጥ ውስጡን 'ማ ከማ ያንሳል?' እያሉ በሚፎካከሯቸው ሰዎች ፊት በመምጣታቸው ፣ ምንዳዬን አስጠርተው 5 ብር ሸለሙት ። ደስ ብሎት እጅ ነሥቶ ቀና ሲል ፣ ከወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ጋር ዐይን—ላይን ተጋጩ ። አቶ ወርቅነህ መዘውር "ይኸ በውነት ይገባዋል ። እከከከከከ!" አሉ ቀኛዝማችን እያዩ ። "የዋዛ ሰው አይምሰልዎት! የሱን ነገር ሬጋ ብዬ አጫውተዎታለሁ ። ነገር እሆዱ ገብቶ ተናዶ ነውዬ ፣ እንደ ሌላው ጊዜማ ቢሆን አፍ ያስከፍታል ። ቢያርስ ፣ ቢተኩስ ፣ ያሻውን ቢሠራ ያምርበታል" አሉ ቀኛዝማች በደስታ የተፍነከነከውን ምንዳዬን እሻግረው እያዩ ። ልኬ ለሽ ብትሠጋም አፎይ አለች ። ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ግን ፣ 'ነገረ—ሥራው ሁሉ ተሰው አይገጥም ። ለታቦቶቹ ሁሉ ቢሳሉ እሱን እይነካው ፣ አበስ ገበርኩ እቴ! አዚመኛ!' አሉ በልባቸው ።

ጠገብኩ ባዩ ሲሔድ ፣ ገና ነኝ ባዩ ሲጠጣ ጀንበር ጠለቀች ። ማደር የሚፈልጉ የካህናቱ ወገን ሁሉ ማደር እንደሚችሉ በመምሬ ተክለ ጊዮርጊስ በኩል ተነገራቸው ። ከዚያ በኋላ እንደ ተለመደው ፣ ከሥቃይ የኢዮብን ፣ ከጥበብ የሰሎሞንን ፣ ከመከራ የእስጢፋኖስን ፣ ከተአምር የማርያምን ፣ ከሠረገላ የኤልያስን ፣ ከገድል የተክለ—ሃይማኖትን ፣ ከዐይን የገብረ—መንፈስ ቅዱስን ፣ እያነሡና እያወደሱ ፣ ቋንቋው ባማረና ለዛው በጣፈጠ እንደበት እየተጫወቱ ሲጠጡ ፣ የአካባቢው ሕዝብ ግን ፣ "ተየሀ በላይስ ራስን ማስገመት ነው" እያለ ፣ የሆነለት እጅ ነሥቶ ፣ የተረታው ነገር ዓለሙን ዘንግቶ ቀስ በቀስ ሔደ ።

ለዐይን ከመያዙ በፊት የበሩት ሁለት ትላልቅ ማሾዎች እጅግ ደምቀው ሲያበሩ ፣ በየጭላንጭሉ ወደ ውጪ የወጣው የብርሃን ጨረር ዘንግ በተለያዩ አቅጣጫዎች ድንግዝግዙ ውስጥ ሥርዖ ይገዛል ። ጨለማው እያደር ኑግ ሲመስል ፣ ከዚያ ቀደም ማር—እምባ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ የብርሃን ደሴት ታዬ ።

እነ ቀኛዝማችም ፣ እንደዋዛ ወደ እልፍኝ መለስ ቀለስ እያሉ አረቄና ኮኛክ ወርወር ሲያደርጉ በመቆየታቸው ፣ የማታ ማታ ለብ አላቸው ።

"ሕዝቡ በጣም ይወድዎታል ! ሁኔታውን ሲመለከቱት ተጋብዞ የመጣ ሳይሆን ፣ እገዛ ቤቱ ያለ ይመስላል" አሉ አቶ ወርቅነህ በተለመደ የማጋነን ጠባያቸው ።

"እንዴታ !" አሉ ቀኛዝማች ። ያመጡቸውም ይህንኑ ጉራቸውን ለማሳየት ነበር ።

"እኔ በውነቱ ብዙ ቦታ አይቻለሁ ። ይኸ በጣም የተለየ ነው ። እክብሮቱ ይበታል" አሉ አቶ ወርቅነህ ራሳቸውን እየነቀነቁ ።



"አዎ ፣ በጣም የተለየ ነው ። ሕዝቡ እንደምወደው ዐውቆ ይወደኛል ። ጠቃሚና ጎጂውን ለይቶ ያውቃል ። እኔም የሰጡኝን መልክ እንካችሁ እላቸዋለሁ ። በዚያ ላይ ሁሉም በዝምድና የተዋሰረ ነው ። ባዕድ የሚባል ነገር የለብንም ። ባባትዎ ቢያጡት በናትዎ ያገኙታል ። ሕዝቡ ከወደደ እንዲህ አይምሰልዎት ። ከጠላ ደግሞ አያድርስ ነው ። — — ፊቱን ካዞረም አይጣል ነው" አሉ ፣ የራሳቸውንም ባሕሪ በሰበቡ ለመግለጽ ።

"መቼም አብዛኛው ሰው በምርጫው ወቅት ደጋፊዎ ነበር ።"

"በጠቅላላው ቢባል ሐሰት አይደለም ። የኔኮ ከሥር ከመሠረቱ የመጣ ነው ። የደህና አማካሪና የውቀት እጦት ነውዬ ፣ ይኸንዬኮ የትናየት መድረስ እምችል ሰው ነበርኩ ። ምን ያረጋል የባላገር ኑሮ ያጃጅላል ። እኔም ገበሬ ሆኜ ቀረሁ ። ርስት እንደ ሸማ ተጠቅሎ እሚወሰድ ቢሆን አዲሳባ ወስጄ እዘረጋው ነበር ። ነቃ ያለ ሰው እሚገኝበት አገር መኖር ጥሩ ነው ። ተማቶ ያተጋል ። ምን ያረጋል ! ይኸን ሁሉ የገበሬ ግብስብስ ሁለት የከተማ ሰው ይበልጠዋል ።"

"መሬት እንደ ሸማ ባይጠቀለልም ፣ ሰንትና ሰንት የሚጠቀለል ነገር አለበት" አሉ አቶ ወርቅነህ በማሾ ብርሃን በደመቀው ዳስ ውስጥ ካፖርታቸውን ደርበው ፣ በእግራም የቀንድ ዋንጫ የቀረበላቸውን ጠላ እየሸመጠጡ ።

"እንዴት ?" አሉ ቀኛዝማች ጥብቆ ይገዛልሃል እንደ ተባለ ልጅ ጓጉተው ።

የሰከሩና ለብ ያላቸው እያጨበጨቡ ፣ ያለ ከበሮና ያለ ጸናጽል ወረብ ጀመሩ ። ቀኛዝማች ነገሬም ሳይሏቸው ለውዬውን ይዘው ወደ እልፍኝ ገቡና የጀመሩትን ጭውውት ቀጠሉ ።

"ከዚህ የሚገኘው ማንኛውም ዓይነት ጥቅም ወደ ከተማ እየተወሰደ ፣ ከፍተኛ ጠቃሚ ነገር ሊሠራበት ይችላል ። ይህንንም ቀደም ሲል አጫውቼዎት ነበር ። የገጠር ርስት የከተማ ሀብትና ንብረት ይፈጥራል ። የገጠሩ እልፍኝ ፣ ባማረ የከተማ ቪላ ይተካል ። አሁንማ እርስዎም አይተውታል" አሉ እየፈገጉ ።

አቶ ወርቅነህ መዘውር ገና ለብታ ሲሰማቸው ፣ የሳሳ ጸጉራቸውን ወደ ኋላ መዳፕ ፣ ከወትሮው በበለጠ ሁኔታ ሣቅ—ፈገግ ማለትንና ፣ የሚጠጡበትን ዕቃ መነካካትና ማንከራተት ያበዛሉ ። ከሰከሩ ደግሞ ፣ የጀመሩትን ቂም ፣ በይሉኝታ የተዉትን ነገርና የሸሸጉትን ሐሳብ አፋቸው እንዳመጣ ይዘረግፉታል ፣

"ታዲያ ለዚህማ ምን ችግር አለ?" አሉ ቀኛዝማች ። "እኔ ብቻ እምፈልገው ዘዴ ዘዴዋን እሚያሳየኝ ሰው ነው ።"

"አይ እርስዎ፣ ይረሳሉ ልበል? ለዚህማ እኔ አለሁ። የእርስዎማ በጣም ቀላል ነው። ስንቱን ሰው ራሱን አስችየዋለሁ። መግባቡትና መተማመን ካለ፣ ሽቅብ ቁልቁል የሚያስኬደውን ዘዴ እናውቀዋለን። እኔ እኮ እዚህ ባላድግም አገሬ ነው። ይህን ያውቃሉ?" አሉ አቶ ወርቅነህ ሐሳባቸው እየተቆራረጠ።

"እንዴታ! ይኸንማ እንዴት አጣዋለሁ። እንኳንም የቀረብዎት። እኔ አባቴ ማይጨው ወድቀው ባይቀሩ፣ መች እዚህ ተወሽቄ እቀር ነበር። እኔን የጎዳኝ ያባቴ ሞት። አፈር ጠባቂ ሆኜ ቀረሁ። አሁን ደሞ እርጅና ሲመጣ ሩጫ ሆነ። ሲመሽ ወደ ቆላ" አሉ እየተከዙ።

* * *

የቀኛዝማች በላይነህ አባት፣ በ1928 ዓ.ም. አራት ሎሌዎችና ሁለት ልጆቻቸውን አስከትለው ማይጨው ከዘመቱ በኋላ፣ አንድ ልጃቸውና ሁለቱ ሎሌዎቻቸው እዚያው ጦር ሜዳ ሲሞቱ፣ እሳቸው ግን ክፉኛ ቆስለው፣ በዚያን ጊዜው የ20 ዓመቱ ወጣት በበላይነህ ታፈስና አብረው በዘመቱት ሰዎች ርዳታ እንደ ምንም ተደጋግፈው ደሴ ከተማ በድብቅ ገቡ። ሆኖም ሕመምና ሥቃያቸው እየበዛ በመሔዱ፣ እዚያው ደሴ ዐርፈው ተቀበሩ።

የኋላ—ኋላም ያባታቸው ሞትና የሳቸውም ዘማችነት ታይቶ፣ በተጨማሪም ንጉሡ በ1948 ዓ.ም. ማርሻል ቲቶን ይዘው ባለፉበት የካራቆሬና የጨፋ—ሮቢት ጐዳና ላይ የአካባቢውን ሕዝብ አሰልፈው በመገኘታቸው ከጉብኝቱ ፍጻሜ በኋላ አዲስ አበባ ድረስ ተጠርተው የቀኛዝማችነት ቀሚስና የገምዛ ወረዳ ገዥነት ማዕርግ ተቀበሉ። ሆኖም በዘር ሐረግና በዐርበኝነት ሙያቸው ከሳቸው የማይተካከሉት ሁሉ ሰፋፊ የግዛት ሀገር ሲሰጣቸው፣ እሳቸው ግን፣ ከወረዳ ገዥነት አለማለፋቸውን እንደ በደል ቆጥረውት በሥውር ቁጭት ሲበግኑ ኖረዋል።

* * *

እና አቶ ወርቅነህ በምኞትና በተስፋ፣ በፍላጐትና ዓላማ ሲደጋገፉና አንዱ ከሌላው የሚያገኘውን ጥቅምና ትብብር ሲያወሩ፣ ለነርሱ ብቻ ራት ቀርቦ ለወጉ ያህል ጎራረሱ። ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ከሚወራው ወሬ በጨረፍታ እየሰሙ፣

"ጉድ እኮ ነው! ሰው ቢጤውን አያጣ! ደሞ እንዴት ያሉት አረ ብራቢ ሰባኪ መጡ እቴ! እኚህ ቄስ በሆኑ ኖሮ ማንም አይታከላ



ቸው ነበር። አበስ ገበርኩ እቴ፣ ስንት አለ በየቤቱ" እያሉ ወጣ ገባ፣ ሔድ መለስ ሲሉ ቆዩና፣ "እኔ እንግዲህ ወጥቶልኛል፣ ተንግዲህ ወዲያ የራሱ ጉዳይ" ብለው እዚያው እልፍኝ ውስጥ ከነቀኛዝማች ባሻገር ደገፍ ብለው ተቀመጡ።

"ያንን ቅድም ሽፍታ አስተናጋጅ በጥይት ናዳ እያለ የፎከረውን ጎበዝ አስጠርተው ይሸልሙልኛል። ቆራጥ ሰው እወዳለሁ" አሉ አቶ ወርቅነህ እግራቸውን ዘርግተውና ተለጥጠው።

"ምንዳን ነው?" አሉ ቀኛዝማች ለማጣራት።
"እኔ የት ዐውቀዋለሁ? ምንዳ ነው ስሙ? ያ የበላይ አሽከር፣ የበላይ ጋሻ ያለው?"

"አዎ እሱ ነው።"

"እንዴት ደስ አለኝ መሰለዎት!"

"እኔም እወደዋለሁ። በጣም ታማኝ ሰው ነው። ይገርሙ እሑዳለሁ።"

"ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑም ነግራኛለች። ለካ እሱ ነው። አቤት ስታመሰግነው!" አሉ ኮኛካቸውን እየጨለጡ።

ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ፣ መርዶ እንደ ሰማ ሰው ደነገጡ። ወዲያው ንዴት አንዘረዘራቸው። አቶ ወርቅነህን ትኩር ብለው አዩዋቸው። ተጠራጠሩ።

"ነገር አለ፣ የተገመደ ግምድ አለ። መች በጤናው እንደ ቀንድ ቀድሞ እንደ ጅራት ተከትሎ መጣ" አሉ በውስጣቸው። ታዲያ ምን ይሆናል! ይኸኛው እንደ አልባሌ ሰው ወይም እንደነምንዳዬ ና ውጣ፣ ና ግባ የማይሉትና የማይገላምጡት፣ ባለባበሱ ያማረ፣ ባነጋገሩ የተንቀባረረ፣ እኩል ተቀምጦ የሚያወራ ሆነባቸውና፣ 'ሆሆይ! ያ ከይሲ በስንት ጣሙ እቴ! የሰው ፊት አይቶ ምልስ ይላል። ለዚያውም እኚህ እብድ ቀማሽ የሆኑ ሰውዬ እያስቸገሩት ነወዬ፣ መቼም የዘመኑ ሰው ይሉኝታ የለው። እዚያም እንዲሁ ሔዶ ሲውጥ ከርሞ ነው። አበስ ገበርኩ ጌታዬ! በሁለት ቢላ መብላት ቱ!' አሉ እንደገና በልባቸው።

"እኔ በወንድነቱም እወደዋለሁ" አሉ ቀኛዝማች። "ልቡ ዱጭ አይልም። ፉከራ ብቻ አይደለም። ባለሙያም ነው። ያረስ እንዲሁ ማንም አይታከለው። አተኳኮሱማ ተብሎ ያቢቃ ነው። የዛሬ ዓመት አንድ ቦታ ደርሰን ስንመለስ፣ በቅሎዬ ላይ ሆኜ፣ አንድ ድኩላ አሳየሁትና 'እምኑ ላይ ልበለው?' አለኝ። እኔ ደሞ እንደዋዛ እቀንድና—እቀንድ

መብቀያው መኻል እልኩት ። ቦታ ፈልጉ በርከክ አለና ፣ ዝቅ የለ ከፍ የለ ፣ እዚያቹ እተባላት ቦታ ላይ መታው ። ቢያስቀድሙት ንቁ ፣ ቢያስከትሉት ጥንቁቅ ነው ። በዚያ ላይ እሱ የሰማትና ያወቃት ምስጢር በቃ ፣ ተመረገች ፣ ተቀበረች ማለት ነው" አሉ ቀኛዝማች አነጋገራቸውን ጠንከርና ረገጥ አድርገው ።

"ሰው ማለት ይኼ ነው ። ቢተለይ ፣ በተለይ ምስጢር መጠበቅ የሚችል ሰው ። እንዳንዱኮ ሽንፍላ የለውም ። ጎሽ! ጎሽ! ጎሽ! እኔም አልተሳሳትኩም ፣ ነገ ያስጠሩልኛል" አሉ ። ምንዳዬን የማሞጋገሱና ስለሱ የማውራቱ ነገር በመቀጠሉ ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ውልቅ አሉ ።

ዳሱ ውስጥ የሰከሩ ካህናት ፣ ብቅምጥና በቁም እየተናጡና እየተወዛወዙ ፣ በአማርኛና በግዕዝ ያዜማሉ ። ያንዳንዶቹ ጥምጥማቸው ተፈቶና ሱሪያቸው ላልቶ ፣ ነጠላቸው ሲንዘላዘል ፣ ሌሎቹ በርጋታና በጸጥታ ፣ ደርበብ ብለው ይወያያሉ ። ከካህናቱ ባሻገር ደግሞ ፣ ገበሬዎቹ ዐለፍ—ዐለፍ ብለው አምስትና ስድስት እየሆኑ ጭብርቅርቅ ያለ ዘፈን ይዘፍናሉ ። አንዱ ገበሬ ፣—

"ተሚወዷት ጋራ አንድ አልጋ መተንፈስ ፣
ስልሳ ዳውላ ጤፍ ፣ ካንድ አውድማ ማፈስ" ሲል ፣

ሌላው ደግሞ ፣ "እንጆኪያና ገምዛ ፣ ግሼና ቀወት

አጥንት የሌላት ልጅ ፣ እንደቀይ ሽንኩርት" ይላል ።
ቹርነትና ምንዳዬ የሞላ ሽክናቸውን እንደ ጨበጡ በሞቅታ እያወሩ ያንጐራጉራሉ ።

"ብለነው ብለነው ታልሆን ነገሩ ፣
የጀግናና የብር የትም ነው አገሩ" ሲል ቸርነት ፣ ምንዳዬ ቀበል ብሎ ፣

"አገሬን ተውሁና ብሔድ እሰው አገር ፣
እንደምን ይመራል የምስማው ነገር" አለ ።

* * *

ልኬለሽ ልጃቿን አስተኝታ ፣ ደጅ ደጁን ትንቀራጠጣለች—የጎጆዋን ዙሪያ እያሰሰች ፣ ዐሥረኞ ምንዳዬን እያየች ። ጨንቋታል ። "ና ጠበንጃህን ውሰድ ልበለው ይሆን? 'ምን አየሽና ምን ሰማሽ' ብሎ ቢያፋጥጠኝስ ? ወይ ጣጣ !" እያለች በሥጋት ትርበተበታለች ።



የድግሱን ጠላ ሲመገምጉ ውለው ሞቅ ያላቸው የጎረቤት ባልቴት ሽኝታ ወደ ቤቷ ስትመለስ ፣ አንድ በደንብ ተከናንቦ ጠበንጃውን በጥንቃቄ የያዘ ሰው ከፊት — ለፊቷ ሲመጣ በማየቷ ፣ እሷም ነጠላዋን ከነብነብ ብላ እስከ አፍንጫዋ ተሸፈነችና ፣ የግራ ቀኙ አጥር ያጣበበውን የመንገዱን ጠርዝ ይዛ ፣ አቀርቅራ አሳለፈችው ። 'ማን ነሽም ምንድን ነሽም ሳይላት በፈጣን ርምጃ አልፏት ሔደ ። አላወቃትም ። እሷ ግን ቆም ብላ ከበስተኋላው አየችው ። በእካሔዱና በቁመናው ስላወቀችው ብርክ ያዛት ። በፍርሃቷ ውስጥ የመከራ መዓት ታያት ። አንዳች ተናካሽ ዐውሬ ያየች ይመስል ፣ የቤቷን መንገድ በሩጫ ተያያዘችው ። ዐርፋ መቀመጥም ሆነ ረጋ ብላ ማሰብ ተሳናት ። ሌላው ቀርቶ ጓሮዋን ፈራችው ፤ ጨለማውን ጠላችው ፤ እናም ተንቀራጠጠች ።

* * *

እስካደች አንገቱ ላይ ተጠምጥማ ፣ "ደህና ነህ ፣ በደህና ሰነበክ ? እንዴነህ ? ዛሬ እንዴት ብለህ መጣህ ?" ብላ አገላብጣ ሳመችው ።

"ደህና ነኝ ! እናንተስ ሁላችሁም ደህና ናችሁ ?" ብሎ እንደገና አገላብጦ ሳማት ።

"እንዴት መጣህ?" አለችው ትከሻውን ይዛ ።

"ምን አለብኝ ! ደሞ ያገሬ ምንገድ ይጥፋኝ እንዴ ? አይዞሽ ! ሆን ብዬ ነው የመጣሁት ፤ ሰዎችም አብረውኝ አሉ ። እየሀ ሥሬ ከምንገድ በታይ ተሸምጠዋል" አላት ልቡ እየተንደቀደቀ ። ቀና ብላ ስታየው ትኩር ብሎ አያት ። የተነፋፈቁ ዐይንና ልቦች ተገናኙ ፣ እየፈሩ ። እስካደች ተመልሳ የአጥሩን በር በተዋጋ አጠበቀችው ። የጎጆዋን በር ሽጉራ ሙቀጫ ካስደገፈችው በኋላ ፣ ኩራዙን ከምሰሶው ላይ አውርዳ ከአፈማ አካባቢ አራቀችው ። አልተቃወመም ።

"ልጆቼን ቀሰቅሻቸው ?" አላት ወደ ተኙበት እየተመለከተ ።

"እሺ ቆይ እቀሰቅሳቸዋለሁ ፣——እንዴት በዛሬው ኸን መጣህ?" አለችው ተጨንቃ ።

"ተሌላው ጊዜ ዛሬ ይሻላል ብዬ ነው ። የሰከረ ሰው ልብ ብሎ አያይም ።"

"ሁሉም ልቡን ይሰት መስሎሃል ሞኝ ? አያድርስ ነው" አለች ፍርሃቷ እያየለ ።

“ለመሆኑ አሉ?” አላት ቀስ ብሎ ።

“ማን?” አለችው ማንን ማለቱ እንደሆነ ቢገባትም ።

“ቀኛማች ።”

“አዎ አሉ ። እሳቸው ምን አለባቸው ። የሞላላቸው ሰውዬ !”

“እቴዋ ጋ ሰው ልኬ ነበር ፣ ብቅም አላለች!”

“እሳቸው እቴ ?”

“ሰው ልኮብኝ ነበር አላለችሽማ ?”

“ነግረውኝማ ቢሆን አልደነግጥም ነበር — — ሰው ሁሉ እንዳንተ መስሎ ሃል —— አንተ ብቻ ——”

“ምናለ! የሚፈርሰውና የሚዘጋው የኔ ቤት ፣ ለመሆኑ ያ ለሃጫም የት ነው ያለው?”

“ማን?”

“አንቺ ደሞ በጨለማ ስም አይጠራም ፣ አሁን ያ የሳቸው ስሎግ ጠፋሽና ነው?”

“እእ! እዳስ ተኸምጠ ይንጀባረራል ። ያለኔ ምን ወንድ አለ እያለ ሲጎማለል ዋለ ፣ ቲፎከር!”

“የወንድና የሴቱማ ነገር ይኸው አሁን ሲለይ ነው ። ተለም ዷል! ——”

“እንዴት ነው ይለያል ብሎ ነገር? ደሞ ምን ታረግ ከጀለህ?” አለች ትኩር ብላ እያየችው ።

“ምነው በይ! ዛሬማ ቁርጥ ነው ። እንጫርረዋለኋ!”

“አይይይይ! ምነው ብተወኝ ይኸን አጉል ነገር?! እያሰላሰሉ ነውዬ ፣ ይኸማ የልጅ ጨዋታ ነው ። ቀድሞ ነገር ምን ቲያረግልህ? በምን ስትገናኙ? ለሰው ብለህ የሰው ሰው ብታበላሽ ማ ይለቅህ መስ ለህ? ተው እንዳፍ አይቀናም” ብላ የጉንዮሽ አየችው ።

* * *

በጣውንታቸው ስም መነሣትና በምንዳዬ መመስገን ደማቸው ፈልቶ ፣ ንዴታቸው የተቀጣጠለው ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ፣ በጓሮ በር



ወጥተው ብቻቸውን ወደ አፈሣ ቤት ሲገሠግሡ አልፈሩም ። ደግነቱ ቅርበቱ ። የአጥሩን በር ቢገፉ ቢነቀንቁ ፣ የታሰረበትን ጠፍር ፣ የተቋጠረበትን ውል አጡት ። ጥቂት ቆርጠጥ ፣ ቆርጠጥ ካሉ በኋላ በቀጭን መንማና ድምፅ “አስካደች!” እያሉ ሁለት ሦስትዬ ተጣሩ ። ጸጥታው ተባበራቸው ።

“እቴዋ ነች ! —— ተነሽ ! ቶሎ ክፈቺላት” አለ የጨበጠውን የሽክና ጠላ አስቀምጦ ።

* * *

“ምንዳ!” አለች ልኬለሽ አንገቷን ሰበር አድርጋ በመጠነኛ ቁልምጫ ፣ “ተነሥ እቤት ግባ መሽቷል ። እኔ ደሞ ታሁን አሁን ትመ ጣለህ ስል —— ነገ ደሞ አንዱ ጋ እንሔድ ይሏችሁ ይሆናል —— የሳቸውን ጠባይ አጣችሁትና ነው” አለች ‘ማ ሰምቶኝ ይሆን’ በሚል ሥጋት ዙሪያውን እያየች ። “በሉ ተነሡ ! ቸርነት ተነሥ !” አለች በትዕዛዛዊ ሁኔታ ።

“እኮ ቆይ ፣ ምን አስቸኮለሽ? ሰዉ ስርፉ—ስርፉውን ይያዝና እንመጣለን ። እንግዳ ተቀምጦ ቤተኛ ይተኛል እንዴ? ሒጂ ቀስ ብለን እንመጣለን” አላት ምንዳዬ አንጋጦ እያየ ።

“አንተ ደሞ ሰው እሚልህን አትሰማም ፣ ብርቱ ዐመል አለብህ ወንድሜ ። ዛሬ ስንቱ ልታይ—ልታይ እያለ ሲከተፈተፍ እያየኸው ፣ አንተን የት ሔደ እሚልህም የለ ። ይልቅዬ ተነሡ ፣ ተነሥ በለው ቸር ነት — — አንተ ደሞ ምን ነካህ?” ብላ ተቆጣች ። ማምረሯ ገባቸውና ጠላቸውን ጨልጠው እንደ ተነሡ፣እእምሮዋ በደስታና በሥጋት ታመሰ። አጥሩ ጥግ ሰው ያደፈጠ ፣ ካሁን — አሁን የሚተኮስ እየመሰላት ተንቀጠቀጠች ። እሷ እፊት እፊት እየተገላመጠችና እየተርበተበተች፣ እነሱ ከኋላ—ኋላዋ እንደ ልባቸው እያወሩ ፣ “ይኸን አፋቸውን ቆረቆንዳ ነበር መወተፍ” እያለች ተከትለዋት እቤት ገቡ ።

“እስቲ ደህና ሰናወጋ እምናመሽውን ፣ ቄሶይ እንኳ ሳያንጎላጁ እንግባ? ከሰው ጋ ይጋጫሉ ብለሽ ሠጋሽ መሰል?” አላት ቸርነት እየ ሣቀ ።

“አዝናልን ይሆናል ፣ መሽቷል ብላ መሰለህ? በገዛ ድግሳችንማ ከሰው ጋ ከተጣላን የጉድ ነው ። ሰዉም ሰው አያረገን” አለ ምንዳዬ በረዥሙ እየሣቀ ።

“እስቲ ቀስ በልና ሣቅ ! ያ ስካር ማለት ይኸ እኮ ነው ። ባት ሰክርም ሰከረ ትባላለህ ። በሉ ረጋ ብላችሁ ቁጭ በሉ ፣ እግረግላችሁን

ኢታቁትም" አለች ። የአፈሣን መምጣት እንዴት አድርጋ ለቸር ነት እንደምትነግረውና በምን አሳባ ወደ ውጪ እንደምትጠራው ግራ ገባት ።

"እስቲ ደህና — — ና እስቲ ቅዳ እያልን እንዳንጠጣበት ——"

ሲል ምንዳዬ ፤ "እንዲሁ ሥጊ ያላት ቤትዮ ፤ 'ፈሪን በሕልሙ ነብር ቲያሯሩጠው ያድራል' ይባል የለ ! የዛ ቢጤ ፈርታ ነው" አለ ቸርነት አፉ እንዳመጣ ።

"እንዴት ያለውን በቃኝ የማይለውን ሆድ ሰጣችሁ ልጄ? አለ መተርተራችሁ —— ካልጠቀማችሁ እኔና አረጋሽ ለወጥ ሠሪዎች የከተትነው አንድ ጋን ጠላ አለ ፤ ና ብቅ በልልኝና እናምጣ — —" አለች ፍርሃት ባልለቀቀው ገጽታ ። ሊከተላት እመር ብሎ ተነሣ ።

"አንተ ና ቁጭ በል ፤ እኔ እከተላታለሁ — በዚ ቤት እኮ ሰክ ሬአለሁ" አለ ምንዳዬ ።

"እኔ አልወጣኝም ። ከሰከራችሁማ አላመጣላችሁም— ና ልጄ!" ብላ ድንገት ወጣች ።

ቸርነት ተከትሏት እንደወጣ ወደ ጓሮ ከሚያስገባው በር ገለል ብላ ፤ "ና እዚህ ጋ እምነግርህ ነገር አለኝ" ስትለው ፤ ነገሩ የቁም ነገር መሆኑ ከአጸቋጧና ከአነጋገሯ ጫን ማለት ገባውና ነቃ ብሎ አጠገቧ ቆመ ። እቧም የአፈሣን መምጣት ፤ ፍርሃትና ጥርጣሬዋን ሁሉ ዝቅ ባለ ድምፅ በፍጥነት ነገረችው ። ቸርነት ደንገጥ ብሎ ላፍታ ያህል ዝም አለ ። ሐሳብ ያዘው ። ወዲያው መጥፎ—መጥፎ ነገር ታየው ። ሁለመ ናው በቁጣ ነደደ ። ሐሳቡን ለመቁረጥ ግን ጊዜ አልወሰደበትም ።

"እንዲች ብለሽ እንዳትውጊ ፤ ማ አባቱ እንዳይነካው ብለሽ ነው! ደሞ ይኸን ያክል ሙያ! ለሱ ብቻ እንዳትነግሪው ። እኔ እማረጋውን ዐቃለሁ" አላት በሙሉ ልብ ራሱን እየነቀነቀ ።

"እኮ እንዴት እናርግ? — — አንተኮ አረጋገጡን አላየኸውም የቁጣ መስሎኛል" አለች ድምጿ እየሰለለና እንባ እየተናነቃት ።

"እንግዲህ እኮ ያንቺ ነገር መላ የለውም ። ይልቅዬ ጠላውን አምጪ ፤ ሌላ—ሌላውን እኔ ዐቅበታለሁ ። ደሞ ይቺን እንባሽን ያይና እምጪ ፤ ሌላ—ሌላውን እኔ ዐቅበታለሁ ። ደሞ ይቺን እንባሽን ያይና ጉድ ይፈላል ፤ ምን ሆነሽ ነው ብሎ ያፈጥብሻል" ብሎ እሱ ባጥሩ ጥግ ወደ ጓሮ ፤ እቧ በጓሉ መኻል ወደ እዳራቹ በመሔድ ተለያዩ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፤ ልኬለሽ በትልቅ ገንቦ ጠላ ፤ ቸርነት ከነጠላው ሥር በክንዱ አጣብቆ የያዘውን ይዞ ሲመለሱ ፤ ምንዳዬ ጋደም ብሎ ነበር።



"እረ እንኳንም የሔድኩ አንተ ።"

"ምነው? ምን አግኝተህ መጣህ?" አለ ከራሱ ቀና ብሎ እየፈገገ።

"አሁን ከልኬ ጋር ወጣ ከማለቴ ፤ ቀኛማች እስፈልገውህ ነበር ብለውኝ ስሔድልህ ጊዜ ፤ እዚሁ እልፍኝ አጠገብ ምናምኑን ጉዛጉዘህ ተኛ ብለው አሉኝ ።"

"እሱም እለ አትላቸውም ኖሯል ?—— ምነው ብቻህን? የት ሔደም አላሉህ?" አለና ተነሥቶ ተቀመጠ ።

"አላሉኝም ። ሌላ ሰው አያስፈልግም ብለውኛል ። አንተ ደሞ የግድ ካልታዘዝኩ ትላለህ ልበል? ማ ጎሽ ይለኛል ብለህ ነው? እስቲ እኔም የታማኝነቱ ወግ ይድረሰኝ?"

"እኔ ለጨዋታው አልኩሂ ፤ እሳቸው ባይሉስ ብቻህን አልተውህ፤ ያውም በዛሬው ቀን ! ——"

"አንተኮ አዙረህ ማየት ትተሃል ፤ እንደ ልጅ የፊት — የፊትህን ነው ። ማ ንገረው አለህ ቢሉኝህ? እኔን ወሬኛ ለማስባል ነው ። በላ የእ ንጀራ ገመዱን በጥበሸው እረፍ! ይልቅዬ ቤቶች ለቤቶች የሚደብ ሉት ጠላ ጥሩ ጥሩውን ነው ። አንድ ሁለቱን ሸከና ከልበሚው ልሒድ" ብሎ ልኬለሽ ፈጠን ብላ የቀዳችለትን ጠላ በቁሙ ጠጥቶ ድንገት መሰስ አለ ።

ቸርነት ፤ የግሉ ጠበንጃ ስለሌለውና ቀን ቀን የሚያነግተውንም ፤ ያለ ቀኛዝማች ፈቃድ ከእልፍኝ ማውጣት ስለማይቻል ፤ ደህና ጅናም ዱላውን ፤ እንዲሁም ባለሁለት አፍ ስለታም ዱቢቱን ይዞ ከምንዳዬ ጎጆ በስተጓሮ ሲል ልክ በአልጋው አኳያ እሚጠረጠር መረማመጃ ጥግ ፤ ደባደቦውን ለብሶ አደፈጠ ።

## ምዕራፍ ሠላሳ ሁለት

ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱ ፥ "አልመጣም እንዴ? የታለ?" አሉ በቀስታ በደብዛዛው ብርሃን ውስጥ ።

"መጥቷል እንዳ ነው ።"

"ምንዬ መጣ ልጄ?" ብለው ወደ ጓዳ ገቡ ።

"ገና ገባ ማለቱ ነው ። ጥኢት ቆየት ብኋል " ብላ 'ከፉ መታረሪያ እግር' አለች በልቧ ።

ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱና አፈሣ ተሳስመው መደቡ ላይ ተቀመጡ ።

"እንዴት ብለህ በዛሬው ቀን መጣህ? ቲነግረኝ ከው አልኩ ።"

"መቼ ይሻል ይሆን ስል ሳእማማ ሰነበትኩና ዛሬ ይሻላል ብዬ ብቅ አልኩ ። ቆይ ዛሬ ቆይ ነገ በማለት ነውዪ በማንቻውም ቀን እችል ነበር" አለ መድፈሩን ለመግለጽ ።

"አዬዬ! እንጃልህ? የዛሬን ይሻላል አንተ ታአለህ! እንደኔ እንደኔስ ——" ብለው ሳይጨርሱ ፥

"ኋላ እንዴት ይሁን ነው እምትዪውን ይኸው ስንትና ስንትኤን አድፍጠን ጠበእነው ፥ ጠላትሽ እልም ይበል ፥ እልም አለ ። እኔ ምን እንደሚነግረው እንጃ ። ታዲያ እሱን እስተ መቼ መጣ አልመጣም ስንል እንከርማለን እቴዋ? ዛሬ ደሞ እንዲህ ሰዉ ተወዲያ—ወዲህ ጅር—ጅር ሲል የልብን ሠርቶ ሸተት ነው ደጉ —— ያም አደራህን ያልሸው ሰውዬ ፈራ መሰል —— እንደ ግመል ሽንት የኋሊት ሔደ ። እኔ አንቺ ብትዪና ደስ ይበልሽ ብዬ ነውዪ ፥ የሱን ሰውዬ ነገር አልወደድኩልሽም" አለ ጠበንጃውን እያሻሸና እያዟዟረ ። አስካደች ደገፍ ብላ በቁሟ ትሰማለች ።

"ማን"

"ያ ጋሼ አስረስ ነዋ! —— እኔም እርም አይቀሬ ልበለውጂ ።"

"አዬዬ ምነው የሱን ነገር ብተወኝ ልጄ? 'ሰውን ማመን ቀብሮ ነው' አለች አሉ ቀበሮ ። ምነው እሱማ ይኸ ነገር የኋላ—ኋላ የተሰ

ማብኝ እንደሁ ከቀኛማይ ጋር ያቆራርጠኛል ። ከሰው ጋ ደም ያቃ ባኛል ብሎ ገደድ—ገደድ ማለት አምጥቶ ! ሰው ያለ መስሎሻል ፣ የነገርኩትለት ፣ ታፋ ቀደም—ቀደም ፣ ሽርከት—ሽርከት ማለት አብ ዝቶ ነበር'' አሉ የተማረሩ በመምሰል ።

* * *

ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱ ፣ ከአዲስ አበባ ማር—አምባ በገቡ በሳ ምንቱ አፈሣ ዘንድ በድብቅ ፣ ገንዘብ ፣ ልብስና ስንቅ ልከው ፣ ከማር—አምባ ውጪ አንድ ዘመድ ቤት ድረስ መጥቶ እንዲገናኙ ቀጠሮ ይዘው ሲጠባበቁት ከዋሉ በኋላ ከአፈሣ ጋር ተገናኝተው ነበር ። ከብዙ ጭውውት በኋላም አፈሣ ምንዳዬን ለማስገደል ወይም ለመግደል ያወጣውን ዕቅድ ከፍ ባለ የብሶት ስሜት አጋንኖ ስለ ነገራ ቸው ፣ ከነገሩ ለማምለጥና ከሱ ንትርክ ለመሸሽ ያሀል ብቻ ፣ "የሚ ሆንልህ ተሆነማ እኔ ምን ቸገረኝ ፣ አንተ ብቻ በርታዬ ፣ የመጣው ቢመጣ ግድ የለህም ፣ ተየህ ቀደምም እኮ ተተላከው ልጅ ላይ እገልግሎን ሽፍታ ቀምቶ ወስዶበትዬ አፈሣ አቀበለ አልተባለም ። ምን በወጣህ ። አድርስልኝ ብሎ የላከውን ልጅ እንኳ በቅጡ እያቀ ውም ብለን ጥርቅም ብለናል ። እኔ ከባቸው ጋ ተታረክ ምን አባቱ እንዳያርግህ ብዬ ነውዬ ፣ የማይሆን ተሆነማ እኔም ችላ አልለው ። እሳቸው እንደሁ የገዛ እጃቸውንም አያምኑ ፣ ጠርጣሪ ናቸው ። ለየህ ብዬ ነበር'' በማለት ለሁለተኛ ጊዜ የታቀደውን የግድያ ሐሳብ የደገፉ በመምሰል ካንገት በላይ ተቀበሉት ። ሆኖም እርም—አይቀሬ ከአፈሣ ጋር እንዳይተባበርና በሰበብ ባስባቡ ነገሩን እንዲያጓትት በምስጢር ነግረው ፣ ነገር እንዳያዝረከርከም አስጠንቅቀው ባንድ ስልቻ ጤፍ ጉርሻ አቶን አስያዙት ።

* * *

"ይተወዋ ይጠንቅረው ! ማባቱ ይለማመጠዋል !'' አለ አፈሣ ።
"ለዚህ ነዋ ጥፍት ያለው ? ሽኩቲያም !''

"ኧረ እሱን ተወው ! እኔ መች የሱ ቅማል በላኝና ! ይልቅ አሁን እንዴት ይሁን ነው እምትለው ?''

"አሁንማ ምን እንዴት ይሁን አለ? ሁለት ሰዎች ይገዬ መጥ ቻለሁ ።''

"ምን ? — — ምን እሚያረጉ ? ከየት የመጡ ?'' አሉ ድንጋጤአ ቸውን ውጠው ።



"ባላጋሮቹ ናቸዋ ! ተኋሁነናል ። የኛን ወንድም ዐፈር በልተት እያሉ ፣ ዋ ንዴታቸውን ባየሽው ? እሳቱ ባፋቸው ቦልቅ—ቡልቅ ቲል !''

"የማር—አምባው ያለህ ! ኧረ ተወኝ ወንድሜ ! እስቲ ስንትና ስንት ቀን ዋልቶ ተርፎ ፣ እንዴት ሰው በዛሬው ቀን የሰው ሰው ይዞ ይመጣል ? በዚህ ላይ እሳቸው ለምድር—ለሰማይ የከበዱ እንግዳ ይዘው መጥተዋል — — እንዴት ጉድ ፍልት ያለበት ነገር አገኘኝ ?''

"ኧረ ንሱ ሰዎች ! እኔ ምንአሻኝ ! ለምን የሰማይ ስባሪ አያህሉ ላቸውምን ማ ከማ ያንሳል !''

"እንግዲህ እኮ ያንተ ነገር መያዣ መጨበጫ የለውም ። እያሰላ ሰሉ ነውዬ ። ሰው መሆናችን ለምኑ ነው ። አለያማ ከብትም ቆሞ ይሔዳል ! እሳቸው ነገ ተነገ ወዲያ ሲሔዱልህ ምን አጣደፈህ? 'የጅብ ችኩል' እሚሉት ቢጤ ! እንዴት ያለው አጉል መካር መከረህ ልጄ ? አዲሳባ ታልወሰዱትም እሰዬው ነው ፣ ቀስ ብለህ የልብህን ትፈጥ ማለህ ። ከሔደም ኀርጊስ በመገላገያው ገላገለህ ፣ ሰተት ብለህ እቤትህ ትገባለህ ። ይኸ የዛሬው ነገርህ ግን ደስም አላለኝ ። እቴዋ ምን ብላኝ ነበር ትላለህ ኋላ'' አሉና መከፋታቸውን ለማሳወቅ ፊታቸውን አዞሩ ።

"ስንት ቀን መሰለሽ ተኔጋ የተንገላቱት? አሁን አይሆንም ብላ ቸው ፣ ማ እሺ ይለኛል ? እንዲህ ዋዛ !''

"እነሱ ምን ቸገራቸው ልጄ? ወንዶይ ተሆኑ ማጀቴ ቲነማለል አይሉትም ኖሯል? እየህ ድረስ ምን አለፋፋቸው? እነሱ የፈለጉትን ፈጣጥመው እየተሣሣቁ እብስ ሊሉ ፣ አንተ ደሞ የኔ ጅል አንድ ነገንና ቶነገ ወዲያን ግፋ ቢል እስተዛሬ ሣምንት መታገሥ አቅቶህ ፣ ዕድሜ ዘላለምክን ተንቅለህ ትቀር እንዴ ? እየህ ማዶ ያሉት ዘመዶቹም አይለቁህ'' አሉ ያሰቡለት መስለው ።

"የኔን ነገር ወዲያ ትተሽ ነው ። አዞብኛል ። እነሱንስ ምን ብዬ ልመልሳቸው?''

"አይ ያንተ ነገር? ደሞ እሚባል ጠፋ በላ! ተውጪ አገር ታዲ ባባ ትልቅ የሹም እንግዳ ይዘው መጥተዋል ፣ ይኸ ነገር አይሆንም ይቅርብን ፣ ተንተሥና ታገሬ—ገገር ያጣላናል ። መግቢያ መውጪያ ያሳጡናል ። ለሌላ ጊዜ ይሁን አትላቸውም ወይ? ደሞ የሚባል ምን ገዶ? ምነው ሲታእበት ። እኔም ለልፋታቸው ጥኢት ከኒ እላ ቸዋለሁ'' አሉ የምንዳዬን ሞት ጠልተው ሳይሆን ፣ የቀኑን አጉልነት በመገመትና ዳግመኛ በሱ ጦስ ሊመጣ የሚችለውን ጣጣ በመፍራት ።

አፈሣ ፣ ሐሳቡ ተበታትኖ መንፈሱ ተንቀራጠጠ ። ውስጡ ባዶ ሲሆን ፣ ኑሮ ቅዠት ፣ ኑሮ መና ሆነችበት ። "እኛ መሆናችን ታልታ ወቀ ምን ቸገረን ገደብ አልፈውና ጀራን ተሻግረው ይሄን አረት የሚለን የለ" ብለው እሺ ባሉት በምንዳዬ ደመኞች ተማምኖ ፣ ድፍረት ቢጤ በመላበሱ የሴትዬዋን ምክርና አይሆንም ባይነት ለመቀበል ሁለመናውን ተናንቀው ። እናም እምቢታው አየለበት ። ቀን በአሳቻ መንገድ አረሀ—ላረሀ አንከራቶ ፣ ማታ በጨለማ እንደ ዱር አውሬ አባዝኖ ያመጣቸውን ሰዎች ፣ በተልካሻ ሰበብ ያውም ደመኛን ያክል ሰው ለመበቀል አሲረውና ሰንቀው ከመጡ በኋላ ፣ እነ እከሌ ስላሉ ፣ እነ እከሌ ስለሚቆጡ ብሎ ያሰቡትን ሳይፈጽሙና ያቀባበሉትን ሳይተኩሱ እንዲመለሱ መንገር እጅግ አሳፋሪ ውርደትና ኃፍረት ሆነበት ። በሚጭለመለመው ኩራዝ ዙሪያ ተፋጠው እንደ ተቀመጡ ተኩስ በመሰማቱ ፣—

"አቤት እኔ! ዐፈር በበላሁት! ሞቼ ባረፍኩልህ ዘንድሮ ቀን" አሉ ድንገት ተነሥተው ።

"አላልኩሽም እቴዋ! መች እንዲህ የዋዛ ሰዎች ናቸው" አለ እሱም ደንግጦ ።

"እንግዲህ ወዴት አባቴ ልግባው፣ ወዴት አባቴ ልሒደው፣ ደሞ እዚህ አንተ ጋ መሆኔ!"

"እመለሳለሁ አላልካቸውም ኖሯል እንዴ?" አለች አስካደች አካላቷ እየራደ ።

"ምን መላ አለው ብላቸው፣ ስዘገይ ጊዜ የነደምኩ መሰሏቸው ይሆናላ?"

"እኮ አሁን ምን ይብጀኝ፣ ወዴት አባቴ ልሒድልህ፣ ካንተ ጋር ያገናኘኝ የዘንድሮ ቀን፣ አሁን እንግዲህ በየት አባቴ ነው እቤቴስ እምገባው ፣ ሰው ሁሉ ግልብጥ ብሎ ነው እሚወጣው" ብለው ወደ በሩ ሲሔዱ ፣ እንደገና ሁለት ጥይት በመተኮሱ ፣ አቤት ! አቤት! አቤት! ተጫረሱላችሁ !" ብለው ወደኋላ ሸሹ ። ሁሉም ጸጥ ብለው ቆሙ ። ምስቱም በእግረ—ሕሊና ተቢታተኑ ። ስቃይ ፣ መከራ ፣ ሽብር እየታያ ቸው ። የአስካደች ሕሊና መለስ እንዳለ ፣ ቀስ ብላ ከቤት ወጣች ። ከልዩ ልዩ ነፍሳት ሲርሲርታና ከዝግተኛ ነፋስ በስተቀር አካባቢው ጸጥ ብሏል ። ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱም ፣ ሹክክ ብለው ወጥተው አጥሩ ጥግ ልጥፍ አሉ ።



ከቀኛዝማች ቤት አካባቢ አንድ ሰው ጉብታ ላይ ሆኖ ፣ "አብዬ! ከየት ነው ይኸ ተኩስ?" አለ ። ሰውዬውን እነ አስካደች በድምፁ ዐወቁት ።

"እንዲህ ወደዚያ ሃች ነው ፣ ጥኢት ራቅ ይላል" አለ መላኩ ከማይታይ ቦታ ። እሱንም ዐወቁት ። ነፍሳቸው ገባች ። "ተመስገን ! ተመስገን! አለሃ የኔ ጌታ! እኔ ነኚ ወላዋይዋ ወለወልዳዋ አንተስ አልከዳኸኝም" ብለው ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ መሬቱን በደስታ ሳሙ ። አስካደችም እፎይ አለች ። ተመልሰው ሲገቡ አፈሣ እበሩ ጥግ ተለጥፎ ነበር ።

"እስቲ ይኸን ያሁኑን አኳኋኔን አይተህ ፍረድ ፣ በል ፍረድ!" አሉ በማስተዛዘን ። አፈሣ ውስጥ ውስጡን 'አጉል ሆንኩኝ ፣ እስቲ በየት አባቴ ሔጄ አገኛቸዋለሁ' በማለት ተርበትብቶ የነበር ልቡ ለራሱ ጉራ ያህል በመጽናናቱ የሰማውን ተኩስ በማናናቅ ፣

"አይዞሽ አትፍሪ ፣ እንዲህ ከመሳቀቅና ቲፈሩ ተመኖር መገላገል ይሻላል" አለ ወደ ጓዳ እየገባ ። ቀደም ሲል ካቀረቡለት ሐሳብ ባል ተለየ ሁኔታ እያስተዛዘኑ ተማፀኑት ።

"እማይሆን ነገር ነው እቴዋ ። በየሁ እንደ ወጣሁ እቀራታለሁዬ ፣ ኑ በሉ እንመለስስ አልላቸውም ። ተየህ ቀደም ስንተዪ አሉ መጡ ስንል ነገራችን ተበለሻሸ ። ዛሬ ደግሞ በግርግር መኻል ወጣ ገባ ሲል እናገኘዋለን ፣ አለያም ሰከሮ እንደተኛ እዚያቹ ድብን እናረገዋለን ብለን ቆርጠን መጥተናል ። አሁን ታዲያ እዚህ ድረስ ታመጣኋቸው በኋላ ምንትስ ቅብጥርስ ብል የሌላ ያስመስልብኛል" አለ በምሬት ።

"ስምህ እንደሚሰበር መች አጣሁት፣ በሬ አድናለሁ ተብሎ አብሮ ገደል አይገባ! እነሱም የመጡት ላንተ አስበው አይምሰልህ ። ባንቱ ሰበብ ——" ብለው ሳይጨርሱ ።

"ቢሆንም እቴዋ! በገደብ የተዉትን ነገር ቆስቁሼ ያጋጋልኳቸው እኔ — —"

"ኧረ በዛሬው ሚካል ይገፍሃለሁ! ኧረ የዛሬን ሰውረኝ! ምነው ሰንትና ስንት ነገር ስታለ እንዲህ መሆንህ?" አሉ ጉሮሯቸው እየሻ ከረና እንባቸው እየከተረ ። "አንተም ሰው ሆንከና አላገጥክብኝ፣ ወይ ነዶ! በየት በኩል ይሆናሊ ፣ ይኸነዬ ነበር ያንን ምንዳዬን ይዞ ከተፍ ማለት !" አሉ በልባቸው የልመናው ርዝማኔ ስለ ሰለቻቸው ።

"ኧረ ተይ እቴዋ! ኧረተይ እንዲህ አትበይ፣ እንዴት አርጌ ላሳ ይሽ አንጀቴን፣ ቀኛማችስ ቢሆኑ መች አዘኑልኝ፣ ከየትም የመጣ ባዳ ቢብስባቸውም አዶል ፣ ቤት ንብረቴን ጥዬ ስሔድ ቀዳዳ ቀርበቦ

የጠፋቸው ያክል እንኳ ትዝ ያላልኳቸው ። ቢያስቡልኝማ ስንትና ስንት ብልሃት ነበረው ። አገልግሎን ከልጅ ቀምተውብት ነው ስትይ በቂያቸው ነበር" ብሎ መሬቱን በጠበንጃው ሰደፍ ደቅ-ደቅ-ደቅ አድርጎ ራሱን በትዝብት ነቀነቀ ።

የወ/ሮ አልፍ— ይከንዱ ፣ የተሰፋ ብርሃን ጨልሞ ነፍሳቸው ተሸቀጠቀጠች ። ክፉኛ ነደዳቸው ። 'ቆይ አባክ! እንዲህ እንዳላንገዋከብኸኝ አትቀር! ወይኔ ልጂትየ' አሉና በልባቸው አንድ የመጨረሻ ደህና መላ አገኙ ። ያባቱ ታቦት ነው እያለ የሚያምነውን ታቦት አስታወሱ ። "እሪ በሥላሴች! በናት ባባትህ አጥንት ይገባሃለሁ!" ብለው ፣ የሥጋት እንባ ቢተናነቃቸውም ፣ ልበ ድንጉጥነቱንም ስለሚያውቁ ፊታቸውን ቋጠሩ ። 'አንት በክት የምር መስሎሃል! ቆይ ይቺ ቀን ትለፍ' እያሉ በልባቸው ።

አፈሣ ያን ያህል በማስደግደጉ ያሸነፈ ስለ መሰለው ፣ ውስጥ ውስጡን በኩራት እየታሸ ራራ ። ያን ያህል በመለመኑም ያሸነፈ መሰለው። ጥቂት አዋይቶ እንደ ሸኛቸው ፣ የሴትዮዋ መንፈስ በመጠኑ ተረጋግቶ፣ የሱ ግን በሐሳብና በጠወለገ ተስፋ ተናግቶ ነበር ። ያንኑ ሊያርቅ የተቃረበ ተስፋውን ከወዲያ— ወዲህ እየጠጋገነ ወደ ቤቱ ተመለሰ ።

* * *

ልኬለሽ ፣ ተኩስ እንደ ሰማች 'በቱኝን በላኝ' ሰበብ ተነሥታ እዚያው አልጋው ላይ ቁጭ አለች ። ምንዳዩ ግን አልሰማም ። የተኩሱ ድምፅ ራቅ ያለ ቢሆንም ፣ በሥጋትና ፍርሃት ተንቀጠቀጠች ። ቸርነት ካቀማመጡ ጠንቀቅ ፣ ከጭብጡ ጠበቅ ቢያደርግም ፣ ያን መሳይ ተኩስ ዐልፎ ዐልፎ እንደሚያጋጥምና ከወደ በረሃው አካባቢ ከሚመጡ ሰዎች መካከል ፣ አገር ቀርጠው መጥተው ፣ በጨለማ ተገን ወይም በብርሃን ጭላንጭል ሰው ገድለው እንደሚያመልጡ ስለሚያውቅ ፣ ጥርጣሬው ወደዚያው አጋደለ ። ግምቱ ትክክለኛ ነበር ። ወ/ሮ አልፍ— ይከንዱ ገባ ብለው ዐረፍ ከማለታቸው ኡኡታና እሪታው ቀጠለ ።

ሁለት ሰዎች በረት ውስጥ አድፍጠው ፣ የቤቱ አባወራ ለሽንት ወጣ እንዳለ ተኩሰው እንደ መቱት ተሰማ ። ሰዉ ከያቅጣጫው ተጯጩሆ ለርዳታ ሲወጣ ፣ በውካታው ምክንያት የነቃው ምንዳዩና ከነበረበት ቦታ የመጣ መስሎ የተቀላቀለው ቸርነት ፣ አንዱ ጠበንጃውን ሌላው ዱላውን ይዞ ቁልቁል ወረዱ ። አፈሣ የወሰዳቸው ሰዎች ባልታሰበ ትርምስ ውስጥ ገብተው በማያውቁት ጦስ እንዳይያዙ አድፍጠው በሚጨነቁበት ጥሻ በኩል እነ ቸርነት ሲያሽቆለቁሉ ፤ ሰዎቹ ድምፃቸውን አጥፍተው በጉንብስ ጉንብስ ሸሹ ።



## ምዕራፍ ሠላሳ ሦስት

አዳራሾቹ ውስጥ እንደየብልጠትና ቅድሚያው ፣ ደህና መኝታና ጉን ማሳረፊያ መደብና ቦታ ያገኘው ፣ ጉዝጓዝ ሰብስቦ ፣ የጠቀለለውን እርጥብ ፊላ ተንተርሶ ፣ የቀናው ቁርበት ፣ ያልቀናው አጐዛ እንጥፎ ፣ ግድየለሹ 'ላንድ ቀን አዳር ምናባቱ' እያለ የተለሸለሸው ሰው ተከርክሞ የተጣለ ግንድ መስሏል ። አፉን ከፍቶና ጥርሱን አግጦ ፣ ላንቃና ትናጋው ተጋጥሞ ፣ አንገቱ ተቆልሞ ፣ የሚያንኮራፋው ባፍጢሙ በጀርባው ፣ በጐኑ ተኝቶ እግሩን ሌላ ሰው ሆድ ወይም ጀርባ ላይ አመናቅሮ የጫነው ፣ አለፍ ብሎ ባንድ አካባቢ የቆመና የተጋደመ መቋሚያ ፣ የተፈታ ወይም የተኅለኀለ ልቃቂት የመሰለ መጠምጠሚያ ፣ እንደ ምሰሶ ቀጥ ፣ እንደ ራበው ውሻ ጥቅልል ብለው የተኙ ካህናት ሁሉም የመጠጥና የእንቅልፍ ሰለባ ሆነዋል ። ወንዶቹ አንዱን አዳራሽና ከለል ያለውን ታዛ ሲይዙ ፣ በሌላው አዳራሽ ውስጥ ደግሞ ሴቶቹ ሰብሰብና ሰተር ባለ ሁኔታ ፣ ዐልፎ—ዐልፎ ከወንዶቹ ባልተለየ አስተኛኘት ፣ ፍንድስ — ግንድስ ብለው ፣ አብሶ አንዳንዶቹ እስከ ጭናቸው ተጋልጠው ፣ ፊታቸው ደርበብ ፣ ፍዝዝ ፣ ረጋ ፣ ሰከን ፣ አፋቸው ግጥም ፣ ክፈት እንዳለ — — እዚህም የመጠጥና የእንቅልፍ ግዳይ...

ጎሀ እንደ ቀደደ ሁሉም ቀስ በቀስ ከእንቅልፉ እየነቃ ፣ ሲንጠራራና ሲያዛጋ ፣ አጉል ቦታና መረማመጃ ላይ ተኝቶ ያደረው ደግሞ ፣ ፈጠን ብሎ ወደ ዳስ በመግባት አቻና ብጤውን እየፈለገ ረፈድፈድ እስኪል ድረስ በባዶ ሆዱ ወሬውን ቀጠለ ።

ካህናትና ደብተሮች ከእንቅልፋቸው እየነቁ በአጥሩ ዙሪያ ተስማሚ ቦታ በመምረጥ በመጽሐፍና በቃል ጸሎታቸውን አደረሱ ። የዓርብ ጾም እንጀራና ጠላውን አዘገየው ። ረፋዱ ላይ የተሠራው የጾም ወጥ ደርሶ ፣ ቁርስ ሲበላ ሁሉም ሽክና ጨበጠ ። 'ሥራ አለብኝና እቸኩላለሁ' ባዩ ፣ ለጉዞ የሚበቃውን የጊዜ መጠን እያሰበ ቀስ በቀስ እየተሰናበተ ሔደ ።

በማግሥቱና በሠልስቱም የሩቅ ዘመድና እንግዳ ተሸኝቶ ፣ ጠላ ሲጠጣ የሰነበተው ቤተኛና ሎሌ ወደ ቅራሪ ተሸጋገረ ። በመጨረሻም ዳስ ፈርሶና አተላው ፈስሶ ፣ የጐረቤት ጋንና ድስት ወደየቤቱ ተመለሰ ።

ቀኛዝማች በላይነህ ርስትና ዝናቸውን ለማሳወቅ ፣ አዲሱን ወዳጅነታቸውንም ለማጠንከር ሲሉ አቶ ወርቅነህ መዘውርን ይዘው መዞር ጀመሩ ። የተገኘውን ያህል አጃቢና ሎሌ በትዕዛዝ እያስከተሉ ፣ ካያት ከቅድም አያት ተወረሰ የሚሉትን ፣ በሹመት ስም የነጠቁትንና በሰበብ አስባቡ ያስለቀቁትን ፣ በማይጨው ዘመቻና በውስጥ አርበኝነት ሳቢያ የጠቀለሉትን የመሬት ስፋት በበቅሎ እየተዘዋወሩ አስጐበኙ ። በየደረሱበትና ውለው ባደሩበት ሁሉ ፣ የተመረጠ እልፍኝ ተለቆ ፣ ጠላው ካለበት ተፈልጎና ሙክቱ ታርዶ መስተንግዶ ይደረግላቸዋል ። 'ዛሬስ ብለው ብለው ሠራይታቸውን ይዘው እየዞሩ ይግጡን ጀመር' አለ ሁሉም በየልቡ ። ምንም እንኳ አቶ ወርቅነህ በወቅቱ እየተዘዋወሩ ካዩት እጅግ የበለጠና የሰፋ ፣ አቀማመጡም ያመቸና የለማ መሬት የሚያውቁ ቢሆንም ፣ ያዩትን ሁሉ አድንቀዋል። ጭሰኛና ተጋዥ ፣ ለራሱና ለቤተሰቡ ኑሮ ሲል ፣ የሚያሳየውን መሽቆጥቆጥና የግዴታ አክብሮት ቢመለከቱም ፣ ቅሬታም ሆነ አዘኔታ አልተሰማቸውም ።

* * *

ድግሱ ባለፈ በሳምንቱ ቀኛዝማችና አቶ ወርቅነህ ፣ ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱና መምሬ ተክለ ጊዮርጊስ ፣ እልፍኝ ውስጥ ተቀምጠው ቡና ሲጠጡ ፣ "መቼ ለመሔድ እያሰቡ ነው?" አሉ ቄሱ የመሔድ ወሬ ስለሰሙ ።

"መድኃኒዓለምን ውለን መነሣታችን አይቀርም ። ከፍ ያለ ሥራ ትተን ነው የመጣነው ።"

"እኔ እንኳ የሌላ ሳይሆን ፣ የቤተ—ክርስቲያኑን ጉዳይ ላስታውስዎት በማለት ነው ።"

"ነገሩ እንኳ ጥሩ ነው ። ግን አስታዋሽ አያስፈልገኝም ። የዚህ ሁሉ ክብርና ማዕርግ ባለቤት ማን ሆነና እዘነጋዋለሁ ። ረዳቴንና እለሁልህ ባዩን ከዘነጋሁትማ ምኑን ሰው ሆንኩት?— —እኔና እሱ እንተዋወቃለን" አሉ ያማከሩት ይመስል ።

"ይዘነጉታል ብዬስ አይደለም ፣ ከሆነ አይቀር ለልጅ ፣ ለልጅ—ልጅ እሚተላለፍ" ከማለታቸው —

"ግድየለም ፣ ግድየለም! እርስዎ ብቻ በጾምና በጸሎቱ ይበርቱ ፣ ያንን ለኔ ይተዉት! ይልቅ እርስዎን አደራ የምልዎ ፣ ዓለማዊ ሰው ምንም ቢያምኑት ዓለማዊ ከመሆን አያልፍም ። እጁ ከመቆንጣጠር



እንደበቱ ከማጥበርበር አይመለስም ። ስለዚህ በበዓሉም ባዘቦቱም ብቅ እያሉ ቤቱንም ደጁንም ሰለል ማድረግ አለብዎ ። ግቢው ለጊዜውም ቢሆን ጭር እንዳይል አቶ አስረስ ቤተሰቦቹን ይዞ አንደኛው አዳራሽ ይገባል ። ለመኖሩ እንኳ ብዙ ሰው ስላለ አያሳስብም ። ቢሆንም ——"

"ደሞ ሰው ምን ገዶ! እዚሁ ባቅራቢያም ምንዳና ቸርነት አሉ። እነሱ እያሉ ወፍም ዝር አትል ፣ እኔስ ምን ያህል ሲርቀኝ?" አሉ ሁሉንም እያዩ ።

"እዩ ፣ ምንዳዩ እንኳ ከኔ ጋ ሒያጅ ነው ። ያነዩም ያልወሰድኩት በዚያ ባዶጋ ምክንያት ነበር ። ደመኛ ያለው ሰው ምን እንቅልፍ አለው ። በናንተ በሽማግ[illegible]ቹ ብርታት ባይሆን ኖሮ ማጀቴ ድረስ አገር እንዲቆረርለት ማ በ[illegible] ይለው ነበር ። አንዳንድ ባላንጋራ ግድ የለውም እንጂ ፣ አሁን ማጀቴ ሳያገኙትና ሳያዩት ቀርተው አይደለም። የከዚህ ቀደሙም እየከነከነኝ ነው ። የተተኮሰ ጥይት 'ና ቆይ ተመለስ' አይባል" አሉ እየማቁ ።

"ወ/ሮ እልፍ ይከንዱስ እዚሁ ሰንባች ነች ፣ ትሔዳለች ?" አሉ ሳያስቡት ።

"እሷም ቤቱን እንደሚሆን ፣ እንደሚሆን አድርጋ ትሔዳለች ። አንድ ወር ያህል ብትቆይ ነው ። እኔስ ብሆን እዚያ ማ ፈቃጅ አለኝ" ። 'የናንተ ሥልጣንና ግዝት እያለ መች እንደልብ መኖር ይቻልና !' አሉ በልባቸው ።

"አንድ ወር ድረስ ምን ታደርጋለች ፣ ሚስት ከባለቤቷ ስትለይ ጥሩ አይደለም" አሉ እየፈገጉ ።

"እሱስ እውነትዎን ነው ። ቢሆንም እዚህ ያለውን ቤትና ንብረት እያፈረስን ፣ እዚያ ቤት እንሠራ ፣ ውሎ ገብ ማ ቢሆን እንዴት ጥሩ ነበር ። እሷም እዚሁ" አሉና ዝም አሉ ። አቶ ወርቅነህ መዘውር ጉዳዩ የማይመለከታቸው በመሆኑ ፣ ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ውስጥ—ውስጡን በንዴት ቅጥል ብለውና 'መሔዴ ላይቀር ምን አስለፈለፈኝ' በሚል ውሳኔ ጸንተው በንግግራቸው መኻል ጣልቃ አልገቡም ።

ምንም እንኳ መምሬ ተክለ ጊዮርጊስና ቀኛዝማች አብሮ አደግና ፣ ቄሱ በዕድሜ ከሦስትና ከአራት ዓመት በላይ ባይበልጧቸውም ፣ ቀኛዝማቹን በሀብት ፣ በሥልጣንና ቢታዋቂነታቸው ምክንያት እጅግ ከፍ አድርገው ስለሚመለከቷቸው ፣ ራሳቸውን ግን በዚያው መጠን ዝቅ አድርገው ስለሚገምቱ ፣ በተግባሩም ሆነ በምክር ወቅት የሕሊና

ሜና ይሰማቸዋል ። ይህም ንብረታዊና ሕሊናዊ ትዕዕና የቀኛዝማቹን እንደበት በትሕትናና በአክብሮት ክልል ውስጥ እንደ ልባቸው ለመሆንና ከሃይማኖታዊ ደንብ ውጪ ለመዘሞት ትልቅ መብት ሰጣቸው ። ሆኖም ቄሱ በሌሎች ምዕመናን ዘንድ የሚያሳዩትን መንፈሳዊ ጥንካሬ ስለሚያውቁ ፣ በግልም ሆነ ባደባባይ ያከብሯቸዋል ።

* * *

ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ፣ እንጀታቸው እየጫሳ ቅናታቸው ቢቀጣጠልም ፣ የምንዳዬ ማር እምባ መቅረት ፣ በአፈሣ ላይ የሚያስከትለውን ችግርና የዘመድ ጉምጉምታ በመመልከት የሱን ቶሎ መሔድ ሳይወዱ ተቀበሉት ።

እሱም የቅርብ ሩቅ የሆነችበትን መንደሩን እየናፈቀ ከዘመድና ወዳጅ ተነጥሎ ከመኖር ፣ ሳይወድ መለየትን ፣ ሳይፈራ ሽሽትን መርጦ ፣ ወደ አዲስ አበባ መሔድን ከልቡ ተመኘ ።

እስከዳችም የቀኛዝማች ቶሎ መሔድ ለባሏ ወደ ቤቱ መመለስና 'ከሰው ጋር ተስማምቶ ምንዳዬን በጥይት ያስመታው እፈሣ ነው' የሚለው ወሬ ያሳደረባትን ሥጋት የምትገላገለው እሱም አብሮ ሲሔድ በመሆኑ ፣ የሰውዬውን የመሔጃ ቀን 'ምነዬ ደርሳ እፎይ ባልኩ' በማለት በታላቅ ጉጉት ትጠባበቅ ጀመር ።

ከድፍን የማር እምባ ነዋሪዎች መካከል ግን ፣ ሁለት ሰዎች በጣም አዝነዋል ። ቸርነት ፣ የምስጢሩ ተካፋይ ፣ የብስጭት ተጋሪና የንዴት አብራጅ ጓደኛው ስለሚሔድ ፣ የለየለት ብቸኝነት ጀምሮታል ። ሌላዋ የመለየት ረመጥ ፈጅቷት ፣ ስሜትና ብሶቷን በእንባ ጐርፍ የምትገልጸው ልኬለሽም ዙሪያው ገደል ሆኖባታል ። ሁለቱም ምንዳዬን የሚያዩባት ፀሐይ ስታዘቀዝቅ ፣ ወ/ሮ እልፍ ይከንዱና እስከዳች እፈሣን የሚያዩባት የተስፋ ብርሃን ከሩቅ ወገገች ።

የምንዳዬ መነሻ ከነገ ወዲያ ሊሆን እንደዛሬ ፣ ቀኛዝማችና አቶ ወርቅነህ መዘውር ለመጨረሻ ጊዜ የሚጐበኙትን አካባቢ ለማየት ማልደው እንደ ተነሡ ፣ ቸርነት "በጣም አሞኝ አደረ ፣ አሁንም ሰማይ—መሬቱ እየዞረብኝ ተቸግሬአለሁ" ብሎ ራሱን በሻሽ አስሮ በመቅረቡ ፣ "ካመመህማ ግድ የለም ሰው ሞልቷል" ተብሎ ቀረ ።

እሱ ግን ፣ ከዚያቹ ካስቀመጣት እህል ላይ ሰባት ቁና ጤፍና ፀሥር ቁና ቀጠጠ ማሽላ ሸጠ ፣ ለባልንጀራው የመንገድ ስንቅ ለማዘጋጀት ሲል 'ታምሜ አደርኩ' በማለት አሳበበ እንጂ ፣ አልታመመም ነበር ።



ያቀረበው የሕመም ዓይነትም ከመንደር ስለማያስወጣው ፣ እዚያው ማር እምባ በርካሽ ጣለው ። ቀደም ሲል ኮትና ቁምጣ ሱሪ መግዣ ትሆነኛለች በማለት ያስቀመጣትና ያሁኗ ገንዘብ ባንድ ላይ ትንሽ ጠርቀም አሉለት ። "ከእጦት የከፋ ምን መጥፎ ነገር አለ" ብሎ ትንሽ ሆደ ጠባብ ጨርቅ ከረጢት ውስጥ ከትቶ በቁጢት ሸምቀቆ አሰራት ።

"በይ እኮ ልኬ? ባንቺ በኩል ይሻላል ። ሳይንም ለጅም የሚሞላ ነገር ቢሆን እኮ አላስቸግርሽም ነበር" አላት ያቀረበችለትን የባቄላ እንጹሽዱሽ እያላመጠ ። 'እሞታል' እንዲባል ራሱን ያሰረባት አሮጌ ሻሽ አልተፈታችም ።

"ለምን ተኸበልሽ ፣ ይቆጣል ብለሽ እምቢ አትዪም ኖሯል ወይ ቢለኝስ?" አለችው ምጣዷን እያሰሰች ።

"ቆስ ብለሽ በለዘብታ ከነገርሽው ምንም አይል ፣ አይቆጣሚ ፣ ከተቆጣም እኔ አለሁ ። እምቢ ብዬው ነበር ብለሽ በኔ አመኻኚ ። እምቢ ካለም እኔ የግዱን እሺ አስብለዋለሁ ። የእጦት ሆኖብኝ ነውዬ ፣ የኔና የሱስ እንደዚህም አልነበር —— ታዲያ ምን ያረጋል" ብሎ ድንገት ትንሿን ከረጢት ሲሰጣት ትኩር ብላ አየችው ። ስሜቷ ተመሳቀለ ። ምጣድ አሰሳዋንና እንጨት ቁስቆሳዋን ተወችው ። ቸርነትም አቀረቀረ ።

"አሁን ምን አሳሰበህ? አንተ ለራስህ ምን አለህና ነው?" አለችው አግድም እያየች ። አልመለሰላትም ። በቀዝቃዛ ሽሮ ወጥ ትኩስ እንጀራ አቅርባለት ሲበላ ፣ ምንዳዬና አሻጋሪ እደጃፍ ቆም ብለው ፤

"ያ በያሰምን የሞተው ሰው አንተን ሊገል ነበር እንዴ አባብዬ?" አለው አንጋጦ እያየ ።

"እዎ! ሊገለኝ ነበር ። ገሎኝ ቢሆን ኖሮ ምን ታረገው ነበር?"

"ታድግና ትልእ ሰው ትሆን ፣ እገለዋለኋ በጥይት!!"

"አንተ እስክታድግ ፣ እሱ ይጠፋል ፣ የት ታገኘዋለህ?"

"ፈልጌ — ፈልጌ አገኘዋለኋ !—— እማላገኘው መሰለህ?"

"ከዚያስ?"

"እኔም ግድል አረገዋለኋ ! አንድ ቀን ለታ'ንኳ እያ እደይ ያጋደሙትለት ፣ ታያዬኝ በድንጋይ ልከካው ነበር ። ሰዎቹ ታዩኝ ይቆጡኛል ብዬ ፈራሁና ዝም አልኩ ።"

"እኔ ደሞ ደፋር መሰለኸኝ ነበር ፣ ለካ ፈሪ ነህና?" አለ እየሣቀ ።

"እማደለሁ! ፈርቼ መሰለህ? ትወረውር ያዩኝና ይቆጡኛል ብዬ ነውዬ" ሲል የምንዳዬ ዐይን እንባ ከተረ ። አባት ቁልቁል ፥ ልጅ አንጋጦ እየተያዩ ፥

"ጎሽ! —— እንዳትፈራ !"

"አልፈራም እምፈራ መስሎህ ነበር?"

"ዐውቄ ነው ፥ የኔ ልጅ ፈሪ አይደለህም ። እንዲህ ጎበዝ ተሆን ክማ ጠበንጃ እሰጥሃለሁ" ብሎ አገላብጦ ስሞት ወደቤት ሲገባ "ደህና ዋላችሁ?" አለ ፊቱ እንደ ፈገገ ።

"እንዴት ዋልክ? በደህና ዋልክ?" አሉት ሁለቱም ኖር ብለው ።

"አባትና ልጅ ይኸን ያህል ወሬ ስታውሩ ሰው ዘወር ብላችሁም አታዩ?" አለ ቸርነት ።

"እንዴት ያለ ወሬ ይዘን ነበር ከዚያ ታች የጀመርን ስናወራ" አለና ምንዳዬ ጠበንጃውን ትራስጌ አስቀምጦ ከቸርነት ጐን ተቀመጠ ። አሻጋሪ የሽክናውን ውሃ በጣቶቹ አፈን አድርጎ በቀጭኗ በማንቆርቆር እንዳስታጠበው ልኬለሽ ምግብ ጨመረችላቸው ።

"በጎ ዋልኩይ? ቀለል ብሎህ ዋለ? አይ የኔ ነገር ፥ ሆዴ ባሰብኝኮ ! ሰው ይደክመዋልን እማያቁ ሰውዬ ከወዲያ ወዲህ ሲያንገላቱን ውለው" ብሎ ባዘኔታ አየው ።

"አሁንስ ደህና ነኝ ። ጢት ነበር ይኸን መኻል አናቴን በቅቶ የያዘኝ ። አሁንማ ቀለል ብሎኛል ። እህሉ አልበላልህ ብሎኝ ውሎ ፥ ይኸው አሁን ገና ወዳፌ አልኩ" ብሎ ልኬለሽን አያት ።

"እኔማ ከስንቱ ኮቸሮ አፍ ጋ የዋልኩ መሰለህ? ወሬአቸው ለዛ የለው ፥ ጨዋታቸው አይጥም ።"

"እንዲህ ታንዳንደዬ'ንኳ ማጉደሌን ዕወቀውዬ! 'በእጅ የያዙት ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራል' ነው እሚሉት" ብሎ አሣቀው ።

"ምን ታረግ? ሰው እኮ እሚያመሰግነው ሰው ሲያጣ ራሱን ያመ ሰግናል ። ይልቅ ምን ሆነህ ነው ያመመህ? ይኸነዬ አረጋሽ ታሁን አሁን መጣች እያልክ ብርድ ላይ ተቀምጠህ ስትንቃቃ ፥ ይኸ የጠር ውርጭ ሳይታወቅህ ጠብሰቆ ጥሎህ ነው" ብሎ ከት ብሎ ሣቀና ፥ "ከጠራራ ጂኒ እኮ የውድቅት ጂኒ ይብሳል አሉ ! አጣፍሮህ እንዳ ይሆን" ብሎ ተንከተከተ ።



"ኤ—ድ! አንተ ደሞ ትለው አታጣም? የምን ጂኒ አመጣህብኝ? እኔን ያጣፈረ አንተንስ የት ያጣሃል?"

"እኔ ምን ፍለጋ ስሔድ ልጄ? ሁሉም መገናኛ መገናኛ አለው።"

"ምነው ታዲያ አንተን ያሾሾ ወንዝ ጂኒ አላጣፈረህ? አሁን ተዚያ እሚብስ አለ? እምን እንደምረግጥ አላእም ነበር አላልከኝም? የረሳሁልህ መሰሎሃል?" አለ በቀስታ እየሣቀ ።

"ያንተኮ ሥጋትም አለበት ። እኔ ማንን እሠጋለሁ ። የቤቶቿም ቢሆኑ ያቁኛል? አጠይቃትም እንዴ? እኔ እንዳንተና እንደ ቆጥህ ስባንን አላድር! ያንተ ደሞ ስንቱ ይወራል" ብሎ ሣቀ ።

"ምነው ብተወው ልጄ? በሽታውን ቢያዳምጥበት ፥ አንተ እኮ!" ስትል ልኬለሽ ፥ ካፏ ነጥቆ ፥

"ኧረ ቆይ ተይው! የረሳሁለት መስሎታል — —" አለ ቸርነት

"ለምን እኔ አሳምሬ አልነግርህም? ይኸነዬኮ አልነገረህም ይሆ ናል? አንተ ብቻ የራስ የራስክን — —"

"አንቺ ደሞ ምን ልትዬ ነው? መረዳቱ ነው? አቤቱ!" አለ ምንዳዬ ቢወራበት እየተደሰተ ።

"ምነው አንድ ኽንሊታ ላይን ያዝ እንዳደረገ ሳባይኔ ድረስ እስልተህ መጥተህ — —" ብላ ስትጀምር ፥

"ሳባይኔ ሩቅ እንዳይመስልህ — —"

"የሰው ወሬ አታቆርፍድ! ዐቀዋለሁ ።"

"በሉ ይሁንላችሁ ፥ ዛሬ በኔ ላይ አብራችኋል ።"

"አንተ እህ በል ልጄ ፥ — — እቴዋ ዘርትሁን ቤት ደርሼ ትመ ለስ ፥ ሰው የለም ይልልህና ፥ 'ልኬ! አንቺ ልኬ!' እያለ ጨበጥ ቲያረ ገኝ ጊዜ ደንግጨ ጩኸቴን ለቀኩበት ። ለካ አብዬ ታዬ ሰምቶልህ ኖሮ 'ምንድን ነው? ማነህ አንተ?' ብሎ ከመጣራቱ ፥ መጣብኝ ፥ ደረሰብኝ ይልልህና የፍሪያቱ ፍሪያት መንገዱን ጥሎ በጉራንጉር ውስጥ ———"

"ጐበዝ ተሆነ አይከተለኝም ኖሯል?" አለ ምንዳዬ እየተንከተከተ።

"የተገላቢጦሹን ተወውና ፥ ጐበዝ ተሆንክ ቆመህ አጠብቀው'ም ኖሯል? ደሞ አንድ ቀን መሸቶብኝ ውሃ ወርጄ ስመለስ ፥ እኋላ—እኋላዬ እያለ አላስኬድ ቲለኝ ፥ ዝም ብዬ ስሔድ—ስሔድ ማንገቻውን ጥርቅም አርጎ ያዘና — —

“አታሸክሚውም ኖሯል? እኔ አንቺን ብሆን — — —”

“ውይ ? ዶሞ ለማሸከሙ ነው ? ቃኸው የለ የኛን አገር ? ተጥጥ— ፈረስ እስተ ቾሬ ጉር ያለውን አቀበት እንጨቴን ተሸክሞ ፡ አሊያም ባህያ ጭኖ ያወጣልኝ ነበር — — —”

“ያልነገርኩት መስሎሻል? ነግሬዋለሁ” ብሎ ተንከተከተ ።

“ማንገቻዬን ጥርቅም አርጎ እንደያዘ ፡ ያብዬ ሪታ ክፉ ውሻ ነበር ። ብቅ ቲልበት ጊዜ ፡ ዐርፎ መመለሱን ይተውልህና ድንጋይ መወርወር ፡ ውሻው ጉድ አፈላልሃ ወንድሜ ። ለካ አባብዬ እቤት ኖሮ ብቅ ቲልበት ጊዜ ደረሱብኝ ይልልህና ፡ ከቤት በታች ያጥር ካብ ነበር ያንን ዘልዬ እሔዳለሁ ሲል ተናደበትና — — —”

“ታዲያ አንተ መች ይኸን ሁሉ እንዲህ አርገህ ነገርከኝ ! አበጀሽ! እኔ ብሆን አስክበው ነበር — —መች በዋዛ !”

“ብክብ ይሻለኝ ነበር ! አንድ ሰበበኛ ድንጋይ ቁርጭምጭሚቴ ላይ መቶኝ ፡ ስንትና ስንት ቀን አመመኝ መሰለህ — — አሁን ይኽ ሁሉ ለምኑ ነው ? አጥር ዘልዬም ፡ ካብ ንጄም አላመለጥሽኝ ! አንቺም ይኸው እኔን የመሰለ ዘንካታ አገባሽ” ብሎ ሁለመናው እየተርገፈገፈ ሣቀ ።

“ዋ—’ቴ!— — ሴቱ ብር የመሰለች እያሉ ሲከታተሉኝ — —ዋል፡ አደር ብትል ኖሮ — —” ብላ ሣቀች ።

“ማባቱ ሊነካሽ? የት አባቱ ሊያራ በይ !? በመስቀሉ ዶዬበት—” ብሎ የተቆጣ መሰለ ።

“እይው እንግዲህ የሱ ጊዜ ዛሩ ቲነሣ! የተወራው የኖረ ወሬ ፡ አሁን ማ ይነካብኛል ብለህ ነው መናደድህ ? — —እኛ አገር ቢሆን ኖሮ ፡ ካላገባት ምኑ ነች እያሉ ያበግኑህ ነበር ።”

“አንተ ደሞ አይዞህ—አይዞህ ትልህ ጊዜ አታናድብኝ ። እንዲህ የዋዛ ሰው አግኝተሃል ? ቀድሞ ነገር ማባቱ ነከቶኝ ? ማባቱ ቀና ብሎ አይቶኝ? እኔም ብሆን ሌላ ወንድ የጨርቄን ጫፍ አይነካት!”

“አይ! እንዲያው ምን ላርግሽ! — — የተናደድኩ መስሎሃል ? እኔ እንዳንተ ወጋግራ እያላተመኝ ስደናበር አላድር! እዳሜ ዐይኑ ሲቀላውጥ ፡ ላስ አረኳት” ብሎ ምንዳዬ በረገርሙ ሣቀ ።

* * *



ምንዳዬ ፡ አካለመጠን እንደ ደረሰ ነቃ—ነቃ ማለት በመጀመሩ ፡ ጥርሱን ነጋ—ጠባ ፋቅ ፋቅ ፡ ልብሱንም አጠብ አጠብ ማድረግ አበዛ። ዘፈኑም፡ ሽለላውና ቀረርቶውም ጨመረ ። ባባቱ ያለጊዜ መሞት የሚናደዱት እናቱ ፡ ሲወጣና ሲገባ ባዩት ቁጥር ፡ በልጄ አደገልኝ ስሜት ልባቸው ደስ ፡ ፊታቸው ፈገግ ይል ጀመር ። “አሁን እንደዝጊሃር ማዞቱ አለ ? ምነው እንዲህ አድጎ ላንድ ቀን እንኳ አይቶት በሞተ ኖሮ” ይላሉ ። ሁለት እህቶቹ ተድረው በመሔዳቸው ፡ የመጨረሻውና አንድ ወንድ ልጃቸው ምንዳዬ ብቻ ነበር አብሯቸው የሚኖረው ። ጢሪያቸውና የማታ ፀሐያቸው ሚስት አግብቶ ሁለት ፡ ሦስት ፡ አራት— —እንዲሆንላቸው ይመኛሉ ። ልጁን ማዘል ፡ ማጫወትና ይዞ መዞር አምሯቸዋል ። እናም ፡ ከዚያ ቀደም እንደ ነገሩት ፡ “ምንዳሁነኝ?” አሉት በተንደረከከው ፍም ላይ ባርማሺላ እየጠበሱ ።

“እመት” አላቸው ፡ የፈለፈለውን እየሰጣቸው ።

“አንተም ቢሆን ሁለት ሦስት ሁን ፡ እኔም ደስ ይበለኝ” አሉት ፈግግታ ባጸደለው የናትነት ገጽታ ።

“ምን!” አለ ነገሩ ቢገባውም ።

“እጨዋ ቤት ፡ እደህና ሰው ልግባልሃ? እቅሜን ፈርቼው ነውዴ እምናም እስቤ ነበር?”

“ምን?” አለ ፈገግ ብሎ ።

“እንዲሁ አይኖር ልጄ? እናት ምን ብትወድ እናት ናት ፡ እኔ ቀድሬ አንተን ወለድኩ ፡ ባላገባ ኖሮ አንተን የት አገኝህ ነበር? አንተ ደሞ እንደኔ ልጅ ውለድ ፡ ሚስት አግባ ነው እምልህ ፡ ልጭልህ ፡ ሰው ዝንታለሙን ተናት ፡ ታባቱ ጋ አይኖርም ፡ እይቼ አጠገቤ ትሠራለህ” አሉት በሚንቀለቀለው የማገዶ ብርሃን ፡ አይቶ በማይጠግበው በእናት ዐይን እያዩና እየፈገጉ ። ዝም አለ ።

“እኮ በል አንድ በለኝ? ተየህ ቀደምም ዳር—ዳር እያልኩ ነግሬህ ነበር — — ዝም ስትለኝ ጊዜ ያሰበው ነገር ቢኖር ነው ብዬ ችላ እልኩህ ። ተዚያም ወዲህ ተነገ ተዛሬ ስል ቆየሁ ።”

“ሆን ብዬ ነው ዝም ያልኩሽ ። ተኔ እሚበላልጡት ሁሉ ታያገቡ” ብሎ እንደ ጀመረ ፡

“አንተ የሌላው ምን ያረግልሃል? ሁሉም በየቤቱ ዘመደ ብዙ ነው ። ሦስት—አራት ወንድማማቾች አሉ ። አንተ ማን አለህ? አንድ ብቻህን ነህ ። እቶችህም እየሔዱበት አገር ወልደው ከብደው ይቀራ

ሉዬ ፣ አይመጡ ። አግባና ወለድ ፡ ወንድም ይሆንሃል” አሉና የተቀበሉትን ቃሙ ። በተደጋጋሚ ተነጋግረው ተስማሙ ። ሁለቱም ደስ አላቸው ። የወደዳትን ልጅ ባይነግራቸውም ቀስ ብለው ሰልለውና ጓደኞቹን ጠይቀው ዐውቀዋታል ። ወደዋታል ።

አንድ ቀን ማታ ራት ሲበሉ ፣ የተለመደው የጋብቻ ጥያቄ ቀረበ። ምንዳዬ አንገቱን ሰበር አድርጎ ፤

“ሳባይኔ ያብዬ ከተማ ልጅ ብትሆን ምን ይመስልሻል?” አላቸው ።

“የትኛዋ?”

“ትልአዋማ አግብታለይ ። አንድ ናት እቤት ያለችው” አለ ቀና ብሎ ።

“በምን አየሃት ልጄ! እኔም እሷን ነበር ያሰብኩልህ ። ጥሎብኝ ፣ ውቃቢ —አምላኬ ይወዳታል ። በዚህ በኛ ደጅ ወደ ተክልዬ ስትሔድ፣ ጉትት አርገሽ አስቀሪያት አስቀሪያት ይለኛል ። ማለፊያ ፣ አንገተ—ሰባራ ልጅ ነች” አሉት ።

አጐቱና ሌሎች ሁለት ሽማግሌዎች ተጨምረው አቶ ከተማ ቤት ሽምግልና ተላኩ ። በሁለተኛው ቀጠሮ ‘ይሁን’ ተባሉ ። ቃል አስረው የተመለሱ ዕለት እናትና ልጅ ፈነጠዙ ።

ያቺ ባገኛት ቁጥር ውሃ የያዘ ገንቦዋንና እንስራቷን ፣ የግድ ተቀብሎ አቀበት ቁልቁለቱን የሸኛት ፣ እንጨት አሳብሮና ተሸክሞ የወሰደላት ፣ አያችሁብኝ ብሎ ዱላ የተማዘዘባት ፣ የቀልቡ ማረፊያና የልቡ መርኪያ የሆነችው ልኬለሽ ግን ፣ መታጨቷንም ይሁን ለባል መስጠቷን አላወቀችም ።

ለጋብቻ የተስማሙበት የመጀመሪያ ዓመት ፣ “የዘንድሮ መኸር አላስደሰተም ፣ እንኳን ለልጅ መዳሪያ ለቀለብም አያቢቃ” በሚል በልኬለሽ አባት ችግር ተላለፈ ። በሁለተኛው ዓመትም ዋናው ሳቢ በሬአቸው ከበሬ ጋ ሲዋጋ ገደል ገብቶ በመሞቱና የመቀናጀ አዝመራም የማያወላዳ በመሆኑ በድጋሚ ሳይሳካ ቀረ ። እናትና ልጅ መክረው፣ ሽማግሌዎች እንደገና ተላኩ ።

“ተናንተ ፈቃድ አንወጣም ብለን ፣ ይኸው ድፍን ሁለት ዓመት ዐለፈ ። እናንተም ወዳችሁ አይደለም ። ችግርና እክል እማይገባበት ቤት የለም ። እየሁላችን ጋ አለ ። ታዲያ በዚህ መኻል ደሞ ልጆቹ አጉል ሆኑብን ፣ ሰው መቼም ቲኖረውና እጁ ቲሞላ ነው በጅጉ ጠምቆ ፣ ጋግሮና አርዶ ጉዳዩን እሚያወጣው ። ተሌለ ምን ይደረጋል ። እንደ



ጊዜውና እንደ ወራቱ እየታየ ደሞ ባቅም—ባቅም ይደረጋል ። ይኸ ልጅ ‘ዘንድሮን አታሳልፉብኝ’ ብሏል ። ‘ባይሆን እኔም ያእሚን እደግፋቸዋለሁ ። እናቴም እየደከማት ነው’ ብሎ ልኮናል” አሉ ከተላኩት ሽማግሌዎች መኻል አንዱ ነገሩን ሲያጠቃልሉ ።

“እኔስ ደስ ቢለኝ መች ጠላሁ! ካምናው ዘንድሮ ፣ ከዘንድሮ ለከርሞ ይሻል ይሆን ስል ባናት ባናቱ ይመጣብኛል ። እኔስ መቸ አጣሁት ። ለዚያውም እናንተ ሆናችሁ ነው ። እሱም እምንገድ ባየኝና ባገኘኝ ቁጥር ተሳቆ ሞተ! ምናባቴን ላርግ ብላችሁ ነው ። ተልጆቼ መኻል እምወደው እሷን ነው ። ዐይኔ ነች ። ለሷ ያልሆነ ለማን ሊሆነኝ ነበር ። እኔ እንግዲህ ተዚህ ወዲያ ምንም አላስቸግራችሁ ። ይህን አረጋለሁ ፣ ይህን እፈጥምበታለሁ የምለውም አቅም የለኝ ። እሷም ዕድሏ እስቲቀናና ቀን እስቲወጣልን ትቆይ ፣ እናንተም እንደ ወደዳችሁ አርጉ” አሉ የልኬለሽ አባት ፣ ያልታሰበ እጦት በሰበረው አንደበት ።

የአባትዬው መልስ ለምንዳዬ ሽማግሌዎች አጥጋቢ አማራጭ በመሆኑ ደስ ብሏቸው ተመለሱ ።

“ምነው ይኸን መልስ አምና በሰጡ ኖሮ! ወይ ነዶ!” አለ ምንዳዬ አንድ ዓመት በከንቱ አለፈብኝ ብሎ ።

ምንዳዬና ሽማግሌዎቹ ፣ ባገሩ ባህል መሠረት እርስ በርስ መክረው ተስማሙ ። የልኬለሽን እናት አነጋገሯቸው ። እናትዬዋም ጉዳዩን ካሰላሰሉ በኋላ ፣ “እምቢ ብልስ ምን መላ አለው?” ብለው በነገሩ ተስማሙ ።

የምንዳዬ እናትና ጐረቤቶቻቸው የድግሱን ሥራ በድብቅ ተያያዙት ። የእንጀራ እህሉ ማጀቴ ውሃ—ወፍጮ ተፈጨ ። የጠላ እህሉ ተዘጋጀ ። ቀኑ ተወስኖ መሰናዶው እንደ ተጠናቀቀ ፣ ሁለቱ ሽማግሌዎች እንደገና የልኬለሽን እናት አነጋገሯቸው ።

“በየት በኩል ይሻላል?” አሉ እናቷ ትክዝ ብለው ።

“ጉባ አክስትሽ ጋ ልላክሽ ብትሏትስ?”

“ከየቱ? በዚያስ አይሆንም! ትደነግጥብኛለች” አሉ እንባቸው እየመጣ ።

“ቁቁ ማለቷና መደንገጧማ የት ይቀራል? ይኸን አጣነው ብለሽ ነው?” አሉ አንዱ ሽማግሌ ። በመጨረሻ ባንድ ብልሃት ላይ ተግባቡ ። ይኸውም ልኬለሽን ከአንዷት ጓደኛዋና ከሌላ የጐረቤት ሴት ጋር

እንጨት ለቀማ መላክና ፥ ባለትዳር ለሆነችው ሴትዮ ነገሩን ነግሮ ከእንጨት ሰበራ መልስ ምቹ በሆነ መንገድ ይዛቸው እንድትመለስ ።

ልኬለሽ እንደ ተለመደው ፥ መጫኛዋን ጠቅላና ድግድጋቷን አሳ ምራ ከባልንጀራዋና ከተመከረችው ሴትዮ ጋር እንጨት ሰበራ ስት ሔድ ፥ ምንዳዬና ሁለት ጓደኞቹ ፥ ጢሻ ውስጥ አድፍጠው እየተሣሣቁ አሳለፏቸው ። ቀስ ብለውም ባሳቻ መንገድ ተከተሏቸው ።

ልኬለሽ ስትሰቅ ፥ ስታወራ ፥ ስትዘፍን ፥ ስትቀልድ ———የሚ ሰማት ምንዳዬ ፥ ጠልፏት እስኪገባ ቸኮለ ። የልቡ ምት ፈጠነ ። እያያት ናፈቃት ። ድምጿ እንደ ውሃ አሧሪት ሕሊናው ውስጥ ተሽከረከረ ። የሚያይና የሚሰማው ሁሉ ደስ አለው ። እነ ልኬለሽ እንጨታቸውን ተሸክመው ወደ ቤት ሲመለሱ ፥ እነ ምንዳዬ እየተከተሉ ከተመከረ በት ቦታ ደረሱ ። ልኬለሽ ከመኻል ሆና እየዘፈነች ስትጓዝ ፥ ሦስቱም ወንዶች ሴትዮዋን አሳለፉና ሁለቱ የልኬለሽን ሸክም ከግራና ቀኝ ድንገት ብድግ ሲያደርጉት ፥ ምንዳዬ ማንገቻውን ባንገቷ በኩል አወ ለቀና ሁለት እጆዋን ይዞ ሲሸከማት እሪታዋን አቀለጠችው ።

“ዝም በይ ! እስቲያባሽ ትጮሂያለሽ !” አላት በቁጣ ። ኡኡታ ዋን ስታስነካው አውርዶ አፏን አፈነው ። አንደኛው ባልንጀራው አሮጌ መቀነቷን ፈትቶ አፏን አሰረና ፥

“ና አሳዝለኝ” አለው ሌላውን ። ልኬለሽ አልታዘልም በማለት ባለ በሌለ ኃይሏ ተፈራገጠች ። አልሆንላትም ። እንድ ሁለቴዬ ቀላል ጥሬ እንደ ቀመሰች ፥ ከማይለቅ ወጥመድ እንደ ገባች ዐወቀች ።

“ዋ ! እንዲች ብላችሁ እንዲት ወሬ ብታወሩ ! በሉ ቀጥ ብላ ችሁ ሒዱ” ተባሉ ሴቶቹ ። ጓደኛዋ እንጨቷን ጥላ እያለቀሰች ፥ ሴት ዮዋ እንዳላወቀች ፥ “ምነው ዛሬ ቀን እግሬን በሰበረው” እያለች ጉዞ ቀጠሉ ።

ልኬለሽ ኡኡ እንዳትል ታፍናና የዱላ ውርጅብኝ ፈርታ ከፊት በምንዳዬ ፥ ከኋላ በባልንጀራው ታጅባ እየንፈረቀች ወደ ምንዳዬ ቤት ታዝላ ስትገባ ዕልልታው ቀለጠ ።



## ምዕራፍ ሠላሳ አራት

ምንዳዬ ፥ በዕለቱ ከቀኛዝማችና ከአቶ ወርቅነህ መዘውር ጋር ስለ ዋለው ውሎ ሲያወራላቸው ፥ “አንዳንድ ቀን ደሞ እሚያሯሩጥ ነገር አለባቸው” አለች ልኬለሽ ። “ድንገት ብድግ ይሉና መንገድ ይገባሉ ፤ ዛሬስ አይመለሱም ሲባሉ ፥ ከተፍ ይሏታል ። ሰው ይደክመዋልን እማ ያውቁ ሰውዬ ! እኔ እንዲያው አቅም ቢኖረኝ ሌላም አልመኝ ። እሳቸ ውንም ጠበንጃ አሸክሞ ሲያስሮጡ ማዋል ነበር ! ታዲያ በየት !” አለች እየሣቀች ።

“ምን በደሉሽ ልጄ ? እኛስ ‘ዕድላችን’ ሆኖ ነው ፥ እሳቸው ደሞ ምን በወጣቸው ? መቼም ሰውን ተጠላነው ፥ የኛን ክፉ ለሱ ነው ።”

አልመለሱለትም ።

ቀኛዝማች ፥ ስለ ልኬለሽ መኖር ወይም አለመኖር ደንታ የላቸ ውም ። በሳቸው ዐይንና ግምት ፥ በአካባቢው ከሚግበሰበሱት አንዷ ነች ። እውነትም የኑሯቸው ደረጃ ሲነጻጸር ከትልቅ ዳመራ አጠገብ የምት ቤራ ስንጥር ትመስላለች ። ታዲያ እንዴት ይዩዋት ?

“እውነክን ነው ልጄ ፤ እኔ ለያውስ ምኑን ዐውቄው ! ይኽነዬኮ ደህና ሰው ይሆኑ ይሆናል” ብላ ምንዳዬን ላለማስከፋት ንግግሯን ጠገነችው ።

“በሉ ሌላ ጨዋታ እንጫወትበት ፥ እኛ ስለነሱ እናወራለን ፥ እነሱ ከጆሯቸውም ጥፈውን ዐያቁ” ብሎ ቸርነት እየሣቀ አሣቃቸው ።

መዓዱ እንደ ተነሣ “ያንን ነገር ሳምጣው እንዴ ?” አለች ልኬለሽ ቸርነትን እያየች ።

“የቱን?” አላት እየጠረጠረ ።

“ያንን ነዋ! ያንን ቅድም የሰጠኸኝን ።”

“ምን ነካሽ ? ደህናም ሰው አልነበርሽ እንዴ ? ምን ነበር የተባባ ልነው ?” አላት በመገረም ።

“አይ ያንተ ነገር ! ምን እንዳይል ብለህ ነው ? ከሆነ አይቀር ሁላ ችንንም ደስ ይበለን ።”